# ተልዕኮአችን የሆነው የእግዚአብሔር ፍለጋ

ጃኪይ ኦስክ

## ማንነቶች እና ምሳሌዎች፡- ከማቴዎስ ፣ከማርቆስና፣ ከዮሐንስ ወንጌላት

ትምህርት1፡ … እስኪሰጥ ድረስ …እንዲሁ ወዷልና —ኒቆዲሞስ
ትምህርት 2: መሲሁ ይሆንን ?—ሳምራዊቱ ሴት
ትምህርት 3: ዛሬ በአንተ ቤት እሆናለሁ—ዘኬዎስ
ትምህርት 4: ጆሮ ያለው ይስማ — ዘሪው፣አፈር፣እና ዘር
ትምህርት 5: ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ — ደጉ ሳምራዊ
ትምህርት 6: ታላቅ ድግስ አደረጉ— ልጁን በጉጉት የሚጠብቀው አባት

“ ቃልህን በልቤ ሰወርኩ…”መዝሙር 119:11

## *መቅድም*

*ቀሪውን የህይወታችሁን ዘመን መልክ የሚያስይዘውን አስገራሚ ጉዞ ጀምራችኋል። የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ከምታጠኑበት ከዚህ አስደናቂ ጉዞ የምታተርፉት ነገር የሚወሰነው ለጥናቱ በምትሰጡት ጊዜ እና በሚኖራችሁ ጠንካራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህንን ጥናት በአግባቡ ማጥናት ከእግዚአብሔር ዘንድ የበረከት የተስፋ ቃል ያለው ነው። ይህም በረከት በምታጠኑት ቃል ውስጥ የሚገለጥ ነው የሚሆነው።*

*የተሳካ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ታደርጉ ዘንድ በጥናታችሁ ወቅት በእጃችሁ ሊኖሩ የሚገቡ የጥናት መርጃ መሳሪያዎች አሉ ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ :*

1. *"ተልዕኮአችን የሆነው የእግዚአብሔር ፍለጋ" የሚለው የጥናት ክፍል ጥራዝ ።*
2. *አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ : ከዚህ ቀደም መጽሐፍ ቅዱስ የሌላችሁ ከሆነ እና አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ለመግዛት ካሰባችሁ የምትገዙት መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ነገሮች የያዘ ቢሆን ይመረጣል:*
   - *ሀ። በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ለሚገኙት ምንባቦች ወይንም ቁጥሮች ማጣቀሻ የሚሆኑ ጥቅሶችን ከእግርጌው ወይህም በመካከሉ የያዘ።*
   - *ለ። በመጽሐፉ የመጨረሻ ገፆች ላይ የቃላት ማውጫ ያለውና።*
   - *ሐ። በመጽሐፉ የጀርባ ገፆች ላይ ጥቂት መሰረታዊ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካርታዎችን የያዘ ቢሆን ይመረጣል።*
3. *እርሳስ ወይንም እስኪብርቶ*
4. *ማስታወሻ የምትይዙባችው ደብተር*

*በተለይ በቁጥር ሁለት ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በተሟላ ሁኔታ ካገኛችሁ ይህንን ጥናት በጥሩ ሁኔታ ማጥናት ትችላላችሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ የምታጠኑት ይህንን የጥናት ክፍል ከሆነ ከዚህ ጥናት በፊት ያለውን "የመፅሐፍ ቅዱስ ቅኝት" የሚለውን የጥናት ክፍል በቅድሚያ ማጥናት ያስፈልጋችኋል። ይህ "የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኝት" የሚለው የጥናት ክፍል መጽሐፍ ቅዱስን በቀላሉ መጠቀም የምትችሉበትን መንገድ ያስተምራችኋል። ነገር ግን ቀጥለን የምናጠናውን "ተልዕኮአችን የሆነው የእግዚአብሔር ፍለጋ" የሚለውን የጥናት ክፍል ለማጥናት የሚረዳችሁ ነገር አይኖርም ምክንያቱም እያንዳንዱ የጥናት ክፍል ራሱን ችሎ እንዲጠና ተደርጎ ነው የተዘጋጀው።*

*መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ልታጠኑት የገዛችሁት የራሳችሁ መጽሐፍ በመሆኑ፣ ጠቃሚ የሆነና ህይወታችሁን የነካውን ክፍል ስታገኙ በምልክት ማድረጊያ ማርከራችሁ በላዩ ላይ ማስመር፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ማክበብ እንደዚሁም ለማስታወስ የሚረዷችሁን የተለያዩ ምልክቶችን ማድረግ ሊያስፈራችሁ አይገባም! ምናልባትም የተለያዩ አዳዲስ ሃሳቦችን ፣ጥያቄዎችን እንደዚሁም ህይወታችሁን የሚነኩ*

ነገሮች ካገኛችሁ ከዚያ በተጨረማሪ በማስታወሻ ደብተራችሁ ፣ወይንም እንደሞባይል ስልክ ያሉ ነገሮችን በመጠቀም መያዝ ትችላላችሁ።

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ማንኛውም ሰው በቀላሉና እራሱን ችሎ እንዲያጠናቸው ታስበው ቀለል ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው። ስለዚህ በትጋት፣ እና በአግባቡ ካጠናችኋቸው ያለምን ችግር ማጠናቀቅ ትችላላችሁ ማለት ነው። ይህንን ጥናት ስታጠኑ አዳዲስ ሃሳቦችን ፣መልስ የሚያስፈልጋቸው አስቸጋሪ ጥያቄዎች ሊገጥሟችሁ እንደሚችሉ ማወቅ ይገባችኋል። እንደተለመደው ሌሎች ሰዎችን በዚህ ጥናት ላይ መጋበዛችሁን አትዘንጉ።

ይህንን ጥናት ስታጠኑ ህይወታችሁ በደስታ የተሞላ ይሆን ዘንድ እንመኛለን። ልባችሁም በቃሉ ውስጥ ለሚናገራችሁ ለእግዚአብሔር ድምፅ ምላሽ የሚሰጥ እና ለመታዘዝ የተዘጋጀ ይሁን። በምታጠኗቸው በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ፣መድኃኒታችን በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእናንተ የገለጠውን ታላቅ ፍቅር የምትረዱበት ጥናት ይሆንላችሁ ዘንድ ተመኘን።

## መግቢያ

በቀጣዮቹ ሶስት ተከታታይ ትምህርቶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ሰዎች ጋር ትተዋወቃላችሁ። እነኚህ ሰዎች ከኢየሱስ ጋር የቀረበ ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን አንደኛው፡ ፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ ነው፣ ሁለተኛዋ ደግሞ፡ በውሃው ጉድጓዱ አጠገብ የነበረችው ሳምራዊቱ ሴት ስትሆን ፣ሶስተኛው፡ የቀራጮች አለቃ የነበረው ዘኬዎስ ነው። እነኚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር መንግስት መታጨት የሚገባቸው ሰዎች ባይመስሉም ኢየሱስን በማግኘታቸው ግን ህይወታቸው ለዘላለም ተለውጧል። እስቲ ታሪካቸውን በጥሞና ተከታተሉ። በእነርሱ ስፍራ ሆናችሁ ኢየሱስ ያመጣላቸው የምስራች ምን ያህል ህይወታቸውን በደስታ ሞልቶት እንደነበር ተመልከቱ።

በዚህ ጥናት ኢየሱስን እንደ አንድ ታሪክን እንደሚተርክ ሰው ሆኖ ታገኙታላችሁ። ትምህርቱን ለመስማት በጉጉት በዙሪያው ለተሰበሰበው ሕዝብ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም መንፈሳዊ እውነቶችን እንዴት ይገልፅላቸው እንደ ነበር አስተውሉ። የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መስማት እና መቀበል እንዳለባቸው ለማስረዳት ታዋቂውን "የዘሪውን ምሳሌ" በመጠቀም ድንቅ ትምህርት አስተምሯል። ለባልንጀሮቻቸው መልካም ማድረግ እንዳለባቸው ሊያስተምራቸው ደግሞ የደጉን ሳምራዊ ታሪክ በመጠቀም በግሩም ሁኔታ አስተምሯል። የእግዚአብሔርን ጥልቅ ፍቅር እንዲረዱ ደግሞ የጠፋውን ልጅ ታሪክ በመጠቀም አስተምሯል።

ኢየሱስ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም የአባቱን ሃሳብ ሲያስተምረን የልቦናችን ጆሮዎች ተከፍተው እንድንቀበለው ይፈልጋል፣ ምህረቱ ለሚያስፈልጋቸው ምህረቱን እንነግራቸው ዘንድ ለመላክ ሁልጊዜ ዝግጁ እንድንሆንለት ይፈልጋል። ጠፍተው የተገኙትንም እጆቻንን ዘርግተን በፍቅር እንድንቀበላቸው ይፈልጋል። በተጓዘባቸው ስፍራዎች ሁሉ የሚቀበሉት ቀራጮችና ኃጢአተኞች ሆኑ፣እግር በእግር እየተከታተሉ ትምህርቱን የሚቃወሙትና፣ የሚያጉረመርሙበት ፈሪሳውያንና፣የህግ መምህራን ህይወታቸውን እና ልባቸውን ይነካ ነበር። ምክንያቱም እውነትን በማወቅ ሁሉ ይድኑ ዘንድ የአባቱን ፈቃድ መሆኑን ያውቅ ነበር (1 ጢሞ 2:4)። በሚያድነው የእውነት እውቀት ተድላ እና ደስታ ይሆንላችሁ ዘንድ እንመኛለን።

# ትምህርት አንድ

# እስኪሰጥ ድረስ... እንዲሁ ወዷልና።

## ዮሐንስ 3:1-21 — ኒቆዲሞስ

---

**የትምህርት አንድ ቅኝት**

**ቅኝት**

*መግቢያ*

ትምህርት 1: ዮሐንስ 3:1-21

- ከእግዚአብሔር ዘንድ ነህ
- መንፈሳዊው ዳግመኛ ልደት
- በመስቀያው ላይ ያለው እባብ
- የተሰወረው የምስራች
- ስለኒቆዲሞስ ተጨማሪ

***መግቢያ***

*ቀጥሎ ያለው የጥናት ክፍል ወደ ኢየሱስ በድብቅ ይመጣ ስለ ነበረ አንድ ሰው ይተርክልናል። ይህ ሰው ማን ይመስላችኋል? ለመሆኑ በምሽት ወደ ኢየሱስ ያመጣው የነበረው ጉዳይ ምን ነበር? እርሱ ስለምን ነበር ማወቅ የፈለገው? የኒቆዲሞስ ታሪክ በጣም ሰፊና ብዙ አይደለም ነገር ግን ታላቅ የሆነውን የአብን መለኮታዊ ፍቅር በግሩም ሁኔታ የሚነግረን ድንቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው። ዩሐንስ 3፡16 እና 17 እግዚአብሔር አምነን እንቀበለው ዘንድ ያዘጋጀልንን ታላቅ የማዳን እውነት በምስጢር ይነግረናል። ኢየሱስ "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የተጠቀመበትን መንገድ ልብ በሉ።*

*ኢየሱስ ድንቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ነገር ለመግለፅ የተጠቀመባቸውን ምሳሌዎች ልብ በሉ። በእነዚያ ምሳሌዎች መሰረት አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት የሚችለው እንዴት ነው? ዳግም በመወለድ? ከመንፈስ በመወለድ? ይህ ነገር ለመረዳት አስቸጋሪ ቢሆንም ኢየሱስ ለዚህ ፈሪሳዊ በምድረበዳ ስለተሰቀለው እባብ የተናገረውን ነገር ይህ ፈሪሳዊ ተረድቶታል። እነዚህ ሁለት ሰዎች የተነጋገሩትን ንግግር በጥንቃቄ ተከታተሏቸው። ሰውየው ጥያቄ ነበረው። እንበል እና እናንተ ሁለቱ እየተወያዩ በነበሩበት ክፍል ውስጥ ተገኝታችሁ ቢሆን ምን አይነት ጥያቄ ትጠይቁ ነበር ? "ነገር ግን" የሚለው ቃል ከቁጥር 16-17 ባለው ክፍል ሁለት ጊዜ ያህል እንደተጠቀሰ ልብ በሉ። እግዚአብሔር ዓለም ሁሉ እንዲያውቀው የፈለገውን በተለይም እኛ በግላችን እንድናውቀው የሚገባንን ነገር በግሩም ሁኔታ ገልፆታል።*

**ትምህርት I**
***ምዕራፍ 1***

***መግቢያ***

የኒቆዲሞስ ታሪክ ረጅም አይደለም ። ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነና በዙሪያው ተሰብስቦ ለነበረው ህዝብ ሲያስተምር የነበረውን ትምህርት ማለትም “የእግዚአብሔርን መንግስት” እንዴት ማግኘት እንደሚችል ለመጠየቅ አንድ ሌሊት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ ስለነበረ አንድ ሰው የሚናገር አጭር ታሪክ ነው። ኒቆዲሞስ የጌታ ደቀመዝሙር የመሆኑ ነገር የሚያጠራጥር ሰው ነው። በሃይማኖታዊ ስልጣናቸው ምክንያት ለእስራኤል ሕዝብ ችግር ከሆኑት ከፈሪሳውያን ወገን ነበር። ኢየሱስም አብዛኛውን ጊዜ የእነዚህን ሰዎች ትምህርት ከሰው እንጂ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ በመናገር ትህርታቸው በግለፅ ይቃወም ነበር።

ይህን ታሪክ ስታጠኑ ልክ ኢየሱስ እና ኒቆዲሞስ ይነጋገሩበት በነበረው ክፍል ውስጥ አብራችሁ እንዳላችሁ አስቡ። ሰአቱ እኩለ ሌሊት ነው፤ ኒቆዲሞስም ኢየሱስን ጥያቄ ይጠይቀው ነበር፤ እርሱም ይመልስለት ነበር። እስቲ ለአንድ አፍታ አስቡ እናንተስ በዚያ ሁኔታ ውስጥ አብራችሁ ብትሆኑ ኖሮ ኢየሱስን ምን አይነት ጥያቄ ትጠይቁት ነበር? ይህንን ንግግር በምትሰሙበት ወቅት ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የሚመልስለት መልስ ለሁላችንም መልስ እንደሆነ እወቁ።

**የቤት ስራ**: ዩሐንስ 3:1-17 አንብቡ።

- ስለዚህ ሰው የተነገረን ምንድነው?
- ለምን ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው? ምን ነበር ማወቅ የፈለገው?
- ኢየሱስ ምን አስተማረው?

***ትምህርት***

ኒቆዲሞስ ከኢየሱስ ጋር ያደረገውን ንግግር መረዳት ያስችለን ዘንድ ፈሪሳውያን ስለሚባሉት ወገኖች ጥቂት ነገር ማወቅ ይኖርብናል። ፈሪሳውያን በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ የከበሬታ ስፍራ ያላቸው ክፍሎች ናቸው። ለህግ ካላቸው ጠንካራ ታዛዥነት እና ታማኝነት በተጨማሪም ህግን በማስተማር ያላቸው ብቃት በአይሁድ ዘንድ ዕውቅና ያላቸው ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ በአደባባይ በሚያስተምርበት ወቅት የእነዚህን ሰዎች ግብዝነታቸውን፣ታማኝ አለመሆናቸው፣እንደዚሁም ጠማማ የሆነውን መንገዳቸውን በሚነቅፍበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ይፈጠሩ ነበር (ማቴዎስ 23)። ፈሪሳውያን ከሰዎች አድናቆትና ፣አክብሮት ስለሚፈልጉ ለእነርሱ በጣም አስፈላጊ የሆነው ነገር ለታይታ የሆነው ነገር ብቻ ነበር። ኢየሱስም ማንም ሳይነግረው በሰዎች ልብ ያለውን በማወቁ ምክንያት ፈሪሳውያን

ምንም እንኳን በውጪያዊ ማንነታቸው እውነተኞች ለመምሰል ቢጥሩም ልባቸው ከእግዚአብሔር እጅግ የራቀ እንደሆነ ያውቅ ነበር (ማቴዎስ 15:8)።

**መልመጃ**:

1. ቁጥር 1: ኒቆዲሞስ ______________________________ነበረ። የአይሁድ ሃይማኖታዊ መሪ ነበረ። የአይሁድ______________ ነበረ።
2. ወደ ኢየሱስ የሚመጣው በምን ሰአት ነበር (ቁጥር 2)? ______________________________
3. ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ምን በሚል መጠሪያ ነበር የተጠቀመው? ______________________
4. ስለ ኢየሱስ ያውቅ የነበረው ምን ነበር? ________________________________________

   ________________________________________________________________________

## ትምህርት

ኒቆዲሞስ ኢየሱስን "መምህር" በማለት ነበር የጠራው። መምህራን ወይንም ረቢዎች በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ሰዎች ነበሩ። አይሁዳውያን ወንዶች ልጆች የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማለትም የህግ መፃህፍትን ፣ እንደዚሁም "ታልሙድ" የሚባለውን የአይሁድን የህግ እና የስርአት መጽሐፍ ትምህርት ቤት (የሺቫ) በመሄድ ይማሩ ነበር። ረቢዎች የሙሴን ሕግ እና ነቢያትን መጻሕፍት የመተርጎም ስልጣን ያላቸው ሰዎች ናቸው። በ"የሺቫ" የሚማሩ ተማሪዎች የአስተማሪያቸው ደቀመዛሙር ሆነው ለመመረጥ በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል። ኒቆዲሞስ ኢየሱስን "መምህር" እንደሆነ እና ተከታዮቹን የሚመርጥ እና የሚያስተምር ይህንንም ለማድረግ ስልጣን የተሰጠው እንደሆነ ተገንዝቧል።

**መልመጃ**:

1. ኒቆዲሞስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መምህር እንደነበረ እውቅና ሰጥቷል (ቁጥር 2)። ለምን እንደዚያ ሊያስብ ቻለ? ________________________________
2. ኢየሱስ ካደረጋቸው ድንቆች እና ተአምራቶች መካከል ጥቂቶቹ ምን ምን ናቸው ? *"አዳኛችን የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ"* የሚለውን የጥናት ክፍል በድጋሚ ከልሱት፡

   ሀ. ማቴዎስ 14:13-21 ______________________________________________

   ለ. ማርቆስ 1:40-45 ______________________________________________

   ሐ. ሉቃስ 8:22-25 ______________________________________________

   መ. ዩሐንስ 2:1-9______________________________________________

   ሠ. ዩሐንስ 11:38-44 ______________________________________________
3. በዩሐንስ 2:11 ላይ ኢየሱስ ስላደረጋቸው ድንቅ እና ተዓምራቶች የተነገረን ምንድን ነው?

   ሀ. እነዚህ ተዓምራቶች ምንን ይገልፁልናል? ______________________________

ለ. ድንቅ እና ተዓምራቶቹ በሰዎች ላይ ያመጡት ተፅእኖ ምን ነበር ? በተጨማሪም ዩሐንስ 2:23 ___________________________________________________

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምራቸውን ትምህርቶች እና የሚያደርጋቸውን ተአምራቶች በመመልከት ኒቆዲሞስ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ የመጣ እና እግዚአብሔር ደግሞ ከእርሱ ጋር እንደሆነ መደምደም አስችሎት ነበር (ቁጥር 2)፡፡

4. በዚህ ስፍራ ላይ ዋና ተናጋሪ የነበረው ኢየሱስ ነበር፡፡ እንዲህ አለ "እውነት እውነት እልሃለሁ፡፡" ኢየሱስ እውነትን የሚያስተምር መምህር ነበር፡፡ የሚናገራቸው ቃሎች እውነት ናቸው፡፡ ሌሎቹ አስተማሪዎች ህጉን በራሳቸው መንገድ እና ልምምድ መሰረት ነበር የሚተረጉሙት፡፡ በተቃራኒው ኢየሱስ ግን እውነትን በመግለጥ ያስተምር ነበር፡፡ በቁጥር 3 መሰረት ስለአንድ ተዓምራት እየተናገረ ኒቆዲሞስን ያስተምረው ነበር ይህ ድንቅ እና ተዓምራት ምን ነበር ? ___________________________________________________

<u>*ምዕራፍ 2*</u>

***ትምህርት***

በቁጥር 3 ላይ ያሉት የኢየሱስ ቃላት ጥያቄን የሚያጭሩ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት ምንድነው? አንድ ሰው የእግዚአብሔር መንግስት አካል መሆን የሚችለው በምን መንገድ ነው? ዳግም መወለድ ማለትስ ምን ማለት ነው? ኢየሱስ የኒቆዲሞስን ልብ ሊያረካና፣ እምነቱንም ስለ እርሱ አስቀድሞ በነበረው መረዳት ላይ ሊመሰርት ፈልጓል፡፡ ስለዚህም ኒቆዲሞስ ኢየሱስ ነው ብሎ ባመነበት እውነት ላይ ማነፁን ቀጠለ፡፡

የእግዚአብሔር መንግስት ማለት "የእግዚአብሔር በሰው ልብ እና ህይወት ላይ ማስተዳደር እና መግዛት" ማለት ነው፡፡ ኢየሱስም ኒቆዲሞስን ስለ እግዚአብሔር መንግስት እንዲያውቅና እንዲረዳ እግዚአብሔርንም በህይወቱና በልቡ ላይ እንዲያነግስ የእግዚአብሔር መንግስትም አካል እንዲሆን ፈልጓል፡፡ ኢየሱስም ለኒቆዲሞስ የእግዚአብሔር መንግስት በህይወቱ ላይ እንዲገዛ በኒቆዲሞስ ህይወት ውስጥ አንድ ተዓምራዊ ነገር ሊካሄድ እንደሚገባ ነገረው፡፡ ያም ዳግመኛ መወለድ እንዳለበት ነበር የነገረው፡፡

***መልመጃ*** :

1. ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ አንፃር የነበረውን እይታ ሲናገር ኒቆዲሞስ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት የማይቻል ነገር እንደሆነ አድርጎ አምኖ እንደ ነበረ ተናግሯል፡፡ በቁጥር 4 ላይ ምላሹ ምን ነበር?___________________________________________________

በእርግጥ ኒቆዲሞስ ትክክል ነበር! ማንም ሰው ዳግመኛ ወደ እናቱ ማህፀን ገብቶ እንደገና መወለድ አይችልም ፡፡

2. ኢየሱስ ሌላ እውነት በማስተማር ምላሽ ሰጠ፡፡ በቁጥር 5 መሰረት ለኒቆዲሞስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? ____________________

   ኢየሱስም ትክክል ነበር! እንዴት ሁለቱም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ? ኒቆዲሞስ ያስብ የነበረው በስጋ የሚሆነውን መወለድ ነበር ፣ኢየሱስ ደግሞ የሚናገረው በመንፈስ ስለሚሆነው መወለድ ነበር፡፡ ይህንን ጉዳይ ኢየሱስ በቁጥር 6 ላይ ግልፅ አድርጎት ነበር፡፡ "ከ__________ የተወለደ __________ ነው፥ ከ__________ የተወለደ __________ ነው፡፡"

3. ቀጥላችሁ በቁጥር 9 ላይ ያለውን አንብቡ፣የኢየሱስን ትምህርት ሲሰማ ኒቆዲሞስ ምን ነበር ያሰበው? ____________________

**ትምህርት**

አይሁድ የአብርሃም ዘር በመሆናቸው ምክንያት የተለዩ እና የተመረጡ ሕዝቦች እንደሆኑ ያምናሉ፡፡ ከአብርሃም በሥጋ መወለዳቸው እንደዚሁም ለህጉ እና ለቃልኪዳኑ ያላቸው ታማኝነት ብቻ ሙሉ እንደሚያደርጋቸው ያምናሉ፡፡ ኒቆዲሞስም የአብርሃም ዘር በመሆኑ እንደዚሁም የተስፋው ልጅ ዘር መሆኑ ብቻ በቂ እንደሆነ ያምናል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ አይሁዳዊ ትምህርቱን እና ልምምዱን ቆም ብሎ እንዲያይ የሚያደርገውን አዲስ አቅጣጫ አሳየው፡፡

ይህ ኢየሱስ እየተናገረለት ያለው ዳግመኛ የመወለድ ጉዳይ የመንፈስን ዳግመኛ መወለድን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሰው ከመንፈስና ከውሃ ካልተወለደ በስተቀር በሥጋ የአብርሃም ዘር መሆኑ ምንም ፋይዳ የሌለው ነገር እንደሆነ ነበር ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የነገረው፡፡ ታዲያ እንዴት ነው አንድ ሰው ከመንፈስ መወለድ የመሚችለው? ንግግራቸው ይቀጥላል…

**መልመጃ**:

1. በቁጥር 8 ላይ ኢየሱስ ምን አይነት ምስል ተጠቅሞ ነበር? ____________________
2. አንድ ሰው ንፋስን ከየት ተነስቶ ወዴት እንደሚሄድ ማወቅ ይችላልን? __________ ንፋስንስ ማየት ይቻላል ? __________ ንፋስ ሲነፍስ ድምፁን ከመስማት ውጪ ከየት ተነስቶ ወዴት እንደሚሄድ ማወቅ ይቻላል? __________ ንፋስ ረቂቅ ቢሆንም እንኳን መኖሩን ታውቁታላችሁ፡፡ ኢየሱስም በቁጥር 8 ላይ እንደዚሁ ነው ያለው (ቁጥር 8)፡፡
3. በጣም የተገረመው ኒቆዲሞስ በመጨረሻ በቁጥር 9 ላይ ጥያቄውን እንደዚህ በሚል ቃል ነበር የገለፀው:____________________
4. በቁጥር 10 ላይ ኢየሱስ ምን ነበር የጠየቀው? ____________________

በቁጥር 11 መሰረት ኢየሱስ ፈሪሳዊውን ኒቆዲሞስን እና የህግ መምህራንን የማያዩትን ነፋስ መኖር አምነው ተቀብለው ሌሎች በህይወታቸው የተለማመዱትን አዲሱን የመንፈስ ሚስጥራዊ አሰራር ለመቀበል በመቸገራቸው ምክንያት ክፉኛ ነቅፏቸዋል፡፡ ምንም ነገር ሊያልፈው አልፈለገም ነበር፡፡ ንፋስን ሳያዩ የመቀበል አቅም ያላቸው ሲሆን ሚስጥራዊ የሆነውን የመንፈስ አሰራር ግን የተለማመዱት ሰዎች ቢመሰክሩላቸው እንኳን አይቀበሉትም ወይንም መቀበል አይችሉም፡፡

5. ከቁጥር 11-15 ባለው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ የሚከተለውን ቃል በታላቅ ስልጣን ተናገረ፡፡
   ሀ. ቁጥር 11: “እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ____________________ እንናገራለን ________________ እንመሰክራለን፥ ምስክራችንንም ________________፡፡
   ለ. ቁጥር 12: “____________________ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ __________________፥ ስለ ________________ብነግራችሁ እንዴት ____________________?”
   ሐ. ቁጥር 13: “ከ___________________ ከወረደ በቀር ወደ ________________የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም ___________________ የሚኖረው _______________ነው፡፡”
   መ. ቁጥር 14: “_________________ በምድረ በዳ _________________ እንደ ሰቀለ እንዲሁ የ___________________ይሰቀል ይገባዋል፡፡”
   ሠ. ቁጥር 15: “በ__________ሁሉ____________እንዲኖረው እንጂ ______________”

<u>**ምዕራፍ 3**</u>

**ትምህርት**

በዚህ በክፍል 3 ጥናታችን ከኒቆዲሞስ ታሪክ በመውጣት ወደ ሌላ አቅጣጫ እንንዛለን፡፡ በዩሐንስ 3፡14-15 ባለው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ሲያስተምር ከብሉይ ኪዳን የጠቀሰው ታሪክ ነበረ፡፡ ይህ ታሪክ የሚናገረው እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ጥቂት ሲቀራቸው ከመዘጋጀታቸው ቀደም ብሎ ባለው ወቅት በምድረበዳው ውስጥ የተከናወነ ታሪክ ነው፡፡ ይህ ታሪክ ተዘግቦ የሚገኘውም በኦሪት ዘኍልቁ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡

**የቤት ስራ**: ኦሪት ዘኍልቁ 21:4-9 አንብቡ

- እስራኤላውያን የት ነበሩ?
- ችግሩ ምን ነበር?
- የእግዚአብሔር ፍርድ ምን ነበር?
- የእግዚአብሔር መድኃኒትስ ምን ነበር?

**ትምህርት** (የቀጠለ): በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ጀርባ ጥንታዊውን ሁኔታ የሚያሳይ ካርታ ካለ አሁን እርሱን ተመልከቱ፡፡ ሕዝቡ በኤዶም ምድር ዞሮ ለመሄድ ከሆር ተራራ ተነስተው (ቃዴስ በርኔ አቅራቢያ የሚገኝ ተራራ ነው) ወደ ቀይ ባህር ነበር የተጓዙት፡፡ የኤዶም ነዋሪዎች የያዕቆብ መንትያ ወንድም የሆነው የኤሳው ዘሮች ናቸው፡፡ በኦሪት ዘኁልቁ 20፡21 መሰረት ኤዶማውያን እስራኤላውያን ወደ ከነአን ማለትም (ወደ ተስፋይቱ ምድር) ሲጓዙ ድንበራቸውን አቋርጠው በምድራቸው እንዳያልፉ ከልክለዋቸው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት እስራኤላውያን በሌላ መንገድ ለመሄድ ተገደዱ፡፡ ስለዚህ ወደ ኢያሪኮ ለመሄድ ኤዶምን እና ሞአብን ትተው የበረሃውን መንገድ ተከትለው መጓዝ ግድ አላቸው፡፡

**መልመጃ**

1. ቁጥር 4 ስለእነዚህ ሰዎች ምን ይነግረናል? ________________________________________
2. ___________________ እና ________________________ በመቃወም ተናገሩ (ቁጥር 5)
3. ጉርምርምታቸው ወይንም ተቃውሟቸው ምን ነበር(ቁጥር 5)?_________________________

   ____________________________________________________________________

4. ሙሴን እና የእግዚአብሔር ባሪያዎችን ክፉ በመናገራቸው ምክንያት የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 6)? __________________________________________________________
5. በቁጥር 6 መሰረት የእግዚአብሔር የፍርድ ውጤት በእስራኤል ላይ ምን ነበር? ____________

   ____________________________________________________________________

6. ቁጥር 7 ላይ ሕዝቡ ወደ ሙሴ ቀረቡ፡፡

   ሀ. ምን ብለው ነበር የተናዘዙት ? ____________________________________________

   ለ. ሙሴስ ምን አደረገ? ______________________________________________________

7. በቁጥር 8 ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው መመሪያ ምን ነበር? ______________________

   ____________________________________________________________________

   እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል ____________________ ሁሉ ____________________

   ____________________አለው፡፡ ቁጥር 9 እግዚአብሔር እንደተናገረው እንደዚያው እንደሆነ ይነግረናል!

   ***ማስታወሻ***: በመስቀያው ላይ የነበረው የነሐስ እባብ ወይንም "ነሑሽታን" በንጉሥ ሕዝቅያስ የንግሥና እና የተሃድሶ ዘመን ተሰባብሮ እንዲጠፋ ተደርጓል ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ እርሱን ማምለክ በመጀመሩ ነበር (መፅሐፈ ነገሥት ካልዕ 18:4) ፡፡

**አስተያየት**

መርዘኞቹ እባቦች ከሕዝቡ መካከል ተወግደዋል፡፡ አነዳደፋቸው ገዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡን በመርዘኞቹ እባቦቹ ተነድፈው ከማለቅ አተረፋቸው፡፡ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ከሰሩት በደል እና ኃጢአት ፣ከማጉረምረማቸው፣በተቃራኒ እግዚአብሔር የፈውሳቸውን መንገድ ቀላል

አደረገላቸው፡፡ በመስቀያው ላይ የተሰቀለውን የነኃስ እባብ በመመልከት ፈውስ ወይንም በህይወት መኖር እንዲችሉ እግዚአብሔር ነገሩን ቀላል አደረገላቸው፡፡ በመካከላቸው በተሰቀለው የነኃስ እባብ አማካኝነት እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ሊያጠፋቸው የነበረው አምላክ ምህረት እና ህይወት አደረገላቸው፡፡

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**

ይህ ታሪክ እኛም በህይወታችን ልንተገብረው የሚገባንን ትምህርት ያስተምረናል፡፡ እኛን ሊያጠፋን በህይወታችን የመጣ ጥፋት ምንድነው?____________________________________________

________________________________________________________________

ዓለም፣ሥጋ፣ሰይጣን በህይወታችን ውስጥ ያለማቋረጥ ጦርነት እንዲካሄድ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ በዚህ ውጊያም በኃጢአት መርዝ እንድንሞት የሚያደርጉን ጠላቶቻችን ናቸው፡፡ በኃጢአት የመፀነሳችን እውነት በዘረ መልአችን (ዲ፡፡ኤን፡፡ኤ) ውስጥ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር ያሰበውን ፍፁምነት የሚቃረን ማንነት ነው፡፡ ልክ እንደ ኒቆዲሞስ ሁሉ፣ ኢየሱስ እኛም ከመንፈስ እና ከውሃ ዳግመኛ እንድንወለድ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ አንድ ሰው የእግዚአብሔር መንግስት አካል ሊሆን የሚችለው ወይንም የዘላለምን ህይወት የሚያገኘው ከውሃ እና ከመንፈስ ሲወለድ ብቻ እንደሆነ ነግሮታል፡፡

ልክ በምድረበዳው በእባብ ለተነደፉት ሰዎች እንዲፈወሱ የነሃሱ እባብ በመካከላቸው ከፍ ተደርጎ እንደተሰቀለ በእርሱ "የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት" ያገኝ ዘንድ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ እንደሚገባ ኒቆዲሞስ መረዳት ይሆንለት ዘንድ ኢየሱስ ፈልጓል፡፡ ወደ እባቡ ትኩር ብሎ ማየቱ እምነትን የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ እስራኤላውያን ትኩር ብለው የተሰቀለውን እባብ ሲመለከቱ ይድኑ ነበር፡፡ ድነትን ለማግኘት ወደ ኢየሱስ በእምነት መመልከት ነው፣ ወይንም የሚያድን እምነት ድርጊት ነው፣በዚህም እምነት የዘላለምን ህይወት እንቀበላለን፡፡ ስለዚህ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይገቡ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል ማለት ነው፡፡ በእምነት ወደ ክርስቶስ ሞት የሚመለከቱ ሁሉ የዘላለምን ህይወት ይቀበላሉ ማለት ነው !

ህይወት ባላቸው ነገሮች ሁሉ ውስጥ ውሃ እንዳለ ሁሉ፣ እንደ ቃሉ በውሃ በመጠመቅ የህይወት ውሃ በሆነው መንፈስ በመረስረስ ወደ አዲሱ ህይወት እንወለዳለን ! በዩሐንስ 7፡37-38 ባለው ክፍል ውስጥ ምንድነው የተነገረን? "ማንም______________ ቢኖር ወደ ________________

________________ና ________________________ ፡፡ _______________________እንዳለ፥

________________________ወንዝ ________________________ብሎ ጮኸ፡፡

## ምዕራፍ 4

### ትምህርት

ታላቅ የሆነው የእግዚአብሔር የምስራች ቀጥሎ በምንመለከተው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተሰውሮ እናገኘዋለን። ይህንን ክፍል እንዲሁ በዋዛ የምናልፈው አይደለም። ዩሐንስ 3፡16 አጠቃሎ እንደዚህ ይገልፅልናል። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" የሚከተለው ክፍል ቁጥር 16 ይህንኑ ያብራራልናል። ቁጥር 17 ደግሞ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን የላከልን በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን በእርሱ ማለትም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን እንደሆነ ይነግረናል።

**ማሰላሰል**

እነዚህን ቃላቶች በደብተራችሁ ላይ መጻፋችሁን እንደዚሁም በቃላት መመዝገቢያችሁ ውስጥ እንደ ጨመራችኋቸው እርግጠኛ መሆን ይኖርባችኋል። በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ የተገለፀው የእግዚአብሔር ቃልኪዳን በመጀመሪያ በዘፍጥረት 3፡15 ለአዳም እና ለሔዋን ፤በመቀጠልም በዘፍጥረት 12፡3 ደግሞ ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው ቃልኪዳን በዚህ የአዲስ ኪዳን ክፍል ውስጥ እውን ሆኗል። ኢየሱስ እነዚህን ቃላቶች የተናገረው ለራሱ ነው። እርሱ ለእስራኤል ተስፋ የተገባው መሲህ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ተናግሯል። እርሱ የእግዚአብሔር አብ ፍቅር መገለጫ ነው። ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ እያንዳንዱን ሰው ወይንም የሰውን ዘር በሙሉ እንዲያድን በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሰጠው ተስፋ ወይንም መሲህ እንደሆነ በማመን ከጥፋት ይድኑ ዘንድ ወይንም የዘላለምን ህይወት ያገኙ ዘንድ እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ወዷል።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ የዘላለም ህይወት የምናገኝበትን ታላቅ ስጦታ እንዳቀረበልን ከማመን ይልቅ፣ በሰማይ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በእኛ ላይ ለመፍረድ የተዘጋጀ አምላክ አድርገን በማመን እንሳሳታለን። ቁጥር 17 ይህንን እውነት ይነግረናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው እኛን ለማዳን እንጂ በእኛ ለመፍረድ አለመሆኑን ማመን ይኖርብናል። ኢየሱስ በኃጢአቶቻችን እና በበደሎቻችን ምክንያት ከዚህ በኋላ እንደማንቀጣ የእኛን ቅጣት ሊወስድልን፣ የበደላችንን ዋጋ ሊከፍልልን እንደመጣ ነግሮናል። ስለዚህ አዲስ ህይወት የተሰጠን፣ ከፍርሃት ነፃ የሆንን፣ ከጥፋተኝነት ስሜት እና ኃፍረት ነፃ የወጣን ከፍርድና ከቅጣት የዳንን እንጂ የተፈረደብን ሰዎች አይደለንም። ከዚህ በኋላ የሚያሳስበን ኃጢአታችን ሳይሆን አለማመናችን ነው። "በእርሱ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው...።" በማርቆስ 16፡16 እንደዚህ የሚል ቃል ተነግሮናል "በአንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ያላመነ ግን ተፈርዶበታል"... ታዲያ ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር የሚጠይቀን አንድ ጥያቄ ነው "ታምናላችሁ?" ይለናል።

*"የእግዚአብሔር ልጅ አዳኛችን"* |በሚለው የጥናት ክፍል ታስታውሱ እንደሆነ በዩሐንስ 11:25-26 ኢየሱስ ሞቶ ለነበረው የአልአዛር እህቶች ያቀረበላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ ነበር። "ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ

ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት።” ታዲያ በቁጥር 27 ላይ ማርታ ምን በማለት መለሰችለት?________________________________

በሮሜ 8፡1-2 መሰረት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከፍርድ፣ እና ከሞት መዳን እና ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ለዘላለም መኖር ምን ማለት እንደሆነ በደብተራችሁ ላይ ፃፉት።

**ማጠቃለያ**

በዚህ የጥናት ክፍል ኒቆዲሞስ ከሚባል ሰው ጋር ተዋውቀናል። ፈሪሳዊ እና የአይሁድ ጉባኤዎች መሪና መምህር እንደነበረ ተምረናል። ስለ ኢየሱስ የማወቅ ወይንም የመማር ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው። ኢየሱስም ለኒቆዲሞስ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት የሚችለው በራሱ መንገድ እና ጥረት ሳይሆን ከውሃ እና ከመንፈስ ዳግመኛ በመወለድ እንደሆነ አብራራለት። ከመንፈስ መወለድ እንደሆነም ነገረው። በተጨማሪም በብሉይ ኪዳን ያለውን የእስራኤል ሕዝብ በምድረበዳ በእባብ በተነደፉ ወቅት ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የነሃስ እባብ ሰርቶ በሕዝቡ መካከል በመስቀል በእባቡ የተነደፉት ሰዎች የተሰቀለውን የነሃስ እባብ አትኩረው ሲመለከቱ ይፈወሱበት የነበረውን ታሪክ ጠቅሶ አብራራለት። በምድረበዳ የነበሩት ሰዎች ወደ ተሰቀለው የነሃስ እባብ በመመልከት ስጋዊ ሞትን እንደማይሞቱ በማመናቸው ምክንያት ከሞት ድነዋል ፣ልክ እንደዚሁ ሰዎች ወደ ኢየሱስ በማየት ወይንም በኢየሱስ በማመን ከመንፈሳዊው ሞት በመዳን የዘላለምን ህይወት ያገኛሉ።

**ምዕራፍ 5**

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**

ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የተናገራቸውን ቃላቶች በህይወታችሁ ለመተግበር ጥቂት ጊዜ ውሰዱ። ልክ እኔ እና እናንተ ኢየሱስ እና ኒቆዲሞስ ሲነጋገሩ በነበሩበት ክፍል ውስጥ አብረናቸው እንደነበርን እናስብ።

1. በዚያ ክፍል ውስጥ የነበራችሁት እናንተ እና ኢየሱስ ብቻ ብትሆኑ የነበራችሁት ኢየሱስ ከተናገራቸው አንድ ወይንም ሁለት ንግግሮች ውስጥ በየትኞቹ ልባችሁ ይነካ ነበር ?
   ሀ.________________________________
   ለ.________________________________
2. ኢየሱስ ከተናገራቸው ንግግሮች ውስጥ የትኞቹ ሳይመቿችሁ ይቀሩ ወይንም ያውኳች ነበር?
   ________________________________
3. ኢየሱስ ስለእርሱ እንደዚሁም ስለሰማያዊው አባት እንድታውቁት የሚፈልገው ዋና እና ጠቃሚ እውነት ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? ________________________________
   ________________________________

**ትግበራ**

1. ይህ ትምህርት ለሚያምኑ ሁሉ የድነትን የምስራች ያቀርባል፡፡ የምስራቹን ለምናምን ለእኛ የእግዚአብሔር ግብዣ ምንድነው ?__________________________________________
   ______________________________________________________________
2. ከዚያስ ለዓለም የምንነግረው መልእክት ምን ሊሆን ይችላል ? _______________________
   __________________________________________________________________
3. ልክ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ እንደነገረው ያንን መልእክት ሲነገራቸው የሚያምኑ በሙሉ እንደሚድኑ ሲናገር ይህንን ድንቅ መልእክት እንድትነግሯቸው ወደ ልባችሁ የሚመጡት የመጀመሪያዎች ሰዎች እነማን ሊሆኑ ይችላሉ?
   ሀ. __________________________________
   ለ. __________________________________
   ሐ. __________________________________

**ስለኒቆዲሞስ ተጨማሪ ነገር**: ታዲያ ኒቆዲሞስ እንዴት ሆነ? አምኖ ይሆን? እነዚያን ለኢየሱስ አገልግሎት ፈተና የነበሩትና ብዙ ጊዜ ኢየሱስን መግደል ይፈልጉ የነበሩትን የፈሪሳውያን ቡድን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለይቷቸው ይሆን? ኒቆዲሞስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌሎች ጥቂት ስፍራዎች ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ እስቲ እነዚህ ክፍሎች እንመልከታቸው…፡፡፡፡

1. ዩሐንስ 7:45-52
   ሀ. ሁኔታው ምን ይመስል ነበር? ______________________________________
   ለ. የኒቆዲሞስ ጥያቄ ምን ነበር ? _____________________________________
   __________________________________________________________
   ሐ. የክሱ ምክንያት ምንድነው? _________________________________________
   መ. እናንተስ እንደ ኒቆዲሞስ የኢየሱስ ተከታዮች ትሆናላችሁ? እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ መሲህ እና፣ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ በማመናችሁ ምክንያት የሚመጣባችሁ መከራ እና ጫና ለመጋፈጥ ዝግጁ ናችሁ? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለፁ: _________________________________________________
   __________________________________________________________
2. ዩሐንስ 19:38-42
   ሀ. ሁኔታው ምን ይመስል ነበር? ______________________________________
   ለ. ኒቆዲሞስ ማን ነበረ? _____________________________________
   ሐ. ኒቆዲሞስ ምን ነበር ያመጣው? ____________________________________

መ. የአርማቴው ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ ሁለቱም የኢየሱስ ተከታዮች ነበሩ። ኒቆዲሞስ የበሰለና ስለኢየሱስ በግልጽ ለመመስከር የበቃ ሰው ይመስላችኋል? እናንተስ የበሰላችሁ እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ኢየሱስ ማን እንደሆነ መመስከር ትችላላችሁ? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ገግፁ: ______________________

______________________________________________

**ፀሎት**:

1. ከኢየሱስ ጋር ስላለኝ የግል ግንኙነት የምፀለየው? ______________________

______________________________________________

2. ጌታ በልቤ ላመጣቸው ጓደኞቼ የምፀልየው? ______________________

______________________________________________

3. የምስራቹን ለዓለም ሁሉ ለማዳረስ ለእግዚአብሔር ተልእኮ እራሴን መስጠት እችል ዘንድ እፀልያለሁ? ______________________

______________________________________________

______________________________________________

# ክፍል ሁለት

# ይህ ክርስቶስ ይሆንን?

## ዮሐንስ 4:3-42 — ሳምራዊቱ ሴት

---

**የትምህርት ሁለት ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 2: ዮሐንስ 4:3-42

- ኢየሱስ ሴቲቱን አገኛት
- የሴቲቱ ችግር
- ትምህርት: የህይወት ውሃ
- የአምልኮ ስፍራ እና ማንነት
- ታላቅ ረብሻ
- መከሩ ደርሷል
- ማወቅ እና ማመን
- የወንጌል ምስጢር

***መግቢያ***

ኢየሱስ የሚያደርገውን ሁሉ ያውቅ ነበር፡፡ በሰማሪያ ማለፍ ነበረበት፡፡ እናም በጉዞው ደክሞ በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ አረፈ፡፡ ታሪኩ በዚያ ስፍራ ላይ ይጀምራል፡፡ አሁን ትዕይንቱ ሊጀመር መድረኩ ተዘጋጅቷል፡፡ በጠራራው ፀሀይ ውሃ ለመቅዳት ወደዚያ ጉድጓድ የምትመጣውን ሴት ሊያገኛት ተዘጋጅቷል፡፡ ኢየሱስ እርሱ መሲህ መሆኑን እስክትረዳ ድረስ የልቦናዋን አይኖች ሲከፍትላት ልብ በሉ፡፡

ኢየሱስ ለደቀዛሙርቶቹ ስለደረሰው መከር ሲያስተምራቸው አድምጡ፡፡ አይኖቻቸውን ከፍተው የነጣውን አዝመራ እንዲመለከቱ ይህንንም እነርሱ ያልዘሩትን አዝመራ እንዲሰበስቡ ይነግራቸዋል፡፡

ሴቲቱ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ባትረዳም አለመረዳቷ አላስቆማትም፣ወደ መንደሯ ተመልሳ በመንደሯ ላሉት ሰዎች የሆነው ነገር አካፈለቻቸው "መጥታችሁ እዩ" የሚል ድንቅ ግብዣ አደረገችላቸው፡፡

**ትምህርት 2**

**ምዕራፍ 1**

**ትምህርት**

ቀጣዩ ታሪክ በሰማሪያ ምድር ትኖር ስለነበረች አንዲት ሴት የሚናገር ነው፡፡ አንዳንድ ስፍራዎች ላይ "በጉድጓዱ አጠገብ የነበረችው ሴት" ተብላ ከመጠቀስ ያለፈ የዚህች ሴት ስም አልተገለፀልንም፡፡ እስቲ በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ዘመን የነበረውን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ የሚያሳየውን ካርታ ላይ ሰማሪያን አመልክቱ፡፡ ይህንን ክፍል ከዚህ ቀደም አንብባችሁት ይሆናል ወይንም ደግሞ ገና አሁን እያነበባችሁት ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁዳ የምትገኘው በስተ ደቡብ ነው፡፡ ገሊላ ደግሞ በስተ ሰሜን ትገኛለች እንግዲህ ሰማሪያ የምትገኘው በእነዚህ ሁለት ስፍራዎች መካከል ነው፡፡ ሲካር ያለች ሰማሪያ መካከል ሲሆን ከገሪዛን ተራራ ጥቂት እልፍ ብላ ትገኛለች፡፡፡፡

ቀጥሎ የምንማረው ክፍል ትርጉም ያለው እንዲሆንልን በሰማርያውያን እና በአይሁዳውያን መካከል ስላለው ግንኙነት አስቀድመን መረዳት ይኖርብናል፡፡ አሶራውያን የሰሜናዊውን ግዛት የእስራኤልን ዋና ከተማ ሲቆጣጠሩ በሰማሪያ ይኖሩ የነበሩትን እስራኤላውያንን ወደ አሶር በማፍለስ እንግዶች ህዝቦች በማምጣ በሰማሪያ አሰፈሯቸው (መፅሐፈ ነገስት ካልዕ 17:24)፡፡ እነዚህ እንግዳ ህዝቦችም አማልክቶቻቸውን ወደ ምድሪቱ በማምጣት በዚያ ቀርተው ከነበሩት እስራኤላውያን ጋር ጋብቻ በመፈፀም በዚያ ምድር ይኖሩ ጀመር፡፡ ስለዚህ በሰማሪያ የሚኖረው ሕዝብ ቅይጥ ወይንም የተደባለቀ ሕዝብ ነበር ፡፡ ይህን አይነት ተግባር በይሁዳ ለሚኖሩት ንፁህ እስራኤላውያን ሃገርን እና ህዝብን እንደመክዳት ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ አይሁዳውያን በሰማሪያ ምድር ማለፍ እንኳን እንደመርከስ ስለሚቆጥሩት ወደ ገሊላ ለመሄድ ዮርዳኖስን ሁለት ጊዜ አቋርጠው ወደ ምስራቅ በመጓዝ ተመልሰው በሰሜን ወደ ገሊላ ይጓዙ ነበር፡፡

*ታዲያ ኢየሱስ ይህቺን ሳምራዊት ሴት እንዴት ሊያገኛት ቻለ ?*

**የቤት ስራ**: ዩሐንስ 4:4-26 አንብቡ

- ከቁጥር 7-15 ባለው ክፍል ውስጥ ንግግራቸው ትኩረቱን ያደረገው በምን ላይ ነበር?
- ከቁጥር 16-18 ባለው ክፍል ላይ ስላለችው ሴት ምን እንረዳለን?
- ከቁጥር 19-24 ያለው የንግግር ክፍል ትኩረቱን ያደረገው በምን ላይ ነው?
- ከቁጥር 25-26 ባለው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ለሴትዮዋ ምን ገለጠላት?

***መልመጃ***:

1. በቁጥር 3 ላይ እንደምንረዳው ኢየሱስ _________________ ትቶ እግረ መንገዱን ወደ ___________________ሄደ። ቁጥር 4 ምን ይነግረናል? _________________________
2. ኢየሱስም ወደ__________________________ከተማ መጣ ያዕቆብም ለልጁ ለዩሴፍ በገዛለት የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ በሲካር የሚገኘው ምን ነበር (ቁጥር 6) ? _______________
3. በቁጥር 6 ላይ ስለ ኢየሱስ የተነገረን ምንድነው? ________________________________
4. ስንት ሰአት ይሆን ነበር? ______________________________________________

   ***ማስታወሻ*** የአይሁዳውያን ሰአት አቆጣጠር ቀን በ6 ሰዓት ጀምሮ ከሌሊቱ በ6 ሰዓት ያበቃል።
5. ውሃ ልትቀዳ የመጣችው ማን ነበረች (ቁጥር 7)? ________________________________

   **ማስታወሻ**: በቁጥር 8 ላይ እንደተነገረን ደቀመዛሙርቱ ምግብ ለመግዛት ወደ ሲካር ሄደው ነበር። ይህ ማለት እነርሱ ምግብ መግዛት በሄዱበት ወቅት በእኩለ ቀን በውሃው ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ ነበር (ቁጥር 6)። በዚያ ከተማ የሚኖሩ ሴቶች ውሃ የሚቀዱበት ሰአት ፀሐይ ሳትወጣ በማለዳ ፣ወይንም ደግሞ ፀሐይ ስትጠልቅ አመሻሹ ላይ ነበር። ይህቺ ሴት ውሃ ልትቀዳ በወጣችበት ሰአት ማለትም እኩለ ቀን ላይ ውሃ ለመቅዳት የሚወጡ ሴቶች ከማህበራዊ ግንኙነቶች የተገለሉ ሴቶች ናቸው። ስለዚህ ይህቺም ሴት በሌሎች ከሚደርስባት ነቀፋ እና ሃፍረት ለመሸሽ ይመስላል በዚህ ሰአት ብቻዋን ወደ ውሃው ጉድጓድ የመጣችው።
6. ኢየሱስ ምን ጠየቃት? ______________________________________________
7. ይህቺም ሴት ወዲያውኑ እርሷን ሊያናግር የቻለበትን ምክንያት በመጠየቅ ፈጣን ምላሽ ሰጠችው። ምን ነበር የመለሰችለት (ቁጥር 9) ? ________________________________

   ______________________________________________________________

   በሌላ አባባል ያለችው “ አንተ እኔ ከቀዳሁት ውሃ መጠጣት አይገባህም! ስለዚህ ከእኔ ውሃ ልትጠይቀኝ አይገባህም” ነበር ያለችው።

***ትምህርት***

ይህቺ ሴት በኢየሱስ ላይ ችግር ልትፈጥርበት ነው። በአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ነገሮች ይኖራሉ ። ***የመጀመሪያው*** ምክንያት ይህቺ ሴት በአይሁድ ዘንድ ተቀባይነት ከሌላቸው ወገኖች ከሰማሪያ ነች ። ***ሁለተኛው*** ምክንያት ደግሞ በእኩለ ቀን ወደ ውሃ ጉድጓዱ የመምጣቷ ጉዳይ ይህቺ ሴት ባለችበት ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት የሌላት መሆኗን ያመለክታል። ***ሶስተኛ*** ደግሞ አንድ ክብሩን የሚጠብቅ ሰው እንደዚህ አይነት ማንነት ካላት ሴት ጋር ሲነጋገር መገኘት የለበትም። ነገር ግን ኢየሱስ እንደዚህ ካሉ ነገሮች ጋር ምንም አይነት ችግር የለበትም። ሴት መሆኗ፣ሳምራዊት መሆኗ፣እንደዚሁም በማህበረሰቧ ዘንድ ተቀባይነት የሌላት ሴት የመሆኗ ነገር

ለኢየሱስ ችግር አልፈጠረበትም። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለእርሷ እና ለምትኖርበት ማህበረሰብ ችግር የሚፈጥር ነገር ሊሆን ቢችልም ለኢየሱስ ግን ምንም አይነት ችግር አልፈጠረበትም። እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ለኢየሱስ ያን ያህል አስፈላጊ ነገሮች አልነበሩም ። ታዲያ ለኢየሱስ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ምንድናቸው? ለኢየሱስ ዋና እና አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ቀጥሎ ባለው የትምህርት ክፍል ተከታተሉ።

**ምዕራፍ 2**

***መልመጃ***

1. በቁጥር 10 ላይ ኢየሱስ በእርሷ ማንነት ዙሪያ የነበረውን ንግግር ወደ እርሱ ማንነት እና ምንነት ንግግር ቀየረው። ይህ ውሃ የሚለምናት ማን እንደሆነ ብታውቅ እርሷ ትለምነው እንደነበር እርሱም ይሰጣት እንደነበር ነገራት፡ ________________________________
2. ኢየሱስ ለእርሷ ስላዘጋጀላት መሰረታዊ ነገር ነበር የነገራት። የሴቲቱ ትልቅ ትኩረት ምን ላይ ነበር (ቁጥር 11)? ________________________________________
3. ኢየሱስ የህይወት ውሃን በመስጠት መሲህነቱን ሊገልፅላት ለእግዚአብሔር ያላትንም ጥማት ለዘላለም ሊያረካላት ይህንን ታላቅ ስጦታ አዘጋጅቶላታል። የጠቀሰችው ችግር ምን ነበር? ኤርምያስ 2:13 ተመልከቱ "________________________________________
________________________________________________________::"
4. ኢየሱስ ይህቺ ሴት በየእለቱ ከቤቷ ወጥታ ከያዕቆብ ጉድጓድ ውሃ መቅዳት ችግር እንደሆነባት አውቋል። በየእለቱ በጠራራ ፀሐይ ውሃ ልትቀዳ ስትመጣ የቀኑ ሃሩር ይህቺን ሳምራዊት ምን አይነት ኃጢአተኛ ህይወት እየኖረች እንደሆነ ያስታውሳታል። ስለዚህ ዳግም እንዳትጠማ ለዘላለም የሚያረካትን የህይወትን ውሃ ሊሰጣት ወደደ።
"ከዚህ ________________________ሁሉ ________________________፤እኔ ከምሰጠው ____________________ ሁሉ ግን ለዘላለም ____________________፥ እኔ የምሰጠው ____________________በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ ____________________ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት (ቁጥር 13-14)።"
5. በቁጥር 14 ላይ በተጨማሪ ኢየሱስ እርሱ የሚሰጠው ውሃ ______________________
____________________________________________መሆኑን ተናገረ።
6. አሁን ኢየሱስ የሴትዮዋን ትኩረት ማግኘት ቻለ። በቁጥር 15 ላይ ምን ነገረችው? "ጌታ ሆይ፥ ________________ ውኃም ________________ ወደዚህ እንዳልመጣ ________________ስጠኝ አለችው።"

**ትምህርት**

ኢየሱስ ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ ነገሮችን ለመግለፅ የተለያዩ ምሳሌዎችን ይጠቀማል፡፡ በክፍል አንድ ትምህርታችን ኒቆዲሞስን ከመንፈስ እና ከውሃ ስለመወለድ ወይንም ዳግመኛ ስለመወለድ ሲያስተምረው የመወለድንና፣ የንፋስን ምሳሌ በመጠቀም አስተምሮታል፡፡ ለሳምራዊቱም ሴት ኢየሱስ ለዘላለም ስለሚፈልቀው የዘላለም ህይወት ውሃ ምንጭ ማለትም በእርሱ በማመን የሚገኘውን የህይወት እርካታ ለማስተማር የውሃን ምሳሌ በመጠቀም አስተምሯታል፡፡

**መልመጃ**

1. እርሱ ስለሚያስፈልጋትና እርሱ ስለሚሰጣት ውሃ ተናግሮ ፈፀመ፡፡ በቁጥር 16 ላይ ምን እንድታደርግ ነገራት? ______________________________
2. የእርሷ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 17)? ______________________________
3. ከዚያም ኢየሱስ እንደዚህ አላት"______________________________፡፡"
4. በቁጥር 18 ላይ በተጨማሪ ምን አላት? ______________________________

   ______________________________

   ***ማስታወሻ፡*** ኢየሱስ ስለማንቷ ከነገረችው በላይ ስለእርሷ እንደሚያውቅ ነገራት፡፡ የኃጢአት ኑሮ እየኖረች እንዳለች ነገራት፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን ኢየሱስ ስላለችበት ሁኔታ ቢያውቅም በእርሷ ላይ ሊፈርድባት አልተነሳም ነበር፡፡ (ዩሐንስ 3:17)

5. ሴቲቱ ኢየሱስ______________________ ለመሆኑ እውቅና ሰጠች (ቁጥር 19) ነገር ግን ወዲያውኑ ርእስ ተቀየረ (ቁጥር 20)፡፡ ስለትክክለኛው የአምልኮ ስፍራ ልትናገር ፈለገች፡፡ አባቶቻችን በዚህ______________________ ሰገዱ (ገሪዛን ተራራ)፡፡ አይሁድ ትክክለኛው የአምልኮ ስፍራ______________________ ነው ብለው ይናገራሉ፡፡
6. ኢየሱስ ዋናው ጉዳይ የአምልኮ ስፍራ እንዳልሆነ በቁጥር 22 ላይ እንደዚህ በማለት ተናገረ "እናንተስ ለማታውቁት ______________________፤ እኛ ______________________ነውና ______________________ እንሰግዳለን፡፡" ኢየሱስ ዋናው ነገር የማምለኪያው ስፍራ ሳይሆን የሚመለከው አምላክ እንደሆነ እንድትረዳለት ነበር የፈለገው፡፡ እናም እግዚአብሔር የሚመለከው በ ______________ እና በ ______________ እንደሆነ እንድትረዳ ፈልጓል (ቁጥር 23)፡፡ አምልኮ የልብ ጉዳይ ነው፡፡ የትክክል እና የስህተት ጉዳይ አይደለም ወይንም የአድርግ እና የአታድርግ ጉዳይ አይደለም፡፡ እውነተኛ አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር የፍቅር ግንኙነት ማድረግ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር የፍቅር ግንኙነት ያላቸው በልባቸው ያመልኩታል፣አባታቸውን በእውነት እና በመንፈስ ያመልኩታል (ቁጥር 24)፡፡
7. በቁጥር 25 መሰረት ይህቺ ሴት መሲህ እንደሚመጣ ታውቅ ነበር፡፡ እርሱ ሲመጣ ሁሉንም ነገር እንደሚገልጥ ታምናለች፡፡ ይህ ነበር ኢየሱስ ማንነቱን የገለጠበት ወሳኝ ሰዓት፡፡ በቁጥር 18 ላይ ስለእርሷ የሚያውቀውን በሙሉ ምንም ሳያስቀር ነገራት በመቀጠልም ማንነቱን እንደዚሁ

ምንም ሳያስቀር ነገራት፡፡ እርሷና እስራኤል በሞላው የሚጠብቀው መሲህ አሁን ከእርሷ ጋር እንደዚህ በማለት እየተነጋገረ ነው፡ "________________________________ (ቁጥር 26)፡፡"

**<u>ምዕራፍ 3</u>**

**ገለፃ**

እስቲ ለጥቂት ደቂቃዎች ትምህርታችንን ገታ አድርገን ከኢየሱስ የተማርነው ነገር እንነጋገር፡፡

1. "በሰማሪያ ሊያልፍ ግድ ሆነበት" የሚለውን በቁጥር 4 ላይ ያለውን ክፍል ተመልሰን ብናየው መልካም ነው፡፡ ልክ ለሳምራውያን ካላቸው ጥላቻ እና ንቀት የተነሳ ኢየሱስም እንደሌሎቹ አይሁዶች ሰማሪያን ሳይረግጥ በሌላ መንገድ ዞሮ መሄድ ይችል ነበር፡፡ ታዲያ ይህ ክፍል እንዴት "በሰማሪያ እንዲያልፍ ግድ ሆነበት" በማለት ሊናገር ቻለ ? በሰማሪያ እንዲያልፍ ግድ የሆነበት ምክንያት የዚህች የሳምራዊት ሴት ጉዳይ ነበር፡፡ ከኢየሱስ ምን እንማራለን?

   __________________________________________________________________

2. የፅድቅ መለኪያ መስፈርት የሚመስለውን ኒቆዲሞስን እና ይህቺን ምንም መልካም ነገር የሌላትን ሳምራዊት ሴት ማወዳደር የማይታሰብ ነገር ነው፡፡ ይህቺ ሰማሪያዊት ሴት ናት፣ በዚያ ላይ ሳምራዊት፣በዚያ ላይ ደግሞ ኃጢአተኛ ነበረች፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ሁለቱንም ሰዎች ያስተናገደበት መንገድ ተመሳሳይ ነበር፡፡ ፈሪሳዊውን አክብሮ ሳምራዊቷን አልፈረደባትም፡፡ የፆታ ጉዳይ ወይንም የአኗኗራችን ሁኔታ ለኢየሱስ ምኑም አልነበረም፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው በእርሱ በኩል በእውነት እና በመንፈስ እግዚአብሔርን ያመልኩ እና ከእርሱም ጋር ህብረት ያደርጉ ዘንድ ይፈልጋል፡፡ በዩሐንስ 14:6 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እርሱ ______________, _________________, ________________ እንደሆነና፡፡ ማንም__________________ ካልሆነ በቀር ወደ___________ መምጣት እንደማይችል ነገራቸው፡፡ ሃብታም ወይንም ድሃ፣ፈሪሳዊ ወይንም ሳማሪያዊ፣ፃድቅ ወይንም ኃጢአተኛ ሁሉም ወይንም ሰዎች ሁሉ_______________በማወቅ ይድኑ ዘንድ ይፈልጋል (1 ጢሞቲዎስ 2:4)፤ ከአብ ዘንድ _______________ እና ______________ ተሞልቶ የመጣውን እናውቅና እናመልክ ዘንድ(ዩሐንስ 1:14)፡፡ ከኢየሱስ ምን እንማራለን? ____________________________________

   __________________________________________________________________

3. ንግግራቸው ቁጥር 25 ላይ አልቆ እንደሆነ እስቲ ጠይቁ፡፡ ነገሩ እንዴት ነበረ? ኢየሱስ የምስራቹን ምንም ሳያስቀር ነበር የነገራት፡፡ እራሱን ገለፀላት ስንል ከዚህ በኋላ ከእርሱ ጋር ተጣብቃ ትኖር ዘንድ ነው፡፡ እርሱ መሲህ መሆኑን ሲናገር አምና ትቀበል ይሆን? እርሱ ማን እንደሆነ ትናገር ይሆን? ያለጥርጥረ መንፈስ ቅዱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ከነገራት ጋር ህብረት ይኖራት ዘንድ ከእርሱ ጋር ያላትን ግንኙት እያሳደገው እንደነበር እናምናለን፡፡ ከኢየሱስ ምን እንማራለን? ______________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. ይህንን የመሰለውን የኢየሱስ አገልግሎት ተመልክቼ እኔስ የተሰጠኝን አደራና ኃላፊነት ፈፅሜያለሁ? ወይ በዙሪያዬ ያሉትን የተተውትን፣ አስታዋሽ የሌላቸውን፣ ድሆችን፣ የተገፉትን፣ የተጎዱትን እና በፍርሃት እና በጭንቀት ውስጥ ያሉትን በምን መልኩ እንዳገለገልኳቸው እንዳስብ ተገደድኩ? ኢየሱስ ግን ሳምራዊቱን ሴት አልፈረደባትም፣ተቀበላት እራሱንም ገለጠላት። ታዲያ እኔስ አሁን ሌሎችን ሰዎች ተቀብዬ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ለማድረግ አሁን መውሰድ ያለብኝ እርምጃ ምንድነው?

   ______________________________________________________________

2. ለሰዎች ልቤን ክፍት አድርጌ የክርስቶስን ፍቅር በእኔ ህይወት ውስጥ ተመልክተው ወደ ክርስቶስ ይመጡ ዘንድ ሰዎችን ጋብዤ አውቅ ይሆን ? ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ምን አይነት መንገዶችን መጠቀም ይኖርብኝ ይሆን? ______________________________

   ______________________________________________________________

**ፀሎት**

ኦ ጌታ ሆይ፣ በዚህ ትምህርትህ በዙሪያዬ ስላሉት ስለ ጎረቤቶቼ ፣በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ስላሉት ሰዎች፣እኔ ከምኖረው በተለየ መልኩ የሚኖሩትን ፣ተስፋ የሚሆን ነገር ያጡትን፣የአካል እና የገንዘብ ችግር ያለባቸውን፣ትርጉም ያለው ግንኙነት ከሰዎች ጋር እንዲኖራቸው የሚፈልጉትን ሁሉ እንዳስብ ተገድጃለሁ። እንዳንተ ያለ ሰዎችን የሚያፈቅር እና ሰዎችን መጥላት የማይችል ልብን ስጠኝ። ለክብርህ የሚሆን ስራን እሰራ ዘንድ ከሰዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ የምችልበትን እድል ስጠኝ። ባስተማርከው ቃልህ እንዲሁም ባደረካቸው ድርጊቶች ውስጥ የአንተን ፍቅር እና ደግነት ሌሎች እንዲያውቁ አደርግ ዘንድ መንፈስህ ይርዳኝ።

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## <u>ምዕራፍ 4</u>

**መግቢያ**

አንድ ተግባር እያከናወናችሁ በድንገት ሳትጨርሱ በድንገት አቋርጣችሁ ታውቃላችሁ? እንደዚህ አይነት ነገር ሊያጋጥማችሁ እንደሚችል አምናለሁ። በዩሐንስ 4:26 ኢየሱስ ለሳምራዊቱ ሴት በቁጥር 27 ላይ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ እየነገራት እያለ "ደቀ መዛሙርቱ ከሄዱበት ስፍራ ተመልሰው መጡ።" ምግብ ለመግዛት ወደ ከተማ ሄደው ነበር። ይህቺ ሳምራዊት ሴት ወደ ውሃው ጉድጓድ ስትመጣ ኢየሱስን በማየቷ እጅግ ተደንቃ ነበር። አሁን ደግሞ ይባስ የሰዎቹ ቁጥር ጨመረ በዚህም በጣም ተደነቀች።

**የቤት ስራ**: ዮሐንስ 4:27-38 አንብቡ። በአንድ ጊዜ ብዙ ነገሮች ተከናወኑ።

- ኢየሱስ ውይይቱን ከ________________________ጋር ቀጠለ።
- ሴቲቱም ውይይቷን ከ___________________________ጋር ቀጠለች።

**መልመጃ**:

1. ደቀ መዛሙርቱ በቁጥር 27 ላይ ምን አስገረማቸው? ________________________________
2. ኢየሱስን ያልጠየቁት እርስ በእራሳቸው የተነጋገሩት ጥያቄ ምን ነበር?
   ሀ.________________________________________________________________
   ለ.________________________________________________________________
3. ሴቲቱ ወደ መጣችበት ተመልሳ ሄደች (ቁጥር 28)።
   ሀ. ትታ የሔደችው ምን ነበር? ________________________________________
   ለ. ወደየት ነበር የሄደችው? _________________________________________________
4. ምን ነበር ለሕዝቡ የነገረችው(ቁጥር 29)? _____________________________________
   _________________________________________________________________________
5. ለነገረቻቸው ነገር የሰጧት ምላሽ ምን ነበር? ጥያቄዋ (ቁጥር 30)? ____________
   _________________________________________________________________________
6. ለጥቂት ጊዜ እስቲ ወደ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ እንመለስ (ቁጥር 31)... የደቀመዛሙርቱ ትኩረት ምን ነበር ? __________________________________________________________
7. እነርሱ ለተጨነቁበት ነገር ምን የሚል ምላሽ ነበር የሰጣቸው (ቁጥር 32)? _______________
   _________________________________________________________________________
8. ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ስለምን እየተናገረ እንደሆነ ነው ያሰቡት (ቁጥር 33)? ______________
   _________________________________________________________________________
9. ልክ ለኒቆዲሞስ ስለመወለድ ፣ስለ ንፋስ እንዲሁም ውሃ ፣ለሳምራዊቷ ሴት ደግሞ ስለ ውሃ በምሳሌ እንደተናገረ አሁንም ሌሎች ምሳሌዎችን በመጠቀም መናገሩን ቀጥሏል። በቁጥር 34 መሰረት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ______________________ ተጠቀመ። አሁንም ምግብን በምሳሌነት በመጠቀም ይናገር ጀመር_________________________________________________
   _________________________________________________________________________
10. በቁጥር 35 ኢየሱስ ስለ እርሻ እና ስለደረሰው መከር እንደገና በምሳሌ ማስተማሩን ቀጠለ። ____________________አንስተው እንዲመለከቱ “ዓይናችሁን አንሡ ___________________ እንደ ነጣ ___________________ ተመልከቱ” በማለት ነገራቸው።

**ገለፃ**

1. "ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ" እያለ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ሲነግራቸው አስቡ። አሁን ወደ ቁጥር 30 ተመለሱ። የነጣውን አዝመራ ምሳሌ አብራሩ:______________________________________________

   ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እያስተማረ በነበረበት ወቅት ሳምራዊቷ ሴት ዜናውን በከተማው እያዳረሰች ነበር። የውሃ እንስራዋን ትታ ነበር የሄደችው። በቁጥር 14 ላይ ኢየሱስ "እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ለዘላለም አይጠማም" ብሎ እንደተናገረው በጣም የሚገርማችሁ ደቀመዛሙርቱ የገዙትን ምግብ እንኳን አልበላም ነበር።

2. ሴቲቱም ከእርሷ ጋር ብዙ ሰዎችን ይዛ መጣች፤ ኢየሱስም አስተማራቸው። ምን አይነት የአገልግሎት ጥምረት ነው! አንዱ ይዘራል አንዱ ደግሞ ያጭዳል። ሴቲቱ በምስክርነቷ ዘሩን ዘራች: ያደረኩትን ሁሉ የነገረኝን ኑና እዩ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? እያለች ዘራች ኢየሱስም ቃሉን በማስተማር በቃሉ አማካኝነት አጨደ!

**መልመጃ**

1. በቁጥር 39 ላይ ምንድነው የተነገረን? ____________________________________
2. በምን ምክንያት አመኑ? __________________________________________
3. ብዙ የከተማው ነዋሪዎች ከሴቲቱ ምስክርነት የተነሳ አመኑ። ከዚያም በላይ ከቃሉ የተነሳ ብዙዎች በእርሱ አመኑ። በእነዚህ ሰዎች ልብ አንድ ነገር ሆነ። ለሴቲቱም እንደዚህ አሏት: "አሁን የምናምን ________________አይደለም፥ እኛ ራሳችን ________________፤ እርሱም በእውነት ________________ ፤________________ እንደ ሆነ እናውቃለን ይሉአት ነበር። (ቁጥር 42)

**አስተያየት**

1. ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ለሁለት ቀናት ቆየ። እርሱ መሲህ እና የዓለም መድሃኒት መሆኑን እንዲያምኑ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ ማንም ከመገመት እና ከመደነቅ በስተቀር ሊያውቅ አይችልም። በጣም ማራኪ የሆነ ማንነት ስለነበረው ይሆን? የማስተማር ብቃቱ እነርሱ ሊረዱት በሚችሉት መንገድ ስላስተማራቸው ይሆን? ወይንም የተናገራቸው ቃላቶች ይሆኑ? ምን ሊሆን ይችላል? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ፃፉ : ____________________________

   ______________________________________________________________

2. ሰዎቹን የሴቲቱ ምስክርነት ወደ ኢየሱስ አምጥቷቸዋል። በእርሱ እንዲያምኑ ያደረጋቸው ግን የእርሱ ቃል ነበር። ከዚህ ክፍል በኋላ ስለዚህች ሴት ምንም የተባለ ነገር የለም። ምስክርነቷ

በቂ ነበር። ይህቺን ሴት ኢየሱስ ከነማንነቷ እንደተቀበላት እና እንደወደዳት ፣ኃጢአቷን በማስወገድ ከእስራቷ ፈቶ ከተማውን በሙሉ ወደ እርሱ እንዲመጣ እና ኢየሱስ የዓለም ሁሉ አዳኝ እንደሆነ በመናገር የእርሱ አገልግሎት አጋር እንዳደረጋት ተመልክተናል። እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን አመለካከት ግለፁ: ______________________________

______________________________

**ምዕራፍ 5**

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**: እኔ በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት ከማን ጋር እመሳሰላለሁ?

1. ሳምራዊቷን ?
   ሀ. ህይወቴ በመመሳቀሉ ምክንያት የማውቃቸውን ሰዎች ማግኘት አልፈልግም። የራሴ የተሳሳተ ምርጫዬ ሕይወቴን በመከራ ሞልቶታል።
   ለ. የሆንኩትን አምኜ እውነትን ከመጋፈጥ ይልቅ የወሬውን ርእስ ማስቀየር ይሻለኛል።
   ሐ. ያለሁበትን ሁኔታ በዝርዝር የሚያውቀው መሲህ ሊወደኝ እና ያለፍርድ ነፃ ሊያወጣኝ ይችላል ብዬ ለማመን እቸገራለሁ።
   መ. እኔን በእርግጥ በመውደዱ ምክንያት ሌሎችም እርሱን እንዲያውቁት እፈልጋለሁ።
   ምን ያህል ይህቺን ሴት እመስላለሁ?______________________________

   ______________________________

2. እንደ ደቀመዛሙርቱ ነኝ?
   ሀ. በረከሰች ከተማ ውስጥ ከሚኖሩ ከእነዚህ ህዝቦች ጋር እንደዚህ አይነት ግንኙነት እንዲኖረኝ አልፈልግም።
   ለ. እየሆነ ያለው ነገር አልገባኝም። እኛ የምናወራው ገዝተነው ስለመጣነው ረሃባችንን ሊያስታግስልን ስለሚችለው ምግብ ነው። አንተ ደግሞ የአንተ ምግብ የላከህን የአባትህን ፈቃድ መፈፀም እንደሆነ ነው የምትነግረን ። ይህ ደግሞ ለእኛ ፍፁም እንግዳ ነገር ነው።
   ሐ. ኢየሱስ፣ከአንተ ጋር ተገናኝቶ ሳያናግርህ የተለየህ ሰው ይኖር ይሆን? ሰዎችን እንዴት አድርገህ ወደ ራስህ እንደምታቀርብ ሊገባኝ አልቻለም።
   መ. መዝራት፣ማጨድ፣ መሰብሰብ...።አይኖቼን ከፍተህ የነጣውን አዝመራ መመልከት እንድችል አድርገኝ። የሚታየኝ ሁሉ ሰዎች፣ሰዎች፣ሰዎች ወደ አንተ ሲመጡ ብቻ ይሁን።
   ምን ያህል ደቀመዛሙርቶችን እመስላለሁ? ______________________________

   ______________________________

3. የከተማውን ሰዎች እመስላለሁ?

ሀ. ስለዚች ሴት እንዴት ሊያውቅ ቻለ ፣ምስጢር አድርገን የተውነውን፣ከጀርባዋ እየተንሾካሾክን የምናወራውን ሁሉ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ለመሆኑ ይህ ሰው ማነው?

ለ. በጣም ጓጉቻለሁ። ይህቺ ሴት እስከዛሬ አንዱንም ባሏን ልታስተዋውቀን አልጠራችንም ዛሬ የተለየ ነገር አግኝታለች ማለት ነው። ይህ ሰው ልዩ መሆን አለበት።

ሐ. በእውነት ልዩ ሰው ነው። ከዚህ ቀደም ሰምቼውም ሆነ ተምሬው የማላውቀውን ትምህርት ነው የሚያስተምረው ። ስለዚህ ብዙ መማር ስለምፈልግ በዚህ እንዲቆይ እፈልጋለሁ።

መ. አሁን የማምነው ሰዎች ስለነገሩኝ ሳይሆን እኔው እራሴ ከእርሱ ስለሰማሁ ነው። በእርግጥም ያ ሰው ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ አምኛለሁ!ምን ያህል የከተማውን ሰዎች እመስላለሁ? ________________________________________

________________________________________

**የቤት ስራ**:

እስቲ የራሳችሁን ታሪክ ፃፉ። የምታውቁትን ተናገሩ! ሳምራዊቱ ወደ ከተማ ሄዳ ታሪኳን ነገረቻቸው፣ምስክርነቷን አካፈለቻቸው። ትናገር የነበረችው በኃይል፣በታላቅ ስሜት ፣በታላቅ ጉጉት እንደነበረ ምንም ጥርጥር የለውም ምክንያቱም ሕዝቡ "ኑ ና እዩ" ለሚለው ጥሪዋ ታላቅ ምላሽ ነው የሰጣት። ነገሯን ሁሉ ስለነገራት ሰው ስትመሰክርላቸው በታላቅ ጉጉት ወደ እርሱ እንዲመጡ ማድረግ መቻሏ ምስክር ነው። እርሱ ይሆንን…? ምንም እንኳን ስለእርሱ የምታውቀው ጥቂት ነገር ቢሆንም እንኳን ስለእርሱ መናገር አልተወችም። ምናልባት እናንተም ይህ ኢየሱስ የሚባለውን ሰው ሔጄ ብተዋወቀው የህይወቴን መልክ ይቀየር ነበር ብላችሁ ማሰባችሁ አይቀርም። የእናንተስ ታሪክ ምን ይመስላል? ያለፈው ዘመናችሁ ምን ይመስላል? ኢየሱስ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ ሳምራዊቱን ሴት እየጠበቃት ነበር። እናንተንም በውሃው ጉድጓድ ፣ወይንም በመኖሪያ ቤታችሁ፣በስራ ቦታችሁ፣በቢሮአችሁ፣በየትኛውም ስፍራ ብትሆኑ ያለማቋረጥ እስኪያገኛችሁ ይጠብቃችኋል። እርሱ የዓለም መድኃኒት መሆኑን እንድታውቁ ሲጋብዛችሁ እናንተም ታሪካችሁን ፃፉ።

ታሪካችሁን ከጻፋችሁ በኂላ ሰዎች ታሪካችሁን እንዲሰሙ እየጋበዛችኂቸው ንገሯቸው ። ያለፍርሃት መስክሩላቸው።

**ማሰላሰል**

ሳምራዊቱ ሴት ኢየሱስ ነገሯን ሁሉ ገልጦ ሲነግራት ወደ ቤቷ ሮጣ ሄዳ በሯን ዘግታ አልተቀመጠችም ወይንም አልተደበቀችም። ነገር ግን የሆነውን ነገር በሙሉ ለሰዎች ማካፈል ቀጠለች። ምስክርነቷን በግልፅ እና በአደባባይ ነበር ያደረገችው!

ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ ክርስቲያኖች መልእክት የፃፈላቸው በእስር ቤት ሆኖ ነበር፡፡ በዚያም ስፍራ ሆኖ ወንጌሉን በግልጥ መናገር ይችል ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳው እንዲፀልዩለት መልእክት አስተላልፎ ነበር፡፡ ኤፌሶን 6:19-20 በደብተራችሁ ላይ በመፃፍ በቃላችሁ ለመያዝ ሞክሩ፡፡

ቀጥሎ ያሉት ክፍሎች የወንጌልን ምስጢር የያዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው፡፡ ይህ ምስጢር ምን ይሆን? በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያለውን ጥልቅ ነገር ተመልከቱ:

- ሮሜ 16:25-27 ______________________________

  ______________________________
- ቆላስያስ 1:26-27 ______________________________

  ______________________________
- ቆላስያስ 2:2-3 ______________________________

  ______________________________
- ኤፌሶን 1:9-10 ______________________________

  ______________________________

**ፀሎት**

በኤፌሶን 6 ላይ ያሉት እነዚህ ድንቅ ቃላት የዘውትር ፀሎቶቻችሁ መሆን ይገባቸዋል፡ ጌታ ሆይ የአንተ አምባሳደር ሆኜ የተላኩበትን ስራ፣ አፌን ከፍቼ የምስራቹን ቃል መናገር እንደሚገባኝ በግልጥ መናገር እችል ዘንድ እርዳኝ…አሜን!

# ትምህርት ሶስት

# ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛል

## ሉቃስ 19:1-10 — ዘኬዎስ

---

**የክፍል ሶስት ቅኝት**


ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 3:  ሉቃስ 19:1-10

- ኢየሱስን ማየት የወደዱ ሁለት ሰዎች
- ኢየሱስ እና ዘኬዎስ
- የጉባኤው ሁኔታ
- የእግዚአብሔር ፍለጋ
- የእኔ ተልዕኮ

***መግቢያ***

ይህ ታሪክ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18 መጨረሻ ላይ ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 19 ቁጥር 10 ድረስ ይዘልቃል። በዚህ ክፍል ኢየሱስን ማየት የወደዱ ነገር ግን ያልሆነላቸውን የሁለት ሰዎች ታሪክ ያቀርብልናል። ነገር ግን ሁለቱም ኢየሱስን ለማየት የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፍል ወስነዋል። አንደኛው ይህንን መሻቱን ለማሳካት መጮህን የመረጠ ሲሆን፣ አንደኛው ደግሞ ዛፍ ላይ መንጠልጠልን መርጧል። ኢየሱስ ሁለቱንም አግኝቷቸዋል። ለአንዱ አካላዊ፣ ለአንዱ ደግሞ መንፈሳዊ እይታ ሲሰጠው ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። ይህንን ክፍል ስታጠኑ ልክ እነርሱ እንዳደረጉት እናንተም ኢየሱስን ለማየት ወስኑ።

ኢየሱስ በኢያሪኮ አቅራቢያ ሲመጣ፣ ከዚያም ወደ ኃጢአተኞች ቤት ሲገባ፣ በዚያ ተሰብስበው የነበሩትን ሰዎች ሁኔታ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። የሁለቱንም "ማየት የተሳናቸው" ሰዎች ሁኔታም ልብ ብላችሁ ተመልከቱ።

የሾላውን ዛፍ ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳትዘነጉ። ይህ ዛፍ ለአንድ ሰው በምን መልኩ ሊያገለግል ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? እስቲ እንደ አንድ ዛፍ እራሳችሁን አስቡ እና ኢየሱስን ለማየት የጓጓን ሰው ማየት ይችል ዘንድ መርዳት ምን ያህል ታላቅ ነገር እንደሆነ አስቡ።

## ትምህርት 3

**ምዕራፍ 1**

**የቤት ስራ**: በዚህ ሶስተኛ የታሪክ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ እየተጓዘ ነው፡፡ በመንገዱ ላይም አንድ ማየት የተሳነው ለማኝ አገኘ፡፡ ይህንን በሉቃስ 18:35-43 የሚገኝ ታሪክ በጥሞና አንብቡ፡፡

- የሰውየው ችግር ምን ነበር?
- ኢየሱስ ምን እንዲያደርግለት ነበር የፈለገው?
- ኢየሱስ ምን አደረገለት?
- የሰውየስ ምላሽ ምን ነበረ?

**መልመጃ**

1. ይህ ሰው ____________________ ለማኝ ነበር (ቁጥር 35)፡፡
2. የሰዎችን ድምፅ እና ግርግር ሲሰማ ኢየሱስ በዚያ እያለፈ መሆኑን ሲያውቅ ምን ብሎ ነበር የጮኸው (ቁጥር 37-39)? "______________________________________________፡፡"

**ትምህርት**

ይህ ለማኝ ሰው ኢየሱስ ማን እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ ስለዚህም "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ!" እያለ ጮኸ፡፡ የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ እያለ መጮኹ የሚያመለክተው ይህ ሰው ኢየሱስ መሲህ መሆኑን አምኖ መቀበሉን ነው፡፡ ኢየሱስ ምህረት ሊያደርግለት እንደሚችልና የታወሩትን አይኖቹን ሊከፍትለት እንደሚችል ተረድቷል፡፡

**መልመጃ**

1. ኢየሱስ በቁጥር 40 ላይ ሰውየውን ወደ እርሱ እንዲያመጡት ነገራቸው፡፡ ኢየሱስ ሰውየውን ምን ብሎ ነበር የጠየቀው? ______________________________________________
2. ሰውየውም እንደዚህ በማለት መለሰ "__________________________________________፡፡"
3. ኢየሱስም ____________________ እምነትህ አድኖሃል አለው (ቁጥር 42) በዚያን ጊዜ __________________ እግዚአብሔርንም እያከበረ __________________፡፡
4. ሕዝቡም ____________________ እግዚአብሔርን ____________________ (ቁጥር 43)፡፡

**የቤት ስራ**:  ይህንን ታሪክ በአዕምሯችሁ ይዛችሁ ሉቃስ ምዕራፍ 19 አንብቡ። ኢየሱስ ሌላውን በቁመቱ ማጠር ምክንያት ኢየሱስን ማየት የተሳነውን ሰው ያገኘው በኢያሪኮ ነበር። ስሙም ዘኬዎስ ይባላል። እስቲ ስለዚህ ሰው በሉቃስ 19:1-10 የተፃፈውን ታሪክ አንብቡ።

- የሰውየው ችግር ምን ነበር?
- መፍትሔውስ?
- ኢየሱስ የሰጠው መፍትሔ ምን ነበር?

**መልመጃ**:

1. በቁጥር 1 ላይ ምንድነው የተነገረን? ____________________

   ምናልባት ኢየሱስ ኢያሪኮ ለመቆየት ያሰበ ላይመስል ይችላል።

2. ዘኬዎስ የሚኖረው በኢያሪኮ ነበር (ቁጥር 2)። በዚህ ስፍራ ስለ ዘኬዎስ የምንማራቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?

   ሀ ____________________ነበረ።

   ለ ____________________ነበረ።

**ትምህርት**

ዘኬዎስ የቀራጮች አለቃ በመሆን የሮም መንግስትን የሚያገለግል ሰው ነበረ። እነዚህ ቀራጮች ኃብት ለማግኘት ብለው በሕዝቡ ላይ ያልተገባ ቀረጥ ይጭኑ ነበር። በዚህ ምክንያት እንዲሁም ለሮማውያን ቅጥረኛ በመሆን የአይሁድን ህዝብ ይጨቁኑ ስለነበር በሕዝቡ ዘንድ እንደ ከዳተኛ ተቆጥረው እጅግ የተጠሉ ነበሩ።

**መልመጃ**

1. በቁጥር 3 መሰረት ዘኬዎስ ምን ነበር ማድረግ የፈለገው? ____________________
2. ነገር ግን ዘኬዎስን ኢየሱስ ማን እንደሆነ መመልከት እንዳይችል ያደረገው ምን ነበር?

   ሀ ____________________

   ለ ____________________

3. ታዲያ ምን አደረገ (ቁጥር 4)? በዚያችም መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና __________ወደ ፊት __________ በአንድ __________ ላይ ወጣ።

**የቤት ስራ**

እውነም ሆነ ዘኬዎስ ኢየሱስን ማየት አለመቻላቸው በጣም የሚገርም ነገር ነው። እስቲ በእነዚህ ሁለት ታሪኮች ውስጥ ከማየት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቃላት በሙሉ አስምሩባቸው። ለምሳሌ

በሉቃስ18፡41 ማየት የተሳነው ለማኝ እንደዚህ በማለት ተናገረ፡ “ማየት እፈልጋለሁ” (ፍንጭ፡ ቢያንስ ስምንት ያህል ተመሳሳይ ቃላትን ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡)

**ገለፃ**

1. ሉቃስ ይህንን ታሪክ በዚህ ክፍል ሲፅፍ ስለ ዘኬዎስ አጭርነት አፅንኦት ሰጥቷል ፡፡ ምናልባት ይህ ሁኔታ በዘኬዎስ ህይወት ላይ ከባድ ተፅእኖ የፈጠረበት ችግር እንደነበረ ልንገምት እንችላለን፡፡
   ሀ. የዘኬዎስ የቁመቱ ማጠር ምን ያህል ችግር ሆኖበታል ብላችሁ ታስባላችሁ? በህዝቡ መካከል ካለው ስፍራ? ወይንም ከአላማው አንፃር? ______________________________
   
   ________________________________________________________________________
   
   ለ. ለዚህ አጭር የቀራጮች አለቃ በሰዎች ዘንድ የተቀባይነትና የተፈላጊነት መንፈስ እንዲኖረው ያደረገው ማን እንደሆነ ታስባላችሁ?
   
   ________________________________________________________________________

2. አሁን በጣም ታዋቂ የሆነ ሰው በዚያ መንደር ያልፋል፡፡ ለመሆኑ ዘኬዎስ “ኢየሱስን ለማየት የወሰነው ለምንድነው?” ይህ ሰው ማነው? የሚከተሉትስ እነማን ናቸው? ኢየሱስን በማንኛውም ጊዜ ማየት የሚችልበት ተስፋ ቢኖረው ኖሮ እንደዚያ ዛፍ ላይ ተንጠላጥሎ ለማየት ዋጋ አይከፍልም ነበር፡፡ ትልቅ እና የተከበረ ሰው ቢሆንም በቁመት ማጠር ምክንያት አንድን ነገር ለመመልከት ሰው በተሰበሰበበት ስፍራ ዛፍ ላይ መንጠላጠል ምን አይነት ስሜት ሊፈጥር ይችላል? ________________________________________________________________
   
   እርሱ ግን ምንም አማራጭ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ ኢየሱስን ማየት ከፈለገ ፈጥኖ ዛፍ ላይ መውጣቱ ግድ ነው!

<u>**ምዕራፍ 2**</u>

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**: ስለ ሾላው ዛፍ አስቡ፡፡ የዘኬዎስን ታሪክ ስታነቡ እራሳችሁን ልክ እንደዚያ ዛፍ ሆናችሁ ማሰብ እንድችሉ ያግዛችኋል…

1. ለመሆኑ ያ የሾላ ዛፍ ዘኬዎስን በምን መልኩ ነበር የጠቀመው? _________________________
   
   ________________________________________________________________________

2. በዚህ የሾላ ዛፍ ሊመሰሉ የሚችሉ ሰዎች ስለእኛ ግድ የሚላቸው እና ካለንበት የውርደት ስፍራ ደግፈው የሚያነሱን፣የሚያበረቱን፣የህይወታችንን አቅጣጫ የሚያስቀይሩን ሰዎች ናቸው፡፡ በእናንተ ህይወት ውስጥ ልክ እንደዚህ ዛፍ ያገለገሏችሁ ሰዎች እነማን ናቸው?
   ሀ. እስቲ ከውድቀት የተነሳችሁበትን ወቅት መለስ ብላችሁ አስታውሱ
   
   ________________________________________________________________________

ለ. እስቲ እናንተም ሰዎች በራሳቸው ማድረግ ያልቻሉትን ነገር በእናንተ እርዳታና ድጋፍ አማካኝነት መመልከት የቻሉበትን ጊዜ አስታውሱ ______________________________

______________________________________________________________________

ሐ. ይህ ልዩ የሆነ የሾላ ዛፍ ዘኬዎስ ኢየሱስን ማየት እንዲችል አድርጎታል። ሌሎች በእኔ በኩል ኢየሱስን ማየት ቢችሉ ፣እርሱ ማን እንደሆነ ማወቅ እንዲችሉ እራሴን እንደዚያ የሾላ ዛፍ ማድረግ ብመርጥ በህይወቴ ላይ የሚፈጠረው ልዩነት ምን ይሆን?______________________________________________________________

______________________________________________________________________

መ. ሌሎች በእኔ በኩል ኢየሱስን ማየት እና ማወቅ ይችሉ ዘንድ እርሱንም ካዩ በኋላ ሕይወታቸውን በቀድሞ ሳይሆን በሌላ መልክ ማየት ይችሉ ዘንድ ለሰዎች ህይወት ብርታት ሆኜ ኢየሱስን እንዴት አድርጌ ላሳያቸው እችል ይሆን? _______________

______________________________________________________________________

**መልመጃ**:

1. ኢየሱስ ወደዚያ ስፍራ ሲመጣ በዚያ ስፍራ ምን ሆነ (ቁጥር 5)? _________________________
   ኢየሱስ ዘኬዎስ የት እንደነበረ ያውቃል። ይህ ሰው ኢየሱስ ማን እንደሆነ ማወቅ እንደሚፈልግ ኢየሱስ ያውቅ ነበር።
2. ኢየሱስ ለዘኬዎስ ምን አለው? _____________________________________________

   ______________________________________________________________________
3. ኢየሱስ ዘኬዎስን ሲጠራው የሚያስቸኩል አይነት አጠራር ጠርቶታል ብላችሁ ታስባላችሁ? ምን አይነት ቃላቶችን ተጠቅሞ ይሆን የጠራው? ____________________________________

**ገለፃ**

ይህንን ታሪክ እንዲያው ስንመለከተው ኢየሱስ በዚያ መንደር ያለምክንያት ያለፈ አይመስልም (ቁጥር 1)። ኢየሱስና ዘኬዎስ በተገናኙበት ወቅት ከተፈጠረው ነገር የተነሳ ኢየሱስ ለዘኬዎስ ያለው ልብ ምን ይመስል ነበር? በዘኬዎስስ ህይወት ቅድሚያ የሰጠው ጉዳይ ምን ነበር? __________

______________________________________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ ጥያቄዎች**: በዚህ ታሪክ ኢየሱስ ህይወቴን በምን መልክ እንድመከተው ነው የፈለገው…

1. እቅዶችን እንዳቅድ ? ____________________________________________________
2. ቀኖቼን እንዳስተካክል? ___________________________________________________
3. ጊዜዬን በአግባቡ እንድጠቀም? _______________________________________________

**መልመጃ**

1. ዘኬዎስ በምን መልኩ ነበር ምላሽ የሰጠው (ቁጥር 6)? ______________________________

______________________________________________________________

ከዛፉ ላይ በፍጥነት ነበር የወረደው፡፡ “ዛሬ በእኔ ቤት መዋል ፈልጓል!” የዘኬዎስ ከዛፉ ላይ የአወራረድ ፍጥነቱ የኢየሱስን የአጠራር ሁኔታ ያመለክተናል ? ______________________

2. በሾላው ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ለነበረው የቀራጮች አለቃ የኢየሱስ ቃላት ምን ትርጉም ይኖራቸዋል? ______________________________________________

**ገለፃ**

1. እራሴ በዘኬዎስ ስፍራ ባስቀምጥና ልክ እንደእርሱ የማልጠቅም ፣ተቀባይነት የሌለኝ፣በዙሪያዬ ባሉት ሰዎች የተጠላሁ ሰው ብሆን የኢየሱስን ጥሪ በምን መልኩ ነበር የማስተናግደው?

______________________________________________________________

2. የኢየሱስን ድንገተኛ ጉብኝት ከፕሮግራሜ ውጪ እና በግድ እንደሆነ አስበው ይሆን? በዙሪያዬ የነበሩት ሰዎች ኢየሱስ እኔን ሊጎበኝ በተናገረበት ወቅት ስለእኔ ያሰቡት እና የተናሩት ነገር ያበሳጨኝ ይሆን ? ወይንስ ደግሞ ኢየሱስን በዚህ አጭር እና ለመስተንግዶ ባልተዘጋጀሁበት ሰዓት በምን ላስተናግደው እችላለሁ ብዬ አስብ ይሆን? እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን ሃሳብ አካፍሉን: ______________________________________________

______________________________________________________________

3. ዘኬዎስ ባለጠጋ ሰው ነበረ፡፡ ያለጥርጥር በቤቱ የሚያገለግሉት ብዙ አገልጋዮች የነበሩት ሰው ነበረ፡፡ አንድ ሰው ኢየሱስን ለማየት በብርቱ የመፈለጉ ነገር በሚያስገርም ሁኔታ ብዙዎች ኢየሱስን እንዲያዩ ምክንያት ሆነ! እስቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁን ሃሳብ አካፍሉን: _________

______________________________________________________________

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ አንዳንድ ጊዜ እንደ ዘኬዎስ እንደሆንኩ ይሰማኛል፡፡ ከሁሉ እንዳነስኩ፣ የማልጠቅም፣ በማንም የማልታወቅ ወይንም ማንም ጎሽ ብሎኝ የማላውቅ ሰው እንደሆንኩ ይሰማኛል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ህይወቴ ምሳሌነት የጎደለው ነው፡፡ ህይወቴን ችግር ውስጥ የሚከቱ የተሳሳቱ ምርጫና ውሳኔዎችን አደርጋለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ እባክህ ምህረትህ በእኔ ላይ ትሁን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እንደ ዘኬዎስ አንተ ለማየት እጓጓለሁ፡፡ ጌታ ሆይ ላይህና ላውቅህ እወዳለሁ፡፡ ከአንተ ጋር በፍቅር ተጣብቄ መኖረ እፈልጋለሁ፡፡ እባክህ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ዛሬ ወደ እኔ ቤት ግባ፡፡ መጥተህ በልቤ ኑር፡፡______________________________________________________

______________________________________________________________

**ምዕራፍ 3**

**መልመጃ**:

1. ለተመለከቱት ነገር የህዝቡ ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 7)? ____________________

______________________________________________________________________________

2. ሕዝቡ ለዘኬዎስ የነበረው አመለካከት ምን ይመስል ነበር? ______________________________
3. ሕዝቡ ለኢየሱስ የነበረው አመለካከት ምን ይመስል ነበር? ______________________________

   በዚያ ተሰብስቦ ከነበረው ሕዝብ አንፃር የኢየሱስ ወደ ኃጢአተኛው ቤት የመግባቱ ነገር አግባብነት የሌለው ድርጊት ነው፡፡ ከኃጢአተኞች ጋር አብሮ መሆኑ እርሱንም ኃጢአተኛ ፣ወይንም ከእነርሱ እንደ አንዱ ያደርገዋል፡፡ ከኢየሱስ ጋር ህብረት የሚያደርጉ ኃጢአተኞች ከኃጢአታቸው ነፃ እንደሚሆኑ አላመኑም ነበር፡፡ ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብ ዘኬዎስ ከኢየሱስ ጋር በመገናኘቱ ይቅርታና ምህረት አግኝቶ ነፃ እንዲሆን ሳይሆን እንዲፈረድበት ነበር በጉጉት የሚጠባበቁት፡፡

4. በዘኬዎስ ላይ ሲያጉረመርሙ ከነበሩት መካከል አንዱ ፈውስን ያገኘው እውሩ ሰው ሊኖር ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? ከኢየሱስ ጋር ወደ ዘኬዎስ ቤት እንደሄደ ታስባላችሁ? ወይንም ወደ ቤቱ ተመልሶ ኢየሱስን መከተል እንዳለበት እና እንደሌለበት የሚያስብ ይመስላችኋል ? እስቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለፁ:________________________________________

______________________________________________________________________________

**ማሰላሰል**

ሁለተኛ ቆሮንቶስ 5:21 በኃጢአትና በበደል ወደ ተሞላው ህይወታችን ኢየሱስን ስንጋብዘው የተካሄደውን ለውጥ በጥሩ ሁኔታ ያስረዳናል፡፡እስቲ ይህን የምንባብ ክፍል ፃፉት፡፡____________________

______________________________________________________________________________

1. የተካሄደው ለውጥ ምን ነበር ? እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ________________እንሆን ዘንድ ________________እርሱን ________________ ________________ አደረገው፡፡
2. ከተሰበሰበው ሕዝብ አመለካከት አንፃር ይህንን ምንባብ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ወደ ዘኬዎስ ቤት ሲገባ በምን መልኩ እንደተፈፀመ ታስባላችሁ ? __________________________

**ገለፃ**: (ሉቃስ 19:8)

1. የዘኬዎስን ጉዳይ ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው? ምን ነበር ተነስቶ ያለፍርሃት እንዲናገር ያደረገው (ቁጥር 8): ______________________________________________________

______________________________________________________________________________

2. የዘኬዎስን ህይወት በልዩነት እንዲለወጥ ያደረገው ነገር ምን ነበር? ____________________

______________________________________________________________________

3. በዚያን ቀን ዘኬዎስን የኢየሱስን ማንነት እንዲረዳ ያደረገው ክስተት ምን ነበር? _________

______________________________________________________________________

**በጥልቀት መመልከት**

አንድ ሰው ባልንጀራን በሚያታልልበት ፣በሚሰርቅበት፣ወይንም በሚያጭበረብርበት ጊዜ የሚዳኘው በኦሪት ዘሌዋውያን ላይ በተፃፈው ህግ መሰረት ነው። ሌዋውያን 6፡4-5 አንድ ሰው የሌላውን ንብረት ቢሰርቅ ወይንም ያለፍቃድ ቢወስድ የወሰደውን ይመልስ ይላል ። በመቀጠል በቁጥር 5 ላይ እንደዚህ ይላል፡“______________________________________________________________________

______________________________________________________________________ይስጠው።”

ሕዝቅኤል 33፡14-16 በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መረዳትን ይሰጠናል። ይህ ክፍል የወሰዱትን ስለመመለስ ጨምሮ ይነግረናል። ቁጥር 16 እንደዚህ ይላል፡

“__________ይታሰብበትም_________ና_________አድርጎአል በእርግጥ _________።”

እነዚህ ክፍሎች ኢየሱስ በዘኬዎስ ቤት “ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኗል” በማለት ስለተናገረው ንግግር ጥሩ መረዳት እንዲኖረን ያደርጋል። ዘኬዎስ የአብርሃም ልጅ ነው። ከእግዚአብሔር ህግ የራቀ አይሁዳዊ ሲሆን የእየሱስ ወደ እርሱ መምጣት በልቡ የሚያውቀውን ኃጢአት ገለጠለት። የሕዝቡ ጉርምርምታ ትክክል ነበር ምክንያቱም ዘኬዎስ ኃጢአተኛ ሰው ነበር። ኢየሱስ ግን ከአብርሃም ቤት የጠፋውን ሰው አገኘው።

**የከህይወት ጋር ማዛመድ ጥያቄ**

1. ዛሬ ኢየሱስ ወደ እናንተ ቤት መጥቷል? ከመጣ በህይወታችሁ ልዩነትን ሳያደርግ አይመለስም። ከእየሱስ ጋራ በመገናኘታችሁ ከህይወታችሁ ፅድቅ እና ቅድስና ይንፀባረቃል። ህይወታችሁን እንዴት ነው የምትመዝኑት ምክንያቱም እርሱ በህይወታችሁ ልዩነትን ሊያደርግ በስራ ላይ ነው?______________________________________________________________
2. ኢየሱስ በህይወታች በሚሰራበት ጊዜ ፅድቅንና እውነተኛ መንፈሳዊነት ለሌሎች በህይወታችሁ የምታሳዩት እንዴት ነው? ______________________________________________

**ፀሎት**

ኢየሱስ ኃጢአቴን ከእኔ ላይ አነሳህልኝ ፣ ኃጢአቴን በጽድቅህ ለወጥከው። ስለዚህም ምስጋና እና አምልኮዬን ለአንተ እሰጣለሁ። ህግ ስለሚያዘኝ ሳይሆን ከታላቁ ፍቅርህና ፣ምህረትህ የተነሳ ኃጢአቴን እንድናዘዝ እርዳኝ።

---

## ምዕራፍ 4

### ገለፃ

እንደዚህ የሚል ጥያቄ እንጠይቅ፡ ዘኬዎስ በኢየሱስ ፊት ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ያደረገው ነገር ምን ነበር ? ለሮማውያን ከሚቀርጠው ቀረጥ ይዘርፍ ስለነበር ባለጠጋ እንደሆነ ተመልክተናል። ኃብቱን ያገኘው ፅድቅ በሌለበት መንገድ እንደሆነና የኃብቱን እኩሌታ ለድሆች እንደሚሰጥ፤ ላታለላቸው እና ገንዘባቸውን በግፍ ለወሰደባቸው ደግሞ አራት እጥፍ እንደሚመልስ ተናገረ። ይህን ሁሉ ሲያድረግ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት "ኢየሱስ! አንተን ከማግኘቴ እና ካገኘሁት ምህረት ጋር ሲወዳደር አሁን የማደርገው ነገር ከምንም የማይቆጠር ነው" የሚል ነው። በዘኬዎስ ህይወት እና ቤት ውስጥ የኃብትና የብልፅግናን ስፍራ የወሰደው ምንድነው? በምን ተተኩ? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ተናገሩ፡____________________________________________________________

_________________________________________________________________

### መልመጃ

1. በቁጥር 9 ላይ ኢየሱስ ለዘኬዎስ ምን ነበር ያለው?
   - ሀ. __________________________________________________
   - ለ. __________________________________________________
2. በቁጥር 10 ላይስ ኢየሱስ ምን ተናገረ? ____________________________________

   ____________________________________________________________

### ትምህርት

እስቲ ቁጥር 9 እና 10 በጥልቀት እንመልከታቸው። በቁጥር 9 ላይ ኢየሱስ "ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆነ" በማለት ተናገረ። በመዝሙር 27:1 "___________________ ብርሃኔና _______________ ነው..." የሚል ቃል እናነባለን። እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው በሚለው ቁጥር ውስጥ መድኃኒት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ነጻ መውጣትን ነው። ከኃጢአተኛ ማንነቴ፣ሊያጠፉኝ ከሚፈልገው ክፉ ፣ከዘላለም ጥፋት ያዳነኝ እግዚአብሔር ነው። ነጻ የሚያወጣኝ፣የሚያድኝ ፣የሚጠብቀኝ፣ሊያጠፉኝ የሚፈልጉትን በሙሉ እቋቋማቸው ዘንድ የሚያስችለኝ እርሱ ነው። ወደ ሉቃስ 19:9 ተመልሰን ስንመለከት ኢየሱስ ለማለት የፈለገው "ዛሬ አዳኝህና ፣ታዳጊ አምላክህ እግዚአብሔር

ወደዚህ ቤት መጥቷል!" ቀጥሎም ኢየሱስ እንደዚህ አለ "...እርሱም ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና" በዚህ ክፍል ኢየሱስ ዘኬዎስን አይሁዳዊ መሆኑን፣እስራኤላዊ እንደሆነ፣ዕብራዊ እንደሆነ፣የአብርሃም ልጅ እንደሆነ መዳንም እንደሚያስፈልገው ተናገረ።

በቁጥር 10 ውስጥም ኢየሱስ ተመሳሳይ ነገር ነበር የተናገረው። እንደዚህ አለ "__________________(ዘኬዎስ ሆይ መድኃኒትህ የሆነው ኢየሱስ) ________________(በስም የአብርሃም ልጆችን ፣ዛሬ ግን በተለይ ዘኬዎስ ሆይ አንተን) ሊፈልግ እና ሊያድን መጥቷል" የመጣሁት የእኔ የሆኑትን የአብርሃምን ልጆችን ላድናቸው ነው። ሌሎቹንም የጠፉትን በሙሉ ልፈልግ መጥቻለሁ፣የህይወት ትርጉም ለጠፋባቸው፣በራሳቸው ፍልስፍና እና መንገድ የተያዙትን፣ህይወታቸውን የሚመሩበት ነገር የሌላቸውን ለማዳን መጥቻለሁ። ዘኬዎስ ሆይ እንዳንተ ያሉትን ኃጢአተኞች፣ የጠፉትን  አሁን ግን የተገኙትን ለመፈለግ መጥቻለሁ።!"

**ማሰላሰል**

ኢየሱስ ለዘኬዎስ የተናገራቸው ቃሎች በሙሉ እኛም ይመለከቱናል። ቁጥር 10 ደብተራችሁ ላይ በመፃፍ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበትን ተልእኮ በደንብ ተረዱ። ዓለማው ፣ከሰማይ የወረደበት ምክንያት ይህ ነበር። ከመጀመሪያው ጀምሮ እግዚአብሔር ፍጥረቱን በሙሉ ወደ ራሱ የመሰብሰብ እና የመመለስ ሃሳብ ነበረው። በዘፍጥረት 3:15 ላይ መሲህ እንደሚመጣ ተስፋ ተሰጥቷል። ይህ መሲህ ደግሞ አሁን መጥቷል፣ እነሆ አሁን በዘኬዎስ ቤት ይገኛል። ዘኬዎስንም "ዘኬዎስ ሆይ ወደዚህ ምድር የመጣሁት በአንተ ምክንያት ነው" እያለው ነው ያለው። "ጠፍተህ ነበር አሁን ግን ተገኝተሃል።" ልክ እንደ እውሩ ሰው አንተም ማየት የተሳነህ ነበርክ እኔ ግን ፈልጌ አገኘሁህ። እኔ የሰው ልጅ ፣የዳዊት ልጅ በሌላ በምንም መንገድ እኔን ፈልገህ ልታገኘኝ ስለማትችል እኔ አንተን ፍለጋ መጣሁ። "ዘኬዎስ ሆይ ልክ አዳምና ሔዋንን በኤደን ገነት እንደፈለኳቸው የመሲህንም ተስፋ እንደሰጠኋቸው አንተንም ፈልጌ ላድንህ መጥቻለሁ ።  ለዘለአለም ትኖር ዘንድ እንደዚሁም የሚያምኑ ሁሉ የዘላለምን ህይወት ያገኙ ዘንድ በቅርቡ እራሴን ለአንተ እሰጣለሁ ( ዩሐንስ 3:16)። "ዘኬዎስ ሆይ ወደዚህ የመጣሁት ልፈርድብህ ሳይሆን በእኔ በኩል ትድን ዘንድ ነው (ዩሐንስ 3:17)!"

**<u>ምዕራፍ 5</u>**

**መልመጃ** : እስቲ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ሰዎች ማን ፈልጎ እንዳገኛቸው እናስታውስ…

| እነዚህን ሰዎች የት ነው ያገኛቸው? | **ያገኛቸውስ ማነው?** | **የት ነበር ያገኛቸው?** |
|---|---|---|
| ዘፍጥረት 3:8-9 | | |
| ዘፍጥረት 11:31-12:4 | | |
| ዘጸአት 3:1-4 | | |
| 1 ሳሙኤል 3:2-10 | | |
| 1 ሳሙኤል 16:11-12 | | |
| 1 ነገሥት 19:19-20 | | |
| ነህምያ1:1, 3-4 | | |

**ገለፃ**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌሎች ብዙዎች ሰዎች እግዚአብሔር ከየት ፤ ከየት እንዳገኛቸው ታሪካቸው ተፅፎ ይገኛል። እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር የእለት ተእለት ስራቸውን ሲያከናውኑ፣ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ላይ እያሉ ነበር ያገኛቸው። አንድ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከዚያ ሁኔታ ነፃ የሚያወጣቸው ነገር እስካልመጣ ድረስ ለመደበቅ መሞከር ስፍራን በመለወጥ መሸሽ የተለመዱ ነገሮች ናቸው ። እረኛ ሆኖ በጎችን መጠበቅ እና የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ በማደሪያው ድንኳን ፣በቤተመቅደስ፣ወይንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ወይንም በጥማድ በሬ ማረስ ወይንም ነገሥታትን ማገልገል ብቻ የትኛውም ስፍራ ላይ ቢሆኑ እግዚአብሔር ያሉበት ሁኔታ ሳይገድበው ከያሉበት ሰዎችን ጠርቶ ህይወታቸውን ለውጦታል። የጠፉትን ለማዳን በሆነው ተልዕኮ ውስጥ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን በፈቃዳቸው ታዘው ለጥሪው ምላሽ ሰጥተውታል።

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**:

1. ኢየሱስ የጠፋውን ለማዳን መጣ፡፡ የእርሱ ተልእኮ የእኔም ተልእኮ እንዲሆን ምን ማድረድ ይኖርብኛል? ______________________________

   ______________________________

2. እኔም ተሰብስቦ ከሚያጉረመርመው ሕዝብ ጋር ሆኜ ማጉረምረም ይሻለኛል ወይንስ የኃጢአተኞች እንግዳ የሆነውን ኢየሱስ ወደቤት ማስገባት? የጠፋውን ለማዳን ኢየሱስ ዛሬስ ማን ቤት ይሆን የሚሄደው? ______________________________

   ______________________________

3. ኢየሱስ የሚፈልጋቸው ሰዎች የት ይሆን የሚገኙት ? በእስር ቤት ውስጥ ይሆን? የወሊድ ችግር ገጥሟቸው በህክምና መስጫ ጣቢያ ውስጥ ወደሚገኙ ሰዎች ይሆንን? ወይንስ መኖሪያ ተቸግረው በጎዳና ላይ ይሆን የሚገኙት? ጎረቤቶቼ ይሆኑ? ወይንስ በእኔው ቤት የሚገኙ ሰዎች ይሆኑ? እነዚህን ሰዎች ለማግኘት እኔን ምን ያህል እየተጠቀመብኝ ይሆን?

   ______________________________

4. እነዚህን ሰዎች እንዳገኛቸው የሚረዳኝ ማነው?______________________________

   ______________________________

**ፀሎት**

በሾላው ዛፍ ላይ ወይንም ደግሞ በሌላ ስፍራ አግኝቶህ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛል ያለህን ኢየሱስን የምታዋራበት ጊዜ ነው፡፡ የሚከተሉትን ሃሳቦች ለእርሱ ማካፈል መምረጥ ትችላለህ፡

- ጌታ ሆይ አንተ ማን እንደሆንክ እንዳላውቅ መንፈሳዊ እይታዬን የጋረደብኝን ዙሪያዩን የከበበኝን ነገር አሳየኝ፡፡
- ከአንተ ጋር ሆኜ ያለፈውን የጥፋት ዘመኔን መልካም በማድረግ እንዳካክሰው አንተ እኔን ይቅር እንዳልከኝ እኔም ሌሎችን ይቅር እላቸው ዘንድ  እርዳኝ፡፡
- እኔ በራሴ እንዴት አድርጌ የምስራቹን ልሰማ እችላለሁ እባክህ አንተ ወደ ቤቴ መጥተህ ንገረኝ! ጌታ ሆይ የጠፉትን የሚፈለገውን ያንተን ሩህሩህ ልብ ስጠኝ፡፡ አንተን በማወቅ የሚድኑበትን መንገድ አሳያቸው ዘንድ የት እንዳሉ ማየት እንድችል የአንተን አይኖች ስጠኝ፡፡ ____________

# ትምህርት አራት

# ዘሪው

## የማርቆስ ወንጌል 4:1-8 — ዘሪው፤ አፈሩ ፤ እና ዘሩ

---

**የትምህርት አራት ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 4: የማርቆስ ወንጌል 4:1-20 ፣የማቴዎስ ወንጌል 13:1-23፣ የሉቃስ ወንጌል 8:4-15)

- ምስሎች እና ምሳሌዎች
- ምሳሌዎች: ዘሪው፣ አፈሩ፣ እና ዘሩ
- የመንግስተ ሰማይ ምስጢር
- የአፈሩ ጠባይ
- ዘሪው

***መግቢያ***

ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ምሳሌነት ያላቸውን ታሪኮች ይናገራል፡፡ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊ እውነቶችን ሲያስተምር ሰዎች በቅርባቸው በሚያውቋቸው እና በቀላሉ በሚረዷቸው ነገሮች በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህ ታሪኮች *ምሳሌዎች* ይባላሉ፡፡ ኢየሱስ ካስተማረባቸው ምሳሌዎች መካከል ሶስቱ በዚህ የጥናት ክፍል ተካትተዋል፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ዘር ሊዘራ የወጣው የዘሪው ምሳሌ ነው፡፡ የዚህ ትምህርት ዋናው ሃሳብ ያለው ዘሩ በሚወድቅበት (በሚዘራበት) የመሬት አይነት ላይ ነው፡፡ የመልእክቱ ኃይለ ቃል ያለው “ጆሮ ያለው ይስማ !” በሚሉት የኢየሱስ ቃላት ላይ ነው፡፡

ይህ ታሪክ በማቴዎስ 13፣በማርቆስ 4፣ እና በሉቃስ 8 ውስጥ ተዘግቦ እንደሚገኝ ልብ በሉ፡፡ በሶስቱም ወንጌላት ውስጥ የተጠቀሱትን የዚህን ታሪክ ክፍሎች ማየቱ ተጨማሪ ትርጉምና መረዳት እንድናገኝ ይረዳናል፡፡ በዚህ ጥናት ማርቆስ 4፡1-20 ማዕከላዊ የጥናታችን ክፍል አድርገን እንቀጥላለን፡፡

## ትምህርት 4

**ምዕራፍ 1**

**ትምህርት**:

በትምህርት 1 እና 2 ውስጥ ኢየሱስ ስዕላዊ አገላገጦችን በመጠቀም መንፈሳዊ እውነቶችን ያስተምር እንደነበር ተመልክተናል፡፡ ከኒቆዲሞስ ጋር በነበረው የትምህርት ጊዜ መወለድን፣ ንፋስ፣ እና ውሃን በምሳሌነት ተጠቅሟል፡፡ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ሲነጋገር ደግሞ ውሃን በምሳሌነት ተጠቅሟል፡፡ እንደ መወለድ ፣ነፋስ፣እና ውሃ የመሳሰሉት ክስተቶች ከሰዎች እለታዊ ህይወት ጋር የተቆራኙ ነገሮች በመሆናቸው ኢየሱስ የሚያስተምረውን ትምህርት በቀላሉ እንዲረዱ ያስችላቸዋል፡፡ በማቴዎስ 13፡34 ላይ ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ በነቢዩም፡- በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም፡፡ በማቴዎስ 13:34 "ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ በነቢዩም፡፡ በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም፡፡" ኢየሱስም ______________________ ይህን ሁሉ ______________________ ተናገረ፤ በነቢዩም፡፡ ______________________ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ______________________ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም፡፡ በ 35ኛው ቁጥር ዳዊት በመዝሙሩ የተናገረውን ትንቢት በዚህ ክፍል ፍፃሜውን እንዳገኘ ይገልፃል፡ "______________

______________________________________________________________

______________________________________________________ (መዝሙር 78:2)፡፡"

### መግቢያ

ከትምህርት 4 እስከ 6 ባለው ክፍል ኢየሱስ ካስተማረባቸው ብዙ ምሳሌዎች መካከል ሶስቱን ትኩረት ሰጥተን እንማራቸዋለን፡፡ ምሳሌዎች አንድን ሃሳብ ልናስረዳ የምንጠቀምባቸው ታሪኮች ናቸው፡፡ ኢየሱስ የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች የእለት ተእለት ኑሮአችን ውስጥ የሚገጥሙንን ነገሮች በመጠቀም ያስተማረባቸው ታሪኮች ናቸው፡፡ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊ እውነታዎችን በእነዚህ ምሳሌዎች አማካኝነት አስተምሯል፡፡ ከወንጌላት መካከል በዩሐንስ ወንጌል ውስጥ ምንም አይነት ምሳሌ አለመጠቀሱ አስገራሚ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ ማን መሆኑን እኔ በሚል ሁሉም በሚያውቀው ቃል ነበር ማንነቱን እየገለጠ ያስተማረው፡፡ እስቲ **እኔ** በማለት ያስተማረባቸውን ክፍሎች በክለሳ መልክ ተመልከቱ፡፡ ምን አይነት ምሳሌዎችን ነበር የተጠቀመው?

| ክፍሉ | የተሰጠው ምስል | “እኔ” የሚለው ንግግር |
|---|---|---|
| ዮሐንስ 6:35, 48, 51 | | |
| ዮሐንስ 8:12 | | |
| ዮሐንስ 10:7 | | |
| ዮሐንስ 10:11 | | |
| ዮሐንስ 11:25 | | |
| ዮሐንስ 15:1 | | |

**የቤት ስራ**: እስቲ ከማቴዎስ 13 ብዙ ምሳሌያዊ ታሪኮችን እንመልከት፡፡

***መልመጃ***:

1. የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንብቧቸው፡፡ ኢየሱስ ህዝቡን ለመድረስ የተጠቀመባቸውን ምስሎች ለይታችሁ ተመልከቷቸው፡፡ ሁሉንም ምለሳሌዎች ስትመለከቱ እንደዚህ በሚል ቃል ነበር የሚጀምራቸው “____________________________________”

    ሀ. ማቴዎስ 13:24-30 — ምስል: ______________________________

    ለ. ማቴዎስ 13:31-32 — ምስል: ______________________________

    ሐ. ማቴዎስ 13:44-45 — ምስል: ______________________________

    መ. ማቴዎስ 13:47-52 — ምስል: ______________________________

2. ምሳሌዎች ስነምግባራዊ ወይንም መንፈሳዊ እውነታዎችን የያዙ ናቸው፡፡ እስቲ እያንዳንዱን ምሳሌዎች በድጋሚ አንብባችሁ ኢየሱስ በእነዚያ ምሳሌዎች ውስጥ ያስተላለፋቸውን እውነቶች ለይታችሁ አውጧቸው፡፡ አስቸጋሪ ከሆነባችሁ ቀጥሎ ወዳለው ክፍል እለፉ፡፡ ፈፅሞ አይተዋችሁም!

    ሀ. ቁጥር 24-30 — እውነታው: ______________________________

    ለ. ቁጥር 31-32 — እውነታው: ______________________________

ሐ. ቁጥር 44-45 — እውነታው: ______________________________________________

መ. ቁጥር 47-52 — እውነታው: ______________________________________________

**ቅኝት**: በሚቀጥሉት ሶስት ምሳሌዎች ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች እንመለከታለን፡

1. እነዚህን ምሳሌዎች የራሳችንን ትርጉም ሳንሰጣቸው ኢየሱስ በተናገረበት መንፈስ ብቻ እንመልከታቸው።
2. በአይሁዳውያንና፣ በፍልስጥኤማውያን ዘንድ የተለመዱ ነገሮችን ለይታችሁ እወቁ፤ በመጨረሻም
3. በህይወታችን ልንተገብራቸው የሚገቡትን እውነቶችን ከምሳሌዎቹ ውስጥ እንፈልግ።

<u>ምዕራፍ 2</u>

**የቤት ስራ**: ማርቆስ 4:1-8 አንብቡ። በተጨማሪም በማቴዎስ 13:1-9 እና ሉቃስ 8:4-8 ውስጥ የሚገኙትን ምሳሌዎችም ተመልከቷቸው። እነዚህን ክፍሎች ፈለጋችሁ ለዚህ ጥናት እንዲረዷችሁ አንብቧቸው።

- ኢየሱስ የት ነው ያለው?
- እነዚህን ምሳሌዎች ለማን ነበር የተናገራቸው?
- ኢየሱስ በዚህ አርሶ አደር በሆነ ህዝብ መካከል የተጠቀመው ቀላል እና ሰዎቹ ሊረዱት የሚችሉት ምሳሌ በእለት ተእለት ህይወታቸው የሚጠቀሙበት ነገር ምን ነበር?
- ምን ነበር የታሪኩ ፍፃሜ?
- በማቴዎስ እና በሉቃስ ወንጌላት መካከል ባቱት ታሪኮች መካከል ያን ያህል ልዩነት ያለው ነገር አስተዋላችሁ ይሆን?

**መልመጃ**

1. ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ተቀምጦ ነበር (ማቴዎስ 13:1)። ትእይንቱ ተለወጠ፣ፀጥ ካለው የባሕር ዳርቻ በማርቆስ 4፡1 መሰረት ምን አይነት ሁኔታ እናገኛለን? ____________________

   ________________________________________________________________

2. ሕዝቡን ለማገልገል እንዲመቸው ኢየሱስ ወደ ታንኳ ውስጥ ገባ።ሕዝቡም በባሕሩ ዳርቻ ተከማቸ። በቁጥር 2 መሰረት ኢየሱስ ምን እያለ ያስተምራቸው ጀመር? __________________
3. ሕዝቡንም በምሳሌ ያስተምራቸው ጀመር (ቁጥር 2)። ማርቆስ ከእነዚህ ምሳሌዎች መካክል አንዱን መዘገብ ችሏል።

   ሀ. በምሳሌው ውስጥ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ገፀ ባህሪይ ማነው (ቁጥር 3)? ________

   ለ. ምን ነበር ያደረገው? ________________________________________________

*ማስታወሻ* በዚያን ዘመን የነበረው አሁንም በእኛ ሃገር እንደሚደረገው ገበሬው በትከሻው ላይ ካነገተው ኮሮጆ ወይንም ከረጢት ውስጥ በእጆቹ እየዘገነ የታረሰው መሬት ላይ እየመጠነ በመበተን ነው ዘሩን የሚዘራው። ሲዘራ ጥሩ ምርት እንዲያገኝ በጥንቃቄ መዝራ ይኖርበታል ምንም እንኳን በጥንቃቄ ቢዘራ እህሉን ግን በእጁ እየዘገነ ሳይሰስት ይበትነዋል።

4. ገበሬው ሲዘራ ዘሩ በምን ላይ ወደቀ (ቁጥር 4)? ______________________
______________________________________________
5. በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር ምን ሆነ ? ______________________
6. ሌላው ዘር የት ወደቀ (ቁጥር 5)? ______________________
   ሀ. ዘሩ በቂ አፈር በሌለበት በጭንጫ መሬት ላይ የመውደቁ ችግር ምን ነበር (ቁጥር 5)?
   ______________________________________________
   ለ. በጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ምን ሆነ (ቁጥር 5-6)? ______________________
   ______________________________________________
   ሐ. ቡቃያው ምን ገጠመው (ቁጥር 6)? ______________________
7. ሌሎቹ ዘሮችስ የት ወደቁ (ቁጥር 7)? ______________________
   ሀ. በዚህ ወቅት የገጠመው ችግር ምን ነበር? ______________________
   ለ. ቡቃያው ምን ገጠመው? ______________________
8. በመጨረሻም የቀረው ዘር በምን ላይ ወደቀ (ቁጥር 8)? ______________________
   ሀ. ውጤቱስ ምን ነበር?
      i. ______________________
      ii. ______________________
      iii. ______________________
   ለ. የምርቱ መጠን ምን ያህል ነበር (ቁጥር 8)? ______________________
   ______________________________________________
9. ኢየሱስ ታሪኩን በምን ደመደመው (ቁጥር 9)? ______________________
______________________________________________

**ቅኝት**:

1. ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ተቀምጦ ነበር። ከዚያም ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ እርሱ ቀረበ እርሱም ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ያስተምራቸው ጀመር። በታንኳይቱ እና በሕዝቡ መካከል ያለው ውሃ ድምፁን ለሕዝቡ እንዲሰማ ይበልጥ ያጎላው ነበር። ምናልባት ባሕር አካባቢ የምትኖሩ ከሆነ ይህንን ነገር ልታስተውሉ ትችላላችሁ። ውሃ በተፈጥሮው ድምፅን የመዋጥ ባህሪይ ስለሌለው በላዩ ላይ የሚያርፈውን ድምፅ በማንጠር እርቀት እንዲጓዝ ያደርገዋል።

2. ምናልባት ኢየሱስ በባሕሩ ዳር ቀድሞ በመድረስ በዙሪያው ለሚሰበሰበው ሕዝብ የሚያስተምረውን ነገር እያዘጋጀ ሊሆን ይችላል። ምናልባት በዙሪያው የሚሰበሰቡትን ሰዎች እየጠበቀ ይሆን? ከዚያ ቀን በፊት እንደዚሁ አስደሳች የትምህርት ቀን አሳልፎ ይሆን? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ፃፉ : ______________________________________

______________________________________________________________

3. ኢየሱስ የተናገረው ታሪክ ግልፅና ለመረዳት ቀላል ነበረ። ዘሪ ዘርን ሊዘራ ወጣ። አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፣አንዳንዱ ደግሞ ጥልቀት የሌለው አፈር ባለበት ቋጥኝ ላይ ወደቀ፤ መብቀልም ጀመረ ነገር ግን ስር መስደድ ስላልቻለ የቀኑ ሙቀት ባገኘው ጊዜ ወዲያው ጠወለገ፣ሌላው ደግሞ በእሾህ መካከል ወደቀ ሾሁም ወጣና አነቀው። ሌላው ዘር ደግሞ በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፣በታረሰ መሬት ላይ ወደቀ ብዙ ፍሬም አፈራ። ይህንን ታሪክ የሚሰሙ ታዳሚዎች በሙሉ ኢየሱስ የተናገረው ይህ ምሳሌ አንድ ገበሬ በማሳው ላይ ሲዘራ የሚያጋጥሙት ክስተቶች እንደሆኑ ያውቃሉ።

4. ታዲያ ለምን ነበር ኢየሱስ ይህንን ታሪክ ሊናገር የፈለገው ? ኢየሱስ ይህንን ትምህርት ሲያስተምር እናንተ በሕዝቡ መካከል ተገኝታችሁ እየሰማችሁ ቢሆን ኖሮ ትምህርቱን ስትሰሙ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድነው? ምናልባት እንደዚህ ልታስቡ ትችላላችሁ… “ ትምህርቱ ተራ ሆኖባችሁ ይህን ሁሉ መንገድ መጥቼ ስለማውቀው ግብርና ያስተምረኛል እንዴ ብላችሁ ከጠበቃችሁት በታች ሊሆንባችሁ ይችላል። ስለዚህ “መልካም ነው ኢየሱስ! ሌላም እስቲ ሌላ የተሻለ ነገር ንገረን” ልትሉት ትችላላችሁ። እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ፃፉት:

______________________________________________________________

5. ኢየሱስ ትምህርቱን እንደዚህ በማለት ደመደመ “የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።” ይህ አንድ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ያስተማረውን ትምህርት ጥልቅ ነገር የያዘ ዓረፍተ ነገር ነው። ይህ ነው ኢየሱስ ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት። ቁሳዊው (የሥጋ) ጆሮአችን የሚሰማው ቁሳዊውን ድምፅ ነው፣ መንፈሳዊው የልባችን ጆሮ ግን የሚናፍቀው ጥልቅ የሆኑትን መንፈሳዊ ነገሮች ለመስማት ነው። በብሉይ ኪዳን ቋንቋ “*መስማት*” ማለት “*መታዘዝንም* ” የሚያጠቃልል ቃል ነው።

## ምዕራፍ 3

**የቤት ስራ**: ማርቆስ 4:10-12 ፣ ማቴዎስ 13:10-17፣ እና ሉቃስ 8:9-10 አንብቡ፡፡

**መልመጃ**:

1. ደቀመዛሙርቱ እና ሕዝቡ ለመሆኑ በኢየሱስ ዙሪያ የተሰበሰቡት ምን ለማወቅ ፈልገው ነው (ማርቆስ 4:10)? ______________________________________________

______________________________________________
2. ደቀመዛሙርቱ በማቴዎስ 13:10 ምን ነበር የጠየቁት? ______________________

______________________________________________
3. በሉቃስ 8:9 ምን ነበር ደቀመዛሙርቱ ማወቅ የፈለጉት? ______________________

## ትምህርት

ሶስቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያመለክቱት "የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር" ነው፡፡ እነዚህን ቃላቶች ፈልጋችሁ አስምሩባቸው፡፡ ኢየሱስ በዚህ ትምህርት ውስጥ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት እርሱን የሚከተሉ እና ትምህርቱን በጉጉት የሚሰሙ በጅምላው ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማይገቡ ነው፡፡ ትምህርቱን የሚሰሙት በተለያየ ምክንያት ነበር፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል በየሄደበት እየተከተሉ ትምህርቱን የሚቃወሙና የሚተቹ ሰዎች ይገኙበታል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር ለካ ለሁሉም ሰዎች የተገለጠ አይደለም፡፡ ምስጢር ያሰኘው ይህ ባሕሪው አይመስላችሁም? ኢየሱስ የመንግሥተ ሰማያት ምስጢር በዚህ ምሳሌ ውስጥ እንዳለ እየነገራቸው ይመስላል፡፡ የኢየሱስን ትምህርት ያደምጡ የነበሩት ስለዚህ ምስጢር መማር ከፈለጉ የልቦናቸውን ጆሮች ከፍተው መስማት ይኖርባቸዋል፡፡ ኢየሱስ ለማስተማር ሁልጊዜ ዝግጁ ነው፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር ለሁሉም ሳይሆን የልባቸውን ጆሮች ከፍተው ሁልጊዜ ጓጉተው ይህንን ትምህርት ለሚከታተሉት ነው፡፡

## መልመጃ

ኢየሱስ የምሳሌውን ትርጉም በዙሪያው ለተሰበሰቡት ይነግራቸው ጀመር፡፡ ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ሲያብራራ ከሕዝቡ መካከል እንዳላችሁ እራሳችሁን አስቡ፡፡

1. ገበሬው ዘሩን ዘራ፡፡ ዘሩ ምን ነበር (ማርቆስ 4:14)? ______________________
2. እስቲ ይህ ምሳሌ የሚገኝባቸው ወንጌላት ስለ ተለያዩት የአፈር አይነቶች እና በዘሩ ላይ ምን እንደተከናወነ የፃፉትን ለይታችሁ አስቀምጡ፡

ሀ. ማቴዎስ 13

| | |
|---|---|
| አፈር አንድ መንገድ ዳር | ቁጥር 19: |
| አፈር ሁለት ቋጥኝ | ቁጥር 20-21: |
| አፈር ሶስት እሾሃማ | ቁጥር 22: |
| አፈር አራት መልካም | ቁጥር 23: |

ለ. ማርቆስ 4

| | |
|---|---|
| አፈር አንድ መንገድ ዳር | ቁጥር 15: |
| አፈር ሁለት ቋጥኝ | ቁጥር 16-17: |
| አፈር ሶስት እእሾሃማ | ቁጥር18-19: |
| አፈር አራት መልካም | ቁጥር 20: |

ሐ. ሉቃስ 8

| | |
|---|---|
| አፈር አንድ መንገድ ዳር | ቁጥር 12: |
| አፈር ሁለት ቋጥኝ | ቁጥር |
| አፈር ሶስት እሾሃማ | ቁጥር 14: |
| አፈር አራት መልካም | ቁጥር 15: |

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**:

1. የራሴን ልብ ፣የልቤን ጆሮ ከዚህ ቃል ጋር ሳነፃፅረው የእኔ ልብ የትኛውን አፈር ይመስላል?

   ______________________________________________

2. ዘሩ (የእግዚአብሔር ቃል) ስር ሰድዶ ለማደግ አፈር (ልብ) ይፈልጋል፡፡ ዘሩን ለመቀበል አፈሩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የጌታ መንፈስ ከአንተ ጋር እንደሆኑ ልባችሁን ለቃሉ የተዘጋጀ እንዲሆን አድርጎ ሲሰራ ያስተዋላችሁበት ጊዜ ይኖራል? ____________________

   ______________________________________________

3. ልባችሁን ለእግዚአብሔር ቃል የደነደነ እና ጠባብ የሚያደርጉባችሁ ነገሮች ምንድናቸው? ቃሉን በልባችሁ ውስጥ የሚያንቅባችሁ ምንድነው? ____________________

   ______________________________________________

<u>**ምዕራፍ 4**</u>

**ማጠቃለያ**

ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ውስጥ የአፈሩ አይነት የምርቱን መጠን እንደሚወስነው መልእክትን አስተላልፏል፡፡ በሉቃስ 8፡12 በመንገድ ዳር የወደቁት ዘሮች ድጋሚ የመብቀል እድል የላቸውም ምክንያቱም “ከዚህ በኋላም ____________ ይመጣል ____________ ____________ ቃሉን ____________ ይወስዳል፡፡”

ስለ ሁለተኛው የአፈር አይነት ሲነግረን ደግሞ እነዚህን አይነት ሰዎች ቃሉን በደስታ የሚሰሙ አይነት ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከበቀለ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ስር ስላልሰደደ ለእድገት የሚያስፈልገውን ነገር ማግኘት አይችልም፡፡ ስለዚህ ብዙም ሳይቆይ ጠውልጎ ይደርቃል፡፡ ይህንን ሁኔታ ማቴዎስ እንደዚህ በማለት ገልፆታል “ነገር ግን ____________እንጂ በእርሱ ____________የለውም፥ በቃሉ ምክንያትም ____________ ወይም ____________ በሆነ ጊዜ ወዲያው ____________ (ማቴዎስ 13:21)፡፡

ሶስተኛው የአፈር አይነት ደግሞ ዘሩን (ቃሉን) ይቀበላል ነገር ግን በላዩ ላይ እሾህ ይወጣና ያንቀዋል፡፡ የ______________ና የ______________ ______________ የ____________ገብተው ቃሉን __________፥ __________ ይሆናል (ማርቆስ 4:19)፡፡

በመጨረሻም መልካሙ የአፈር አይነት! ሉቃስ ይህን ሁኔታ በቁጥር 15 እንደዚህ በማለት ይገልፅልናል፡ በመልካም መሬት ላይም የወደቀ እነርሱ ____________ና ____________ ልብ ቃሉን

ሰምተው _______________ በ_______________ ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው። የተሰጣቸው ተስፋ ይህ ነው!

***ትምህርት***

በዚህ የማጠቃለያ ክፍል ኢየሱስ እየተናገራቸው ያሉትን ሰዎች እነማን እንደሆኑ በልባችሁ ያዙ። በዚህ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም አይነት የልብ አይነቶች እንደገለጣቸው እናስባለን። በማቴዎስ 13፡10 ላይ ደቀመዛሙርቱ ለምን በምሳሌ እንደሚናገር ጠይቀውት ነበር። በሉቃስ 8፡9 ላይ የምሳሌውን ትርጉም እንዲነግራቸው ሲጠይቁት እንመለከታለን። የተሰወረውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር ለማወቅ ጓጉተው ነበር። ለዚህ ነው መልካም መሬት የሚፈለገው። ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት እነዚህ ናቸው። ቃሉን ሰምቶ የሚቀበል እንደዚህ አይነት ልብ ነው። ቃሉን ሰምቶ የሚታዘዘው እንደዚህ አይነት ልብ ነው።

በማቴዎስ 13፡16 በዙሪያው ለተሰበሰቡት ኢየሱስ እንደዚህ አላቸው "የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ ብፁዓን ናቸው።" የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር በዓይናቸው ፊት ነው። የእግዚአብሔርን መንግስት በፊታቸው እያገለገለ የነበረው ኢየሱስ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ኢየሱስን ፣ለዓለም ሁሉ ተስፋ የተገባውን መሲሁን ለማየት ብዙ ነቢያቶች እና ፃድቃን ተመኝተው ነበር ነገር ግን ሊያዩት እድል አላገኙም ነበር።

አሁን ወደ ምሳሌው ዝርዝር ፍቺ እንመለስ። በሉቃስ 8፡11 የተነገረን የዘሪው ምሳሌ ምንድነው? ሶስቱም የወንጌል ክፍሎች ስለዚህ ምሳሌ አንድ አይነት ነገር ነው የተናገሩት። ቀጥሎ በምናየው በዩሐንስ 1፡1-2 ባለው ክፍል ውስጥ ዘሩ ________________ነው። በዚህ ክፍል በመጀመሪያው ቃል እንደነበረ እናያልን በዩሐንስ 1፡14 እንደዚህ ይላል "__________ሆነ፤_________ና___________ተመልቶ በእኛ አደረ…።

"ቃል" በእግዚአብሔር የተነገረን "ቃል" ማለት ነው፤ ዮሐንስ ግን ኢየሱስ "ቃል" ነው ይለናል። ገበሬው ዘሩን ይዞ ወጥቶ ዘራ፣ ዘሩም በተለያዩ አይነት መሬቶች ላይ ወደቀ። ኢየሱስ እርሱን እንዴት የተለያዩ ልቦች እንደተቀበሉት በዚህ ምሳሌ ተናገረ። ከክፉው የተነሳ በብዙዎች ልብ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። በሌሎች ልብ ደግሞ በቶሎ ተቀባይነትን አገኘ፤ ነገር ግን በልባቸው ስፍራን አግኝቶ አልቆየም። እርሱን መከተል ዋጋ እንደሚያስከፍል ሲረዱ ወዲያውኑ ፊታቸውን ከእርሱ አዞሩ። ሌሎች ደግሞ በገንዘብ ፍቅር ፣በብልፅግና፣ እና በዚህ ዓለም ነገር ስለራሳቸው በመጨነቃቸው ምክንያት ሊያስተናግዱት አለቻሉም። ነገር ግን ኢየሱስን በመቀበል የእግዚአብሔርን መንግሥት ጉዳይ ወደ ልባቸው ያስገቡ ሰዎች ህይወታቸው የሚያተርፍ ሆነ መቶ፣ ስልሳም ፣ሰላሳም አፈሩ!

***ከህይወት ጋር ማዛመድ ጥያቄዎች***: በዚህ ምሳሌ ውስጥ እራሳችሁን የትኛው ምሳሌ ውስጥ አገኛችሁት? *ሥጋ* የሆነው ቃል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር የሆነውን፣ የእግዚአብሔርን ቃል

ምስጢር የሚያካፍላችሁን ኢየሱስን በህይወታችሁ በደስታ ተቀብላችሁታል? እስቲ ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁን ሃሳብ አካፍሉ: ______________________________________

______________________________________________________________

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ ልቤን ቃልህ ተቀብሎ የሚያፈራ ይሆን ዘንድ እንደ መልካሙ መሬት አድርግልኝ። ክፉውን ከእኔ አርቅልኝ። እምነቴ ስር ሰዶ ከአንተ ጋር ፀንቼ መኖር እችል ዘንድ እርዳኝ ። ስለአንተ ያለኝን መረዳት ሊነጥቁኝ ከሚፈልጉ ሁሉ ትጠብቀኝ ዘንድ ምንም ነገር አንተን ከማወቅ የበለጠ ዋጋ እንዳልሰጠው ጠብቀኝ። የመንግስትህንም ምስጢር እለት እለት በህይወቴ ትገልጥልኝ ዘንድ ከዚህም የተነሳ ለአንተ ክብርን የሚሰጥ እንደዚሁም ቅዱስ ስምህን የሚያከብር ፍሬ አፈራ ዘንድ እርዳኝ። _____

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## <u>ምዕራፍ 5</u>

**መግቢያ**

ይህንን የጥናት ክፍል ከማጠናቀቃችን በፊት ከእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ ማየት የሚገባንን ትልቅ ነጥብ እንመለከታለን። ጥያቄው፦ ገበሬው ማነው የሚል ነው? እስካሁን ባሉት ክፍሎች ስለመሬቱ ፣ስለዘሩ ተነግሮናል ስለገበሬው ግን ምንም የተባለ ነገር የለም ማንነቱም አልተገለፀልንም። ስለዚህ ጉዳይ የሚናገሩ የወንጌል ክፍሎች በሙሉ “ዘሪው ሊዘራ ወጣ” ብለው ነው የሚጀምሩት። በማርቆስ 4 ላይ “ዘሪው ቃሉን ይዘራል” የሚል ቃል ተፅፎ እናገኛለን።

**ገለፃ**

እስቲ ለአፍታ እራሳችሁን ለአፍታ መቶ፣ስልሳና ፣ሰላሳ እንዲያፈራለት አስቦ እንደዘራው ገበሬ አድርጋችሁ አስቡ ።

1. የዘራችሁበት መሬት የትኛው ነው? ______________________________

   ______________________________________________________

2. የዘራችሁት ምንድነው? ______________________________________

   ______________________________________________________

3. ከዘራችሁት ዘር ምን ትጠብቃላችሁ? ______________________________

   ______________________________________________________

4. የተትረፈረፈ ምርት እንድታገኙ ሳትሰስቱ ነው የዘራችሁት? ____________________

   ______________________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**

እኔ እና እናንተ ገበሬዎች ከሆንን የኢየሱስን ቃል የምናካፍላቸው ሰዎች እነማን ናቸው? ከሰዎች ጋር ተቀላቅለን ይህንን እውነት እናካፍላቸዋለን ወይንስ ዘሩን ይዘን ብቻችንን ተቀምጠናል።

1. የቃሉን ዘር የማካፍለው የት ነው?______________________________________________
2. ዘሩን የት ነው የምዘራው፣ የኢየሱስን በልባችን ላይ የመንገስ ፍላጎት እውነትን የማካፍለው ለማን ነው? ______________________________________________________

   ________________________________________________________________
3. እኔ ገበሬ ብሆን ዘሩን ያለስስት እዘራለሁ ወይንስ በስስት እና በቁጠባ ነው የምዘራው? ዘሩን ስዘራ በመንገድ ዳር ይወድቅብኛል ወይንም በጭንጫ ላይ የሚለው ፍርሃት በብዛትና በስፋት እንዳልዘራ ያደርገኝ ይሆን? ምንድነው ማድረግ ያለብኝ? ________________________________

   ከዚህ በተለየ ማድረግ የሚገባኝ ምንድነው? _____________________________________

   ________________________________________________________________
4. በከረጢት ውስጥ ያለውን የዘር አቅም ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቻለሁ? ይህንን ዘር በጎረቤቶቼ ላይ ፣በማህበረሰቤ ውስጥ፣በእኔ ዙሪያ ባሉት ጓደኞቼ ላይ፣መልካም መሬት ባገኘሁበት ስፍራ ሁሉ ስዘራ የመንፈስ ቅዱስ ደርሻ የሚሆነው ምንድነው? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለፁ:

   ________________________________________________________________

**ማሰላሰል**

እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ፍሬን ወይንም ምርትን ተስፋ ሰጥቶናል! አሁን የሚያስፈልጉት በደስታ ወጥተው የሚዘሩ ገበሬዎች ናቸው። ለዚህ የትምህርት ክፍል የምናሰላስለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በኢሳያስ 55:10-11 ላይ ያለው ቃል ነው። ከዚህ ቀደም አንብባችሁት የምታውቁ ከሆነ እንደ ክለሳ ይሁንላችሁ። አንብባችሁት የማታውቁ ከሆነ ግን በደብተራችሁ ላይ በመፃፍ በዚህ የተስፋ ቃል ሃሴት አድርጉ፣ ተበረታቱበት፣ተስፋ ይሁንላችሁ፣ብዙ የምታፈሩበት የተስፋ ቃል ይሁንላችሁ ከዘራችሁት መቶ እጥፍ እንድታፈሩ ያድርጋችሁ! በነቢዩ ኢሳያስ እንደዚህ በማለት ይነግረናል፡ "____________________ና____________________ ከ____________________ እንደሚወርድ፥ ____________________፥ ____________________ና ____________________ ዘንድ እንደሚያደርጋት፥ ____________________ ለሚዘራ ____________________ ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ____________________፥ከአፌ የሚወጣ ____________________ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ____________________ የላክሁትንም ____________________ እንጂ ወደ እኔ __________________::"

**ፀሎት**

ጌታ ኢየሱስ ሆይ ወጥቶ ከመመስከር ይልቅ እነዚህን ምሳሌዎች ማንበብ በጣም ቀላል ነው፡፡ የተትረፈረፈውን ምርት የተስፋ ቃል ማመን ለእኔ አስቸጋሪ ነው፡፡ ቃልህን ለሁሉም መናገር ያለመቆጠብ ወይንም ያለስስት መዝራት አስቸጋሪ ሆኖብኛል፡፡ ምንም እንዳላወቅኩ እና ብዙ እንደሚቀረኝ አስባለሁ፡፡ የተስፋ ቃሎችህ ከእኔ ጋር እንዳሉ ማሰብ ባለመቻሌ እፈራለሁ፡፡ እንደላከኝ እያወኩ ነገር ግን በቤቴ ተቀምጫለሁ፡፡ እባክህ ዙሪያዬን ከከበቡኝ ፍርሃቶች እጅህ ነፃ ያውጣኝ፡፡ ሥጋ የሆንከው እና በመካከላችን ያደርከው ቃል ሁሉ ከአንተ፣በአንተ እና ለአንተ መሆኑን አስብ ዘንድ እርዳኝ!

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ትምህርት አምስት

# ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ

## ሉቃስ 10:25-37 — ደጉ ሳምራዊ

---

**ቅኝት 5**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 5: ሉቃስ 10:25-37

- ኢየሱስ እና ህግ አዋቂው
- ጎረቤቴ ማነው?
- ምሳሌ:- ደጉ ሳምራዊ
- ምህረት እና ርህራሄ
- ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ

***መግቢያ***

በቀጣዩ ምሳሌ ውስጥ ርህራሄን በተግባር እንመለከታለን፡፡ ክፍሉን በጥንቃቄ አንብቡ፡፡ ኢየሱስ በተናገረው ታሪክ ውስጥ ያለውን በወንበዴዎች ጉዳት የደረሰበትን ተጓዥ የረዳውን ሰው ልብ በሉ፡፡ የሰውየውን የድርጊቱን ምክንያት ልብ በሉ፡፡ ኢየሱስ "መምህር ሆይ የዘላለምን ህይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?" ብሎ የጠየቀውን ሰው በምን መልኩ እንዳስተናገደው ተመልከቱ፡፡ ሰውየው ሌላ ጥያቄ ቀጠለ "ጎረቤቴ ወይንም ባለእንጀራዬ ማነው?" እናንተስ እንደዚህ አይነት ጥያቄ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?

ኢየሱስ ሊፈትኑት የሚመጡትን ሰዎች ልብ ያውቅ ነበር፡፡ ልባቸው ህይወታቸው በአጠቃላይ በርህራሄና በምህረት የተሞሉትንም እንደዚሁ፡፡ በሰማይ ካለው አባቱ ጋር የሚኖር ግንኙነት ለሰው ልጅ ምን ያህል አስፈልጊ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ "አንተም ሄደህ እንዲሁ አድርግ" በማለት ከሰውየው ጋር የነበረውን ንግግር ፈፀመ፡፡ ምህረትን የሚያደርግ ሰው ምህረትን ይቀበላል (ማቴዎስ 5:7)፡፡

## ትምህርት 5

**ምዕራፍ 1**

### ትምህርት

ትምህርት 5 ለእግዚአብሔር እና ለሰው ስላለን ፍቅር የሚያስተምር ስለፍቅር የሚናገር ምሳሌ ነው። አክራሪ ለሆኑት አይሁዶች ዋናው ህጋቸው የሙሴ ህግ ተብለው የሚታወቁት አስርቱ ትእዛዛት፣ በሌዋውያን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ ህግጋት እንደዚሁም በአጠቃላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ በሆኑት አምስቱ የህግ መጻሕፍት እና በውስጣቸው የሚገኙ ህግጋት በአጠቃላይ ናቸው። እነዚህ የሙሴ ህግጋት እግዚአብሔር የአይሁድ ህዝቦች እንዲኖሩበት የሚፈልገውን ደንብ እና ስርአት የገለጠበት መለኮታዊ ህግ ነው። አንድ ሰው እነዚህን ህጎች ይበልጥ በጠበቀ መጠን በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ከበሬታ የዚያኑ ያህል እየጨመረ ይመጣል።

እንደምታስታውሱት ፈሪሳውያን የህጉ ሊቃውንት የሚባሉ የማህበረሰቡ ክፍሎች ናቸው። የህጉን አላማ በመሳታቸው ምክንያት ኢየሱስ ሁልጊዜ ከእነዚህ ሰዎች ተግዳሮት ይገጥመው ነበር። እግዚአብሔር ህግን የሰጠበትን ምክንያት በቅጡ የተረዱ አልነበሩም። ፍቅር ከሆነ አምላክ የተሰጠ መመሪያ ጎረቤቶቻችንን እንድንወድድ የሚያስተምር ህግ እንደሆነ ሳይሆን ራሳቸውን ለማስከበሪያነት ይጠቀሙበት ነበር። ኢየሱስ ፈሪሳዊያን በትዕቢታቸው ቀብረውት፣በአድርግ አታድርግ እስራት ተብትበውት የነበረውን የፍቅር ህግ በህይወት እና በትምህርቱ እየገለጠ ነበር ወደ አይሁድ የመጣው።

**የቤት ስራ**: ሉቃስ 10:25-28 አንብቡ።

- ማን ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው?
- ለምን ነበር የመጣው?
- ጥያቄው ምን ነበር?
- ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰለት?

**መልመጃ**:

1. ማን ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው (ቁጥር 25)? ________________________________

   እየሆነ ያለውን ነገር ጥርት ባለ ሁኔታ መመልከት እንችል ዘንድ በማቴዎስ 22:34-35 ምን ተነገረን? ____________________________________________________________

2. _____________ መጣ:: ሊፈትነው መጣ ይላል:: ይህ ህግ አዋቂ የኢየሱስን ትምህርት እንደዚሁም የእርሱን መሲህነት እንደዚሁ ሊያጣጥል ፈልጎ ሊፈትነው መጣ:: የእነርሱ ጥያቄ እና የኢየሱስን መልስ ስንመለከት አስገራሚ ነበር::
3. ወደ ሉቃስ 10 እንመለስ...በቁጥር 25 ላይ ህግ አዋቂው ኢየሱስን እንደዚህ በማለት ጠየቀው: ________________________________________________
4. ኢየሱስ የህግ አዋቂውን ጥያቄ በጥያቄ መለሰለት (ቁጥር 26):: ምን ነበር የመለሰለት? ________________________________________________
5. ህግ አዋቂው የሚነበበውን ህግ ወዲያው ነበር መመለስ የቻለው (ቁጥር 27): "እርሱም መልሶ፦ _____________በፍጹም _____________ በፍጹም _____________ በፍጹም _____________ በፍጹም _____________ ውደድ፥ _____________ እንደ ራስህ _____________አለው::(ዘዳግም 6:5), "ነገር ግን _____________እንደራስህ_____________"
6. ኢየሱስ እንደዚህ በማለት መለሰ(ቁጥር 28): ________________________________________________

**ገለፃ**

1. ከእነዚህ የህግ አዋቂዎች መካከል አንዱ ብትሆን በዚህን ሰአት በአእምሮህ የሚመላለሰው ነገር ምን ሊሆን ይችላል? ________________________________________________
2. የእነዚህ ፈሪሳውያን ጥያቄ አጠያየቅ ህግን መፈፀም ከቻለ አንድ ሰው ራሱን ማዳን ይችላል ብለው ያመኑ ይመስላል:: "የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድወርስ ምን ላድርግ?" ኢየሱስ ምን እንዲለው የፈለገ ይመስላችኋል? ________________________________________________
3. ኢየሱስ ምላሽ ሲሰጠው ስለጽድቁ የሚያመሰግነው መስሎት ጥያቄውን ቀጠለ:: ኢየሱስ ግን ህጉ ምን እንደሚል ጠየቀው:: በእርግጥ ይህ ሰው ህግ አዋቂ ነው:: የእነዚህ ሁለት የብሉይ ኪዳን ህጎች ፍፃሜ ምን ነበር? ________________________________________________

## <u>ምዕራፍ 2</u>

**ትምህርት**: በዘጸአት 20 የሚገኙት ህጎች አንዳንዴ በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ:: አንደኛው ክፍል የመጀመሪያዎቹን አራት ህጎች የያዘ ነው::

1. ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ::

2. በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ።አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም…
3. የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ
4. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።

እነዚህ አራት ህጎች የሚናገሩት______________ስለመውደድ ነው።

ቀሪዎቹ ስድስት ትእዛዛት ሁለተኛውን ክፍል ይይዛሉ፡

5. አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።
6. አትግደል
7. አታመንዝር
8. አትስረቅ
9. በሐሰት አትመስክር
10. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።

እነዚህ ስድስት ትእዛዛት የሚናገሩት ከ ____________________________ስላለን ፍቅር ነው።

**አስተያየት**:

1. ኢየሱስ ህግ አዋቂውን ለጥያቄው ትክክለኛ ምላሽ መስጠቱን አረጋግጦለታል ነገር ግን “አንተም ሂድና እንደዚሁ አድርግ በህይወት ትኖራለህ” ሲለው ትዕቢቱን ሊያስወግድለት የፈለገ ይመስላል።ማወቅና ማድረግ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ሰውየው ትክክለኛውን መልስ አውቋል ኢየሱስ ደግሞ ህጉ የሚጠይቀውን ሰውየው እንደማይፈፅም አውቋል። ሮሜ 3:20 የሚከተለውን ያስታውሰናል፡ “ይህም ________________ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ________________ ነው፤ ኃጢአት ________________ ይታወቃልና።”
2. ይህ ህግ አዋቂ አሁን ምን የሚሰማው ይመስላችኋል? ስለራሳችሁ ስታስቡ መልካም ከሆናችሁ፣የዘላለምን ህይወት እንደምታገኙ፣እንደምትድኑና፣ ወደ ገነት እንደምትገቡ አስባችሁ ታውቃላችሁ ? ____________________________________________________________

____________________________________________________________
3. ለዚህ ሃሳባችሁ ኢየሱስ ምን ብሎ የሚመልስላችሁ ይመስላችኋል? ____________________

____________________________________________________________

**የቤት ሥራ**: ሉቃስ 10:29-37 አንብቡ።

- የህግ አዋቂው ጥያቄ ምን ነበር?

- ኢየሱስ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ ገፀ - ባህሪያቶቹ እነማናቸው?
- ኢየሱስ ሰውየውን ምን አይነት ጥያቄ ጠየቀው?
- ለሰውየው ምን የሚል ቃል ነው የሰጠው?

***መልመጃ***

"አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ" የሚለው ቃል የሚጠቅስ ቃል ነው። ህግ የሚለውን ቢፈፅም በህይወት ይኖራል ነገር እውነታው ግን ህግን ለመፈፀም የሚታገለው ጎረቤቶቹን ሳይወድ ነው።

1. በቁጥር 28 ስንመለከት ይህ ሰው በኢየሱስ ንግግር አስቸጋሪ እንደሆነበት እንመለከታለን። በቁጥር 29 ላይ ስለዚህ ሰው የተነገረን ነገር ምንድነው? ______________________________
2. ሰውየው ህግን መፈፀሙ ብርታት እንደሆነው እንደሚያስብ ኢየሱስ አውቋል ።ኢየሱስ ግን ሰውየው የት ጋር እንደወደቀ አውቋል። ህግ አዋቂው የት ጋር ህግን መጠበቅ እንዳቃተው ገለጠ። ኢየሱስን ምን አይነት ጥያቄ ጠየቀው (ቁጥር 29)? ___________________________
3. ለዚህ ጥያቄው መልስ እንዲሆነው ኢየሱስ ____________________________ብሎ ነገረው።
4. ሰውየው ወዴት ነበር የሄደው (ቁጥር 30)? ______________________________________
   ኢየሩሳሌም በጽዮን ተራራ ላይ ነው የምትገኘው። ከኢየሩሳሌም እስከ ኢያሪኮ ድረስ ያለው መንገድ በደረጃ የሚወጣ ፣ሌቦች እና ቀማኞች የሚያደፍጡበት አስቸጋሪ መንገድ ነበረ።
5. በመንገዱ ሲሄድ ምን ገጠመው? ______________________________________________
6. ዘራፊዎቹ ምን አደረጉት? _________________________________________________
7. ዘራፊዎቹ ትተውት ሲሄዱ የነበረበት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ______________________
8. አንድ አዲስ ሰው በታሪኩ ውስጥ ተጨመረ (ቁጥር 31)። ያ ሰው ማን ነበር? ____________
9. በመንገዱ ላይ ሲመጣ ምን አይነት ሰው ነበር የገጠመው? ___________________________
   ______________________________________________________________________

***ትምህርት***:

ካህኑ በመንገዱ ላይ የገጠመውን ነገር አልገፎ ሲሄድ: "ማንም ሰው ከሕዝቡ ስለ ሞተው፥______________________________________________________________ (ሌዋውያን 21:1)።" የሚለውን ህግ እየተገበረ ነበር። በምሳሌው ውስጥ ያለው ካህን ሰውየውን እያየ ያለፈው በህጉ ላለመጠየቅ ነው። በሉቃስ 10:32 የሚገኘው ሌዋዊም እንደዚሁ ምን አደረገ ? ____________________ ሌዋውያን ለክህነት ስራ በእግዚአብሔር የተለዩ ሰዎች ናቸው። ከካህኑ የተለየ ምንም ነገር ሳያሳይ ሌዋዊውም እንደዚሁ የወደቀውን ሰው አልፎት ሄደ። ሁለቱም ሰዎች ተመሳሳይ ነገር ነበር ያደረጉት ቁስለኛውን እያዩ አልፈውት ሄዱ።

**<u>ምዕራፍ 3</u>**

**መልመጃ**:

1. በቁጥር 33 መሰረት ቀጥሎ በዚያ መንገድ ማን መጣ? ______________________________

   በትምህርት 2 አይሁዳውያን ለሳምራውያን የነበራቸውን ጥላቻ አስታውሱ። አይሁዳውያን ከማንም ጋር ያልተቀላቀሉ የአብርሃም ዘሮች ሲሆኑ ሳምራውያን ግን ምርኮውን ተከትሎ በምድራቸው ከሰፈሩት ባእድ ሕዝቦች ጋር ተጋብተዋል።

2. ሳምራዊው ሰው ምን አደረገ ?

   ሀ. ___________________________ወደ እርሱ _______________________(ቁጥር 33)።

   ለ. ሳምራዊው ሰው ይህንን ጉዳት የደረሰበትን ሰው ሲያየው ምን አረገ? ______________

   ሐ. ሰውየውን ለመርዳት ምን አደረገ (ቁጥር 34)?

   i. ____________________________________________________________

   ii. ____________________________________________________________

   iii. ____________________________________________________________

   iv. ____________________________________________________________

   መ. በዚህ ሁሉ ላይ ተጨማሪ ምን አደረገ 35?

   ______________________________________________________________________

   ሠ. ለሚጠብቁትስ ሰዎች ምን አላቸው? _____________________________________

   ______________________________________________________________________

**ገለፃ**

"አንድ ሳምራዊ ግን … ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥ (ቁጥር 33-34)።" እነዚህ ቃላቶች ትኩረታችንን ይሻሉ። ሰዎች ወዳሉበት ስፍራ መምጣት ቀላል ነገር አይደለም።ለምሳሌ ከእኛ አመለካከት ውጪ የሆነ ሰው ሲገጥመን ወደ እኛ አመለካከት ለማምጣት እንጥራለን። የአንድ ሰው አኗኗር አግባብነት የጎለው ኑሮ ከሆነ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲመጣ እናስገድደዋለን። የእኛስ ዝንባሌ እያዩ ካለፉት ካህን እና ሌዋዊ የተለየ ይሆን? ጓደኞችን በሱስ ሲጠቃ እንደ ካህኑ እና ሌዋውያኑ ዝም ብለን እናልፈው ይሆን፡ እርዳታን ፈልጎ በመንገድ ላይ የወደቀውን እዚያው ያለበት ስፍራ ካልሔድንለት እንዴት ነው የምንደርስለት? በርህራሄ አይን ካላየናቸው እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን? እነርሱ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ እራሳችንን ሳናስገባ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን? እስቲ በዚህ ነገር ያላችሁን አመለካከት ግለፁ፡

______________________________________________________________________

**መልመጃ**:

1. አሁን ኢየሱስ ታሪኩን ተናግሮ ጨርሷል። የህግ አዋቂውን የጠየቀው ጥያቄ ምን ነበር (ቁጥር 36)? ________________________________________________
2. ህግ አዋቂው እንደዚህ በማለት መለሰ (ቁጥር 37): ______________________
3. ኢየስስ እንዲህ አለው: ________________________________________

**ማጠቃለያ**

የደጉን ሳምራዊ ምሳሌ ቅኝት አሁን አጠናቀናል። ታሪኩ በአጭሩ አንድ ሰው በመንገድ ላይ ዘራፊዎች አግኝተው ክፉኛ ደብድበው ዘርፈው ጥለውት ሄዱ። ሁለት ሰዎች ተራ በተራ በዚያ መንገድ አለፉ የተጎዳውን ሰው ቢያዩትም ምንም ሳይረዱት አለፉ። በመጨረሻም አንድ ሳምራዊ በዚያ መንገድ ሲያልፍ ይህንን ሰው ተመለከተ፣ ለሰውየው አዘነለት፣ሰውየው በራሱ ማድረግ የማይችለውን ሁሉ አደረገለት፣ለሰውየውም እንክብካቤ ለሚያደርጉለት ሙሉውን ዋጋ ከፈለለት።

**ገለፃ**

(ቁጥር 25-37) በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ላይ የተረዳችሁትን ስታንፀባርቁ እናንተ እራሳችሁን የትኛው ጋር አገኛችሁት? ሕግ አዋቂው፣የተጎዳው ሰው ፣ወይንስ ካህኑ እና ሌዋዊው ?

1. እራሳችሁን ማን ጋር አገኛችሁት ህግ አዋቂው ጋር ይሆን? እግዚአብሔርን የተፈታተናችሁበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ ? እግዚአብሔርን ያለአግባብ ወይንም ያለመረዳት ስንት ጊዜ በቃሉ ልታጠምዱት ሞከራችሁ? እራሳችሁን ከሁሉ የበለጠ ጻድቅ አድርጋችሁ ያሰባችሁበት ጊዜ ይኖር ይሆን? ስንት ጊዜ ከእናንተ ጋር የሚኖሩትን ጎረቤቶቻችሁን ልትረዱ ልታግዙ ፈቅዳችኋል? በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ እና ነፀብራቅ አቅርቡ: ______________

   ________________________________________________

   ________________________________________________

2. ጉዳተኛውንስ ሰው እርሱን መስላችሁ ይሆን ? ምናልባት እንደእርሱ ተሰምቷችሁ ይሆን ? በኑሮ ተደቁሳችሁ በመንገድ ዳር ለሞት ወድቃችሁ ይሆን? ምናልባት በዚያን ወቅት ቤተ ክርስቲያን ትረዳኛለች ብላችሁ አስባችሁ ሊሆን ይችላል። የቅርብ ወዳጆቻችሁም ሊደርሱላችሁ ባለመቻላቸው በእነርሱ ላይ ያላችሁ ተስፋ ተሟጦ ሌላ የሚረዳችሁ፣መልካም የሚያደርግላችሁ እየጠበቃችሁ ሊሆን ይችላል። እስቲ በዚህ ነገር ላይ ያላችሁን አስተያየት ወይንም ሃሳብ ግለፁ:

   ________________________________________________

3. ምናልባት ሌዋዊውና ካህኑስ? ምናልባት እራሳችሁን እንደ እነዚህ ካህናት እና ሌዋዊ እራሳችሁን በእነርሱ ስፍራ አግኝታችሁ የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማችሁ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ምቾቶቻችሁን የሚነካባችሁ ሆኖ አግኝታችሁት ሌሎችን ከመርዳት እጃችሁን

ሰብስባችሁ ተቀምጣችሁ ሊሆን ይችላል። እንደ ቤተ ክርስቲያን አባልነታችሁ ፣ወይንም እንደ አገልጋይነታችሁ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ለመሳተፍ ጊዜ ሳትሰጡ ቀርታችሁ ሊሆን ይችላል፡ እስቲ በዚህም ላይ ያላችሁን አስተያየት ፃፉ፡ ________________________________

________________________________________________________________

**ምዕራፍ 4**

**ትምህርት**

ሳምራውያን አይሁዳውያንን አይሁዳውያን ደግሞ ሳምራውያንን ይጠሏቸው ነበር። ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ ሳምራዊው ለአይሁዳዊው ምህረት ሲያደርግለት እንመለከታለን። ለመሆኑ ምህረት ማለት ምን ማለት ነው ? ጎረቤቴ ማነው? ለሚለው ጥያቄ ይህን አይነት ግንኙነት ለምን በምሳሌ ሊያቀርብ ቻለ?

ምህረት የማያደርግ ሰው ምናልባት እንደዚህ ሊል ይችላል "የእጅህን ነው ያገኘኸው፣ እኔን አያገባኝም ፣ደንታዬ አይደለም፣አላውቅህም ስለዚህ ምንም ብትሆን ግድ የለኝም፣ በዚህ ላይ ጠላቴ ነህ።" ልክ ይህን አይነት ነገር ነበር ካህኑና ሌዋዊው በዚያ ሰው ላይ ያደረጉበት። በአይሁዳዊ ወንድማቸው ላይ ጭካኔ የተሞላበት ነገር ነው ነበር የፈፀሙት።

ሳምራዊው ግን ምህረትን አደረገለት። ምህረት እንደዚህ አይነት ክፉ ነገር ለአንተ አይገባህም ነበር፣እኔ መወደድ የምፈልገውን ያህል እወድሃለሁ፣ምህረት ወደ ኋላ ተመልሶ አቅም የሌለውን ተስፋ ቢሱን በርህራሔ ይደግፋል። በቁጥር 33 ላይ ሁለት ፈሪሳዊ እና አንድ ሳምራዊ ማየት በጣም አስገራሚ ነው። "አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ________________________አይቶትም አዘነለት ፥ ቀርቦም ________________________ አሰራቸው …" ሌሎች አይተው አለፉ ሳምራዊው ግን ወደ ወደቀበት ስፍራ መጣ። ምህረት በሌሎች ጫና ወይም በውለታ የሚደረግ ነገር አይደለም። ነገር ግን ምህረት ምንም ሳይፈልግ ምንም ሳይጠብቅ መልካምን ያደርጋል።

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**:

1. በህይወቴ ፍርድና ኩነኔ ሳይሆን ምህረት እና ርህራሔ በሚያስፈልገኝ ጊዜ ምህረት እና ርህራሔያቸውን ያሳዩኝ እነማን ናቸው? ________________________________

   ምህረት እና ርህራሔያቸውን ለእኔ ለማሳየት ምን ነበር ያደረጉት? ________

   ________________________________________________________________

2. እኔስ ለእነማን እንደ ደጉ ሳምራዊ ሆኜላቸዋለሁ? ለእነማን ይሆን ያሉበት አስቸጋሪ ስፍራ ድረስ በመሄድ ምህረት ያደረኩላቸው? ________________________________

   ________________________________________________________________

3. በየእለቱ ለሰዎች ምህረት እናሳያቸው ዘንድ እድል እናገኛለን። ለሰዎች ምህረት ማድረግ ኢየሱስን ለሰዎች እናደርስ ዘንድ በር ይከፍትልናል። ተስፋ አጥተው በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ የማውቃቸው ሰዎች ይኖሩ ይሆን? ______________________________
እነዚህ ሰዎች ላራሳቸው ምንም ማድረግ የማይችሉት እኔ አደርግላቸው ዘንድ የሚገባኝ ነገር ምን ይሆን? ______________________________
______________________________

**አስተያየት**

አሁንም በድጋሚ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች እንመለከታለን። በመንገዱ ላይ ለሞት በሚያደርስ ሁኔታ የተደበደበውን፣ልብሱን የተገፈፈውን፣የተደበደበውን፣ እና የተዘረፈውን ችግር ሰው በተለየ መልኩ እንመልከተው። ይህ ሰው የሚደርስለት ያጣ፣አቅም የሌለው፣የተራቆተ ደሃ የሚያድነው ምንም ተስፋ የሌለው ሰው ነው።

1. እራሴን ልክ እንደዚህ ሰው ተመልክቼ አውቅ ይሆን? ኃጢአት አካላዊ ብርታቴን ፣የገንዘብ አቅሜን፣በሰዎች ዘንድ ያለኝን ደረጃ፣እንደዚሁም ዓላማዬን እና በሰዎች ዘንድ ያለኝን ጠቃሚነት ዘርፎኝ ይሆን? በራሴው የኃጢአት ቦይ ውስጥ ተስፋቢስ ሆኜ ወድቄ ይሆን? የራሴን ህይወት ስመለከተው በምን አይነት መንፈሳዊ ውስጥ እሆን? እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግለፁ፡ ______________________________
______________________________
2. ጥላ ይታየኛል ልበል? ሊረዳኝ የቆመ ሰው መጥቶ ይሆን? አንድ ሰው በዚህ በወደኩበት ስፍራ አግኝቶኝ ይሆን? አንድ ሰው እየተንከባከበኝ ይሆን ፣በፍቅር እየተንከባከበ ኃዘኔን አባሮ፣ቁስሎቼን ፈውሶልኝ ይሆን? ማነው ለእኔ እንደ ደጉ ሳምራዊ የሆነልኝ? ወደዚህ የእረፍት ስፍራ ያመጣኝ ኢየሱስ ነው፡ እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ ግልፁ፡
______________________________
______________________________
3. ምህረት ማለት- ለአንዴና ለመጨሻ ጊዜ ኃጢአቴን የወሰደልኝ፣በደሌን የደመሰሰልኝ፣ብቁ ያደረገኝ፣ችግሮቼን ሁሉ ያስወገደልኝ፣ክፉ ነገሮችን በሙሉ የወሰደለኝ ያራቀልኝ? ይህ ነው ከወደኩበት የኃጢአት ቱቦ ውስጥ ስቦ ያወጣኝ አዲስ ህይወትን የሰጠኝ ? በህይወቴ የተከናወነው ምንድነው? ______________________________
______________________________

**<u>ምዕራፍ 5</u>**

**መልመጃ**

እግዚአብሔር ስለምህረት ይናገራል፡፡ እርሱ የምህረት አምላክ እንደሆነ ይናገራል እኛንም የምህረት ህይወት እንድንኖር ይፈልጋል፡፡ እስቲ ከታች የተዘረዘሩትን ስለ እግዚአብሔር ምህረት የሚናገሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተመልከቱ፡፡ ስለ እግዚአብሔር ምህረት እና አንዳችን ለአንዳችን ልናደርገው ስለሚገባ ምህረት ምን እንማራለን?

| **ስለ ምህረት እና ስለፍቅር የሚናገሩ ክፍሎች?** | እኛስ ምን እናድርግ |
|---|---|
| **መዝሙር** 23:6 | |
| **መዝሙር** 27:7 | |
| **ሉቃስ** 6:36 | |
| **መዝሙር** 52:8 | |
| **ዘዳግም** 4:31 | |
| **መዝሙር** 103:11 | |
| **ሆሴዕ** 6:6 | |
| **ማቴዎስ** 5:7 | |
| **ሚኪያስ** 6:8 | |
| **ኤፌሶን** 2:4 | |

**ማሰላሰል**

ኢየሱስ እንደ ደጉ ሳምራዊ ወደ እኛ የመጣበትን እውነት በአእምሯችሁ ይዛችሁ እስቲ አሁን ኤፌሶን 2:4-5 አብረን እንመልከት፡፡ ይህ ክፍል የሚናገረው የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ እኛ የመጣበት ሁለት መንገዶች እነርሱም ምህረት (የተገባንን አለመቀበል) እና ፀጋ (ያልተገባንን መቀበል)፡፡ በዚህ ቃል

ሃሴት አድርጉ: "ነገር ግን እግዚአብሔር ______________ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥________________ ከትልቅ ______________ የተነሣ በበደላችን __________________ እንኳ በሆንን ጊዜ ____________________ ጋር ___________________ ሰጠን፥ ____________________ ድናችኂልና፥" ይህንን ቁጥር በደብተራችሁ ላይ ጻፉት ፣እስከ ዛሬ ምረት ያደረጉላችሁን ሰዎች ጻፉ እናንተም ለሌሎች ምህረትን ታደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር እድል እንዲሰጣችሁ ጸልዩ።

**ክለሳ**

1. እስቲ ኢየሱስ የተናገረው የሳምራዊውን ታሪክ በራሳችሁ ቃል ፃፉት: ___________________

   ________________________________________________________________________

2. ለዚያ ለተጎዳው ሰው ባልንጀራው የሆነው በታሪኩ ውስጥ የትኛው ሰው ነው? ____________

   ________________________________________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

1. ምህረት ያሳየው ሳምራዊው ሰው በመሆኑ እውነተኛ ባልንጀራ ሊባል የሚገባው እርሱ ነው። ምናልባት ይህ ሰው ልክ አንድ ሰው ለባልንጀራው የሚያደርገውን ነገር ነው ያደረገው ብለን ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን እስቲ የዚህ ሳምራዊ ባልንጀራ እንደሆናችሁ አስቡ። ህጉ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ነው የሚለው። እኔ እራሴን እንዴት ነው የምንከባከበው? ለራሴ ምህረት አደርጋለሁ? እራሴን ይቅር እላለሁ ? ለራሴስ እንክብካቤ አደርጋለሁ? ለራሴ መልካም ምርጫ እና መልካም ውሳኔ አደርጋለሁ? እራሴስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ምህረት ውስጥ እኖራለሁ? በዚህ ላይ የምጨምረው ሃሳብ :

   ________________________________________________________________________

2. እኔ መልካም ባልንጀራ ነኝን? ለማነው ምህረት የማደርገው? ለጎረቤቴ? በቢሮዬ አብረውኝ ለሚሰሩት? ልጄን ለሚያስተምሩት ሰዎች? ለአስቸጋሪው ሰው? የእኔ ምህረት የሚመነጨው እግዚአብሔር ለእኔ ካደረገው ምህረት የተነሳ መሆኑን ተገንዝቤ ለባልንጀራዎቼ ምህረትን አደርግ ይሆን? በዚህ ላይ የምጨምረው ሃሳብ: ______________________________

   ________________________________________________________________________

**ምዘና**

እስቲ ለልጆች፣ለትዳር አጋራችሁ፣ለጓደኞቻችሁ፣ወይንም ለሚቀርባችሁ ለአንድ ሰው የደጉን ሳምራዊ ታሪክ ንገሯቸው። ይህ ታሪክ ምን ማለት እንደሆነ እና ለእናንተ የሰጣችሁን ትርጉም አካፍሏቸው። ከዚያም ታሪኩን ለእናንተ ጋር አብረው እንዲያነቡ አድርጓቸው።

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ እጅግ ብዙ ጊዜ ለሰዎች ምህረት ላደርግ የምችልበትን እድል ሰጥተኸኛል፡፡ ነገር ግን በማይረቡ ምክንያቶች ምህረትን ማድረግ አልቻልኩም፡፡ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ፡፡ ምህረት የሚያስፈልጋቸውን ማየት ይሆንልኝ ዘንድ እንዳንተ ያለ በምህረት እና በርህራሄ የተሞላ ልብ ስጠኝ፡፡ አንተ ከወደኩበት ስፍራ ፈልገህ እንዳገኘኸኝ መረዳቱን ስጠኝ፡፡ የተጣልኩ እና ተስፋ ቢስ ነበርኩ ነገር ግን ምህረትህ በእኔ ላይ ገነነች፣በምህረትህም የራስህ አደረከኝ፡፡ ቆሻሻዬን ከላዬ አራግፈህ ከትቢያ ላይ አነሳኸኝ ነፍሴንም መለስካት፡፡ በደሌን ከእኔ ወስደህ በመስቀል ላይ ሰቀልከው፡፡ እዳዬንም ከፍለህ ነጻ አወጣኸኝ፡፡ በታላቁ ፍቅርህም ከአንተ ጋር ለዘላለም እንድኖር ህያው አድርገኸኝ፡፡ ላደረክልኝ ሁሉ ከምስጋና በቀር የምሰጥህ ምንም የለኝ ጌታ ሆይ ለዘላለም ተመስገን______________________________

______________________________________________________________________________

# ትምህርት ስድስት

# ደስም ይላቸው ጀመረው

## ሉቃስ 15:11-32 — የጠፋው ልጁን መመለስ የሚጠባበቅ አባት

---

**የትምህርት ስድስት ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 6: ሉቃስ 15:11-32

- ምሳሌው
- ወደ አእምሮው መመለስ
- በጉጉት የሚጠብቀው አባት
- ታላቅ ወንድሙ
- መንፈሳዊ እውነታዎች
- አስታውስ!
- የፍቅር ህግ

### *መግቢያ*

ይህ ታሪክ የሚነግረን ድርሻውን ተካፍሎ ስለኮበለለና ንብረቱንም አባክኖ ስለጨረሰ ልጅ ነው፡፡ የዚህን ልጅ ታሪክ ስታነቡ እራሳችሁን በዚህ ልጅ ታሪክ ውስጥ ታገኙታላችሁ፡፡ በአንድ በኩል የልጁን መምጣት በጉጉት የሚጠባበቀውን አባት ሩህሩህ ልብ ስትመለከቱ በሌላ በኩል ደግሞ በታናሽ ወንድሙ በተደረገለ አቀባበል እና መስተንግዶ የተበሳጨውን ወንድም ትመለከታላችሁ፡፡

ሉቃስ 15 ስታጠኑ የኢየሱስን ትምህርት ሲያዳምጡ የነበሩትን ታዳሚዎች አስታውሱ፡፡ ኢየሱስ ልክ እንደትንሹ ወንድም እንደጠፉ ለሚቆጠሩትን ቀራጮች እና ኃጢአተኞች ነበር ሲያስተምር የነበረው፡፡ ከእነዚህም መካከል ፈሪሳውያንም የሚገኙ ሲሆን በህዝቡ መካከል ሆነው ያጉረመርሙ ነበር፡፡ ይህን ምሳሌ ስናጠና ለአባትየው ሩህሩህ ልብ ትረኩረት መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ በዙሪያው ለነበሩት ሲናገር የነበረውን ምሳሌ በጥንቃቄ ስሙ፡፡

አባትየው ደስታውን እየገለጠ የነበረው “ልጄ ሞቶ ነበር እነሆነ አሁን በህይወት አለ፣ ጠፍቶ ነበር ተገኝቷልም” በማለት ነበር፡፡ ታላቁን ልጁንም ወደ ደስታው እንዲቀላቀል “ወንድምህ ጠፍቶ ነበር እነሆ ተገኝቷል ፣ሞቶም ነበር እነሆ ተነስቷል” ስለዚህ ከእኛ ጋር ደስ ይበልህ እያለ ያበረታታው ነበር፡፡

## ትምህርት 6

**<u>ምዕራፍ 1</u>**

***መግቢያ***

ሉቃስ 15 ኢየሱስ ለተከታዮቹ የተናገራቸውን ብዙ ምሳሌዎችን የሚገኙበት ክፍል ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች የኢየሱስ ተከታዮች እነማን እንደነበሩ ይነግሩናል፡፡ በቁጥር 1 ላይ እንደዚህ ተብሎ ተነግሮናል "_________________________እና_________________________ ሁሉ ሊሰሙት ወደ እርሱ ይቀርቡ ነበር፡፡ሌሎች ደግሞ ሊተቹት እና ሊነቅፉት ይከተሉት ነበር፡፡ እነርሱም _________________________እና _________________________ነበሩ፡፡ በሉቃስ 19፡7 ላይ ኢየሱስ ወደ ዘኬዎስ ቤት ሲገባ እነዚህ _________________________የሚባሉት ሰዎች እንደነበሩ ታስታውሳላችሁ፡፡ ኢየሱስ የ_________________________ወዳጅ ስለሆነ ያጉረመርሙ ነበር፡፡ ፈሪሳውያን እና የህግ መምህራን ኢየሱስ ከሚያስተምረው ትምህርት ይልቅ የሚያበሳጫቸው ውሎው ከኃጢአተኞች እና ከቀራጮች ጋር መሆኑ ነበር፡፡

***መልመጃ***: ከቁጥር 3 ጀምሮ ኢየሱስ ሶስት የተለያዩ ምሳሌዎችን ይነግረና፡

1. የጠፋው________________ ምሳሌ (ቁጥር 3-7) በቁጥር 7 ላይ ያለው ትምህርት:________
________________________________________________________________________
2. የጠፋው ______________ምሳሌ (ከቁጥር 8-10) በቁጥር 10 ላይ ያለው ትምህርት:
________________________________________________________________________
3. በቁጥር 11 ላይ የሚገኘው የጠፋው ____________________ ፡፡ የትምህርት 6 ዋና ትኩረት በዚህ ምሳሌ ላይ ይሆናል፡፡

**የቤት *ሥራ***: ሉቃስ 15፡11-16 አንብቡ፡፡

- ልጁ ምን ነበር የፈለገው?
- ምን ነበር አባትየው የሰጠው?
- ልጅየውስ ምን አደረገ?
- የልጁ ነገር የት ላይ ተደመደመ?

***መልመጃ***:

1. በቁጥር 11 ላይ ምን ተነገረን? ________________________________________________

2. ታናሹ ልጅ ለአባቱ ምን ነገረው(ቁጥር 12)? ________________________________________

________________________________________________________________________

3. አባትየውስ ምን አደረገ (ቁጥር 12)? ________________________________________

4. ልጁስ ምን አደረገ (ቁጥር 13)?

   ሀ.________________________________________________________________

   ለ. ________________________________________________________________

   ሐ. ________________________________________________________________

5. ያለው በሙሉ ከእጁ አለቀ ። ገንዘቡን በሙሉ ጨረሰ ። ከዚያስ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 14)?

________________________________________________________________________

6. የዚህ ልጅ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 14)? ________________________________

7. ምን ሊያደርግ ወሰነ (ቁጥር 15)? ________________________________________

8. ምን አይነት ስራ አገኘ (ቁጥር 15) ? ________________________________________

9. እስቲ የነበረበትን የተስፋ  (ቁጥር 16): ________________________________________

________________________________________________________________________

**ገለፃ**

የኢየሱስን ታዳሚዎች እነማን እንደነበሩ አስታውሱ። ይሰሙት የነበሩት ቀራጮች እና ኃጢአተኞች ነበሩ። ይህንን ታሪክ ሲናገር የአድማጮችን ትኩረት ለማግኘት እንዴት መያዝ እንዳለበት አስቡ። ለአንዳንዶች የራሳቸውን የተበላሸ ታሪክ እየነገራቸው ነበር። ተስፋ የሌለው፣ በገንዘብ አቅማቸው የደቀቁ እና መጨረሻው የማይታወቅ ህይወት ነበር የሚመሩት። ህይወታቸውን ሊወጡበት የማይችሉት አዘዕቅት ውስጥ ያሉ በወጥመድ የተያዘ ህይወት እንዳላቸው እየተመለከቱ ነበር።

**ትምህርት**

ኢየሱስ ስለ አንድ አይሁዳዊ አባት እና ልጁ እየተናገረ እንደሆነ ልብ በሉ። ከአባቱ ቤት ጠፍቶ መሄዱ መጨረሻውን ከአሳማዎች ጋር እንዲውል አድርጎታል። በሙሴ ህግ መሰረት አሳማ ለመብል ከተከለከሉት የእንስሳት አይነቶች ውስጥ የሚበደቡ ናቸው። በሌዋውያን 11፡1-3፣7-8 ባለው ክፍል የተጠቀሰው እውነት ምን የሚል ነው?

1. ለምግብነት የሚውል ስጋ ምን አይነት መሆን አለበት (ቁጥር 3)?

   ሀ. ____________________________________________________________

   ለ. ____________________________________________________________

2. አሳማ መብላት ምን ችግር አለው (ቁጥር 7)? ________________________________

3. ከቁጥር 7-8 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምን አይነት መመሪያ ሰጥቷቸው ነበር? ______________________________________________

______________________________________________

ያለጥርጥር ፈሪሳውያን እና የሕግ መምህራን ቀራጮችን እና ሃጢአተኞችን እንደ እርኩስ ፣ሃይማኖት የለሽ እና ትዕቢተኞች አድርገው ነው የሚቆጥሯቸው፡፡

<u>ምዕራፍ 2</u>

**ገለፃ**

የዚህን ልጅ ታሪክ ስንመለከት በመጀመሪያው ትእይንታችን ላይ ይህንን ልጅ ምግባረ ብልሹ፣ወራዳ ፣ለአባቱ ፍቅር የሌለው ልጅ አድርገን ልንመለከተው እንችላለን፡፡ የዚህን ልጅ ታሪክ ስንመለከት ይህ ልጅ የአባቱን እና ያደገበትን ማህበረሰብ ባህል ሊረሳና ሊተው ወደ ሚችልበት እሩቅ ሃገር እንደ ኮበለለ እንመለከታለን፡፡ ከዚህ በኂላ ባደገበት ስርአት መኖር አይችልም፡፡ የአመፅና ያለመታዘዝ ምሳሌ ነበር፡፡ ለራሱ የኃጢአትን ህይወት መርጧል፡፡ ለገዛ ምኞቱ ባሪያ ሆነ ስለዚህም በባዶነት፣በውርደት እና በሽንፈት ውስጥ ተዘፈቀ፡፡

**የቤት ስራ**: አሁንም ምሳሌዎችን ማንበብ ቀጥሉ፡፡ ሉቃስ 15:17-24 አንብቡ፡፡

- ወደ አእምሮው ሲመለስ ምን ነበር ያስተዋለው?
- ምን ለማድረግ አሰበ?
- ለአባቱ ምን ሊነግረው ተዘጋጀ?
- አባቱስ ለልጁ ምን አይነት ምላሽ ሰጠው?

**መልመጃ**:

1. በቁጥር 17 ላይ ምን ተነገረን? ______________________________
2. ምን ተረዳ?
   ሀ. በአባቱ ቤት ስላሉ ባሮች? ______________________________
   ለ. ስለ ራሱ ______________________________
3. ምን አቀደ (ቁጥር 18-19)?
   ሀ. ወዴት ሊመለስ አሰበ? ______________________________
   ለ. ለአባቱ ምን ሊነግረው ተዘጋጀ?
      i. ______________________________
      ii. ______________________________
      iii. ______________________________

**ገለፃ**

ምን ተከሰተ? በዚህ ልጅ ህይወት ምን እየተከናወነ ነበር? ይህ የአቅጣጫ ለውጥ በዚህ ልጅ ህይወት ውስጥ ምን አመጣ? ወደ ቤት እንዲመለስ ሊለምና አባቱ በዚያ አብሮት አልነበረም። ወደ አእምሮው እንዲመለስ ሊያደርገው የሚችል የቅርብ ሰው ወይንም ዘመድ አልነበረም። በቁጥር 17 ላይ የሚያውቀውን ነገር አስታወሰ። የአባቱ ባሮች አሁን እርሱ ከሚኖረው ኑሮ የተሻለ እንደሚኖሩ አወቀ። ምግብ በልተው ይተርፋቸዋል። እርሱ ግን አሁን ምንም በእጁ ምንም የለውም!

ይህ ኮብላይ ልጅ ከዚህ በተጨማሪ ምን ማወቅ ቻለ? ይህ ልጅ ማነው? ካጠፋቸው ስህተቶች ሁሉ በላይ ይህ ልጅ ዛሬም ቢሆን ለአባቱ ልጅ ነበር። ለእርሱ እንደ አባቱ ቤት የሚሆንለት እንደሌለው ያውቃል! በልጅነት ውስጥ ምን አይነት ሃይል ነው ያለው! ልጅየው ያጠፋውን ጥፋት አስቦ ልጅ ሊባል እንደማይገባው አምኗል! ልጅ ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም እንኳን ከተስፋ መቁረጡ በላይ የአባት ፍቅር ምን ያህል ጠንካራ ነው! እርሱ ለአባቱ ልጅ ነው አባቱም ደግሞ ለልጁ አሁንም አባት ነው። በዚህ የኃጢአት እና የባርነት ኑሮ ውስጥ ቢኖርም እንኳን በዚህ በውድቀት ህይወት ውስጥ እየተመላለሰ ቢሆንም እንኳን በእርሱ እና በአባቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ምንም ነገር ሊያበላሸው አይችልም ነበር። ከአባቱ ጋር ያለውን የተበላሸ ግንኙነት ሊያድስ ከሚችልባቸው ነገሮች ሁሉ የልጅነት ግንኙነቱን የሚያክል ሊረዳው የሚችል ምንም ነገር የለም። ታሪኩ በቀጠለ ቁጥር ይህ እውነት እየጎላ ይመጣል።

**መልመጃ**:

1. ቁጥር 20 እንደሚነግረን "______________ ወደ አባቱ ______________።
2. ልጁ ተመልሶ ሲመጣ የአባትየው ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 20)?
   ሀ. ____________________________________________
   ለ. ____________________________________________
   ሐ. ____________________________________________
   መ. ____________________________________________
3. አባትየው የልጁን መምጣት ከርቀት ሲመለከት የነበረውን ስሜት ልብ በሉ። "እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና *አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው።*" በውስጡ ያለው ርህራሄ አባትየውን እንዲያመነታ እድል አልሰጠውም። ልጁ በደሉን ተናዘዘ። ልክ አባቴን እለዋለሁ ብሎ እንደተናገረው እንደዚያው ለአባቱ ነገረው። በኑዛዜው ምን እስከማለት ደረሰ? ቁጥር 21 ከ ቁጥር 18 እና 19 ጋር አነፃፅሩ ______________________________

   ____________________________________________
4. አባትየው ደስታውን መግለፅ ነበር የፈለገው! ለአገልጋዮቹ ምን የሚል ትእዛዝ ነበር የሰጣቸው (ቁጥር 22-23)?

ሀ. ______________________________________________ (የከብር ልብስ)

ለ. __________________________________________ (የውርስ ቀለበት)

ሐ. __________________________________________ (የክብር ጫማ)

መ. ______________________________________________

5. በቁጥር 24 መሰረት የዘፈኑ ፣የማሲንቆው ድምፅ ምክንያት ምንነበር? ድግሱና ፈንጠዝያው በምን ምክንያት ነበር? __________________________________________________

__________________________________________________

## ምዕራፍ 3

**ማሰላሰል** : የተደረገው ታላቅ ግብዣ ይመስለኛል!

**ክለሳ**

ሌሎች ምሳሌዎችን ከማየታችን በፊት ኢየሱስ ሲያስተምር የነበሩትን ሌሎች ታዳሚዎች እናስታውስ። ቀራጮች እና ኃጢአተኞች እንደነበሩ አውርተናል። ሉቃስ 15፡2 የኢየሱስን ታዳሚዎች እነማን እንደነበሩ ያስታውሰናል። ከቀራጮችና ኃጢአተኞች ውጪ እነማን ነበሩ? ____________እና __________። ስለምን ነበር እርስ በእርሳቸው የሚያንጎራጉሩት?____________________________

**የቤት ስራ**: ሉቃስ 15:25-32 አንብቡ።

- በዚህ ታሪክ ውስጥ አዲስ የተዋወቅነው ሰው ማነው?
- እየሆነ ለነበረው ነገር ምላሹ ምን ነበር?
- የአባትየው ምላሽ ምን ነበር?
- በዚህ ምሳሌ ውስጥ የተላለፈው ትምህርት ምንድነው?

**መልመጃ**:

1. እርሻው ውስጥ ሲሰራ የዋለው ማን ነበር (ቁጥር 25)? ____________________________
2. ወደ ቤት ሲመጣ ምን አይነት ድምፅ ሰማ? ______________________________
3. ከብላቴናዎችም አንዱን ጠርቶ። ይህ ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀ። እርሱም ፡-
   ________________በደኅና ________________ አባትህ ________________አረደለት አለው (ቁጥር 27)።
4. ታላቅ ወንድሙ ለዚህ ንግግር የሰጠው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 28)? ______________
   __________________________________________________
5. አባትየውስ ምን አደረገ (ቁጥር 28)? __________________________________

6. ይህ ልጅ ለአባትየው ምን አለው?

   ሀ. (ቁጥር 29) ______________________________________________

   ለ. ______________________________________________________

   ሐ. (ቁጥር 30) ______________________________________________

   መ. ______________________________________________________

7. አሁን ወደ አባትየው ልብ መጥተናል፡፡ ለታላቁ ወንድም ክስ የአባትየው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 31-32)? "እርሱ ግን፦ ልጄ ሆይ፥ _______________ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር _______________፥ ለ_______________ የሆነ ሁሉ የ_______________ ነው፤ዳሩ ግን _______________ሞቶ ነበረ _______________ ስለ ሆነ _______________ነበር _____________ደስ እንዲለን _______________ይገባናል አለው፡፡"

**ገለፃ**

ከቤት ያልኮበለሉና እና በቤታቸው ተረጋግተው የተቀመጡ ሰዎች የታላቅ ወንድምየው ስሜት ይገባቸዋል፡፡ ከአባቱ ጋር አብሮ ሃሴት ማድረግ ይከብደዋል፡፡ ምክንያቱም የሰባው ታርዶ እንዲህ ያለው ታላቅ ግብዣ መደረግ ያለበት ለእርሱ ነበር! ምክንያቱም በታማኝነት ያገለገለው እርሱ ነበር፡፡ የአባቱን ንብረት ከጋለሞቶች ጋር አላጠፋም፣በአባቱ ቤት ተረጋግቶ ተቀምጦ በእርሻው በትጋት ይሰራ የነበረው እርሱ ነበር፡፡ ስለዚህ ለታማኝነቱና ለትጋቱ የምስጋና ድግስ መደገስ የነበረበት ለእርሱ ነበር፡፡ ነገር ግን አባትየው በተለየ መንገድ ነበር ነገሩን የተመለከተው፡፡ አባትየው እጅግ ደስ ያለው የጠፋው ልጁ በደህና ወደ ቤቱ መመለሱ ነበር፡፡ ለዚህ ነው ድግስ ያዘጋጀው፡፡ ከዚህ ውጪ ማድረግ አይችልም ነበር ፡፡ለምን (ቁጥር 24)? ______________________________________________

**<u>ምዕራፍ 4</u>**

**ትምህርት**

በዚህ የጥናት ክፍል በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱትን ሰዎች በመመልከት ኢየሱስ በዚያ ታሪክ ምሳሌ ውስጥ ሊያስተላልፍልን የፈለገውን መንፈሳዊ መልእክት መመልከት ይገባናል፡፡

ሀ. <u>የጠፋው ልጅ</u> በውድቀት ህይወት ውስጥ ያሉትን እና ከሰማዩ አባታቸው ጋር ህብረታቸው የተቋረጠባቸውን ሰዎች ምሳሌ ነው፡፡ እርሱ ህይወታቸው የተበላሸባቸውን ሰዎች ምሳሌ ነው፡፡ እነርሱ ባሉበት የጉስቁልና ስፍራ ወደ አእምሮአቸው ተመልሰው ከእግዚአብሔር ጋር መስማማት እንዳለባቸው የሚወስኑ እና የአባታቸውን ቤት የሚናፍቁ ሰዎችን ይወክላል፡፡

ለ. <u>አባትየው</u> ደግሞ የሚወክለው እግዚአብሔርን ነው፡፡ የእርሱ እንደፈቃዱ እንድንሆን የፈጠረንን የሰማዩን አባታችንን ነው፡፡ የጠፋው ልጁ አንድ ቀን ተመልሶ ይመጣል በማለት ሁልጊዜ በደጅ ቆሞ ወደ እርሱ ቤት የሚወስደውን መንገድ በጉጉት እና በናፍቆት

የሚመለከተው አባት ነው፡፡  ገና በመንገድ ላይ ሳለ አባትየው እንደተመለከተው ከታሪኩ እንረዳለን፡፡ እስከመቼ ነው አባትየው የልጁን መመለስ የሚጠባበቀው?

ሐ. ታላቅ ወንድሙ ደግሞ የሚወክለው በእግዚአብሔር ቤት በትጋት እና በታማኝነት የሚያገለግሉትን ነገር ግን የጠፉት ፣በኃጢአት ወድቀው የነበሩት ወደ አባታቸው ቤት ተመልሰው ሲመጡ ከአባትየው ጋር አብረው ደስ የማይላቸውን ሰዎች ወይንም አማኞችን ናቸው፡፡ የእንደዚህ ዓይነት ሰዎች እያንዳንዱን ህግ ለመጠበቅ የሚታገሉ ናቸው፡፡ እንደ ወንድማቸው ኃጢአተኛ ባለመሆናቸው ሁለም የሚያደንቃቸውና ያለነቀፋ የሚኖሩ ናቸው፡፡

1. በቤት ውስጥ ያሉት ታማኝ ልጆች ለአባታቸው የማያቋርጡ የደስታ ምንጮች ናቸው፡፡ ነገር ግን አባት ዘጠና ዘጠኙን ትቶ አንዱን ፍለጋ መውጣቱ አይቀርም (ሉቃስ 15:4)፣ የጠፋው ድሪም እስኪገኝ ድረስ መፈለጉ አይቀርም (ሉቃስ 15:8)፣ የጠፋው ልጅ ተመልሶ እቤት እስኪመጣ ድረስ በር በሩን ማየቱን አይተውም (ሉቃስ 15:20)፡፡ ለቀራጮች እና ለኃጢአተኞች ይህ ታላቅ የምስራች ነው!  የምስራቹም:  በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ብሆን ፣ርቄ ብጠፋም፣የሰማዩ አባቴ እኔን ፈልጎ እስኪያገኘኝ ድረስ እረፍት የለውም፣ይፈልገኛል! እስቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁን ሃሳብ እና አመለካከት __________________________________________

________________________________________________________________

ለፈሪሳውያን እና ለህግ መምህራን ይህ ጉዳይ የሚዋጥላቸው አይደለም፡፡ በእነርሱ አመለካከት የተዛባ ፍርድ ነው፡፡ እነርሱ ፅድቅ የመሰላቸውን ነገር በሙሉ ለማድረግ ሲታገሉ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ ኢየሱስ እየነገራቸው ያለው የአብርሃም ፣የይስሃቅ ፣የያዕቆብ አባት የሆነው እግዚአብሔር ጠፍተው የነበሩት ስለተገኙ "ኑ አብረን ደስ ይበለን" እያላችሁ ነው የሚል መልእክት ነው የሚያስተላልፍላቸው፡፡ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ እና አመለካከት ግለፁ:  __________________________________________________

________________________________________________________________

### ከህይወት ጋር ማዛመድ

1. በዚህ ታሪክ ውስጥ የእናንተ ህይወት ከየትኛው ሰው ጋር ይመሳሰላል? _________________ የእናንተን ትኩረት በተለየ መልኩ ያገኘውስ ባለ ታሪክ ማነው?

   ______________________________________________________________

2. እየፈለጋችሁ እንደሆነና እስኪያገኛችሁ ድረስ እንደሚፈልጋችሁ ስትረዱ ኢየሱስ ወደ እናንተ ያመጣው የምስራች ምን የሚል ነበር?________________________________________

   ________________________________________________________________

3. መጥፋታችሁን እና ወደ አባታችሁ ቤት መመለስ እንዳለባችሁ ስትገነዘቡ አስቸጋሪ የሆነባችሁ ነገር ምን ነበር? ______________________________________________________

4. ከባልንጀሮቻችሁ ፣ከጎረቤቶቻችሁ፣እንደዚሁም ከቤተሰቦቻችሁ የገጠማችሁ አስቸጋሪ ነገር ምን ነበር?________________________________________________________________

5. የጠፋውን ለማዳን ከአባታችሁ ጋር በምን መልኩ ነው በተልእኮው ውስጥ የምትሳተፉት?______

_____________________________________________________________________________

### ክለሳ

አብዛኞዎቹ ኢየሱስ ያስተማረባቸው ምሳሌዎች መደምደሚያቸው እንደዚህ የሚለው የአባትየው ቃል ነው፡ "ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፣ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም።" በዚህ የክለሳ ምንባብ ውስጥ ይህንን የመሰሉ ቃላትን ወይንም ሃሳቦችን ተመልከት:

1. በዮሐንስ 3:16-17 ለኒቆዲሞስ ምን ነበር ያለው? ________________________________

_____________________________________________________________________________

2. በዮሐንስ 4:14 ለሳምራዊቷ ሴት ምን ነበር ያላት? ________________________________

_____________________________________________________________________________

3. በሉቃስ 19:10 ኢዩስስ ለዘኬዎስ ምን ነበር ያለው? ____________________________

_____________________________________________________________________________

### አስተያየት

አሁንም ደግመን ልንመለከተው የሚገባ አንድ ባለታሪክ አለ። እርሱም አባትየው ነው። አባትየው በፍለጋው ተልእኮ ውስጥ እንድንሳተፍ ይፈልገናል። እንደ አባትየው ለሌሎች ርህራሄንና ደግነትን እንድናሳያቸው በዙሪያችን ብዙ እድሎች አሉ። እስቲ እራሳችሁን ለአፍታ በሰማዩ አባቱ ላይ ፊቱን አዙሮ የነበረን የአንድ ልጅ መመለስ በጉጉት የምትጠባበቁ ሰዎች አድርጋችሁ አስቡ። ሁሉን ትታችሁ ለፍለጋ እና ለማዳን ጥሪ እንደደረሰው እና በመንፈስ ሙት የሆኑትን ስታገኙ ፈውስ ያገኙ ዘንድ ወደ እርሱ ወደ ሰማዩ አባታችሁ ይዝችሁ በደስታ እንደምትመጡ አስቡ። እስቲ በዚህ ላይ ያላችሁን ሃሳብ እና አመለካከት፡

_____________________________________________________________________________

<u>ምዕራፍ 5</u>

### ማሰላሰል

ጳውሎስ ወደ እምነት ቤተሰብ ከመምጣታችን አስቀድሞ የነበርንበትን ህይወት እንድናስብ ያበረታታናል። እስቲ ኤፌሶን 2:12 — 13 አንብቡት እና እነዚህን ቁጥሮች በደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው። ምክንያቱም እንድናስባቸው ተጠይቀናል! ቁጥር 12 የቀድሞውን ማንነታችንን እንድናስታውስ ያስታውሰናል፡

1. ______________________________ ክርስቶስ ነበራችሁ።

2. በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ____________________________
3. ለተስፋውም ቃል ኪዳን ____________________________ ሆናችሁ
4. ____________________________ ተለይታችሁ
5. በዚህም ዓለም ____________________________ አጥታችሁ

ሐዋሪያው ጳውሎስ ቁጥር 13 ላይ "አሁን ግን" በማለት ይቀጥላል። በአንድ ወቅት ህይወታችን እንደዚያ ነበር "አሁን ግን" የሚለው ቃል በእኛም ህይወት ሰራ። ህይወታችንም ተለወጠ። በቁጥር 13 ላይ ከክርስቶስ በፊት የነበራችሁን ህይወትና ክርስቶስን ካገኛችሁ በኂላ ያለውን ልዩነት አትዘንጉ። "አሁን ግን እናንተ ______________ ______________ የነበራችሁ ______________ሆናችሁ ______________ ______________።" ከዚህ በኂላ የተጣልኩ፣እንግዳ፣እና ባእድ አይደለሁም አሁን ግን ቤተሰብ ሆኛለሁ፣የቅርብ ሆኛለሁ ፣በሸፈነኝ በክርስቶስ ደም ቀርቤያለሁ። ሁላችንንም የክርስቶስ ደም ሸፍኖናል። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

## ትምህርት

ፈሪሳውያን አጉረመረሙ። የህግ መምህራንም አጉረመረሙ። አይሁዳውያን አጉረመረሙ። ኢየሱስ በሚያገለግልበት ስፍራ ሁሉ እየተከተሉ ያጉረመርሙ፣ትምህርቱን ይቃወሙና አገልግሎቱን ለማበላሸት ይጥሩ ነበር። እነርሱ የተጣበቁበት አንድ ሰው ወይን በሆነ ምክንያት የሙሴ ህግ ይለወጣል የሚል ፍርሃት ዘውትር ያስጨንቃቸው ነበር። ነገር ገን ኢየሱስ ህግን ሊሽር አልነበረም የመጣው (ማቴዎስ 5:17)። ነገር ግን ማንም ሰው ያልቻለውን እርሱ ፈፅሞታል። ማንም ሊፈፅመው ያልተቻለውን የፍቅርን ህግ እርሱ ፈፅሞታል።

ፈሪሳውያን እና የህግ መምህራን ሲያጉረመርሙ ቀራጮች እና ኃጢአተኞች ግን ወደ ቤታቸው ይጋብዙት ነበር። በእግሮቹ ስርም ተቀምጠው ትምህርቱን በጉጉት ይሰሙት ነበር። የት ናቸሁ? ብሎ የፈለጋቸውን ሰዎች ማንም እንዲፈርድባቸው እርሱ አይፈልግም ፣እኔም አልፈርድባችሁም ያላቸው ሰዎች ኢየሱስን ወደውታል የእነርሱ ህይወት በእርሱ ተነክቷል። "እኔም አልፈርድብሽም ፣ሂጂ ከአሁን ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአትን አትስሪ" (ዮሐንስ 8:10-11)።" ሌሎች ደግሞ ወደ እቅፉ ጠርቷቸዋል። "ኢየሱስ ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ። ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና።" በማለት ህፃናትን ወደ እርሱ ጋብዟቸዋል (ሉቃስ 18:16)።" በእስራት እና በድካም ውስጥ ያሉትን "አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል" በማለት ነፃ ያወጣቸዋል። በእርሱ ያመኑትን አይሁዳውያንን ደግሞ "እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኂል አላቸው...። እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።" በማለት አስተምሯቸዋል (ዩሐንስ 8:32, 36)።"

## ከህይወት ጋር ማዛመድ

እኛንም ሁላችንን ይጠራናል ይጋብዘናልም፡፡ ቤተሰብ እንሆን ዘንድም በመልካም ተቀብሎናል፡፡ በኃጢአት የቆሸሸው ታናሽ ወንድም ቢሆን ወይንም ደግሞ አግባብነት የሌለው ፍርድ ነው የተካሄደው ብሎ ያሰበው ታላቅ ወንድሙ ሁላችንንም እጆቹን ዘርግቶ በፍቅር ወደራሱ ይጠራናል፡፡ በደህና ወደ እርሱ በመምጣታችን እጅግ ደስ ይለዋል (ሉቃስ 15:27)፡፡

1. ከሰማዩ አባታችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙት ልባችሁን በምን አይነት ሽክም ሞላው?

    ________________________________________________

2. በምህረቱ እና በፀጋው ህይወታችሁን ሲነካው ከምን አይነት እስራት ተፈታችሁ?

    ________________________________________________

3. በቃሉ እውነት ነፃ በመውጣታችሁ ምክንያት እርሱ ስለእናንተ የሚዋጋው ውጊያ ምንድነው?

    ________________________________________________

## ፀሎት

"ቸር ነውና ምህረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑት" ይህንን የፀሎት ጊዜ እግዚአብሔር በህይወታችሁ ውስጥ ስለሰራው ድንቅ ነገር ለማመስገን ተጠቀሙበት…

1. በምህረቱ በህይወታችሁ ላይ ያለውን ሸክም ስላነሳላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት: ________

    ________________________________________________

2. ነጻ ስላወጣችሁ እና ፀንታችሁ መቆም ትችሉ ዘንድ አቅም ስለሰጣችሁ አመስግኑት: _________

    ________________________________________________

3. በቃሉ እውነት ውጊያችሁን ስለተዋጋላችሁ አመስግኑት:______________________________

    ________________________________________________

## ክለሳ

# ተልእኮአችን የሆነው የእግዚአብሔር ፍለጋ

እንኳን ደስ አላችሁ! *ተልእኮአችን የሆነው የእግዚአብሔር ፍለጋ* የሚለውን የጥናት ክፍል አጠናቃችኋል፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱ ሶስት በጣም ጠቃሚ ገፀ-ባህሪያት ጋር ተዋውቃችኋል፡፡ እንደዚሁም ከብዙዎቹ የኢየሱስ ምሳሌዎች ውስጥ ሶስቱን የማጥናት እድል አግኝታችኋል፡፡ ገና ከፍጥረት የውድቀት ዘመን አንስቶ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰውን ልጅ እየፈለገ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ሁሉም ይድኑ ዘንድ እና እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ ይፈልጋል፡፡ እኛንም የጠፋውን የማዳን ተልእኮ አካል እንዳደረገን እና የእርሱ ተልእኮ የእኛም ተልእኮ እንደሆነ አውቀናል፡፡ ይህ ግብዣ ጎረቤቶቻችንን ስንደርስ፣የእግዚአብሔርን ፍቅር ያሉበት ድረስ ይዘን ስንመጣ፣ እነርሱ ሊያደርጉ የማይችሉትን ነገር እኛ ከልባችን ስናደርግላቸው ይህ ግብዣ በህይወታችን ውስጥ አላማና ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ኃጢአተኞችን ስንቀርባቸው እንዲሁም አብረናቸው ስንበላ የእግዚአብሔር ፍቅር የማያዳላ፣በህግ ላይ ያልተመሰረተ ነገር ግን ለሁሉም በነፃ የተሰጠ መሆኑን እናውቃለን፡፡ ኢየሱስ ለዘኬዎስ የተናገረውን ቃል እኛም ደግመን ማለት እንችላለን “ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆነ” እንዳለው “እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ሊፈርድ ሳይሆን ዓለም በልጁ እንዲድን ነው!”

አሁንም እስቲ ጥቂት ነገሮችን በክለሳ መልክ እንመልከት፡፡ አስታውሱ ይህ ፈተና አይደለም ነገር ግን ይህንን አስደናቂ ጉዞ ስትጓዙ ምን ያህል እንዳተረፋችሁ ወይንም በህይወታችሁ ውስጥ ምን አይነት መሻሻል እንደመጣ ትገመግሙበት ዘንድ ነው፡፡ በጥናታችሁ ወቅት በታሪኮቹ ውስጥ ያለውን እውነታ እና በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ስላለው እውነታ ተምራችሁበታል፡፡ በ21ኛው ክፍለ ዘመን እነዚህን እውነታዎች በህይወታችሁ ውስጥ እንደምትተገብሩትም ተመልክታችኋል፡፡

1. ያጠናናቸው ሶስት ማንነቶች እነማን ናቸው ? ታሪካቸውስ የሚገኘው የት ነው? ሊታወስ የሚገባው እውነት መንድነው?

| ማንነት | ክፍሉ የሚገኘው | እውነታ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

2. ሶስቱ ምሳሌዎች ምንድናቸው? የት ነው የሚገኙት? ሊታወስ የሚገባው እውነት?

| ምሳሌዎች | የሚገኝበት ክፍል | እውነታ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

3. የተለያዩ ማንነቶችን ስታጠኑ ስለ ኢየሱስ ያገኛችሁት እውነታ ምንድነው?________________

_______________________________________________________________

4. ኢየሱስ ከእነዚህ ማንነቶች ጋር ሲታገል ስትመለከቱ ስለእግዚአብሔር ምን ተማራችሁ?______

_______________________________________________________________

5. ወደ ህይወታችሁ የሚመጡትን የተለያዩ ማንነቶች ስታስተናግዱ የምትከተሉት ተግባራዊ አካሄድ ምንድነው? _______________________________________________

6. ምሳሌዎችን ስታጠኑ በህይወታችሁ የቀረላችሁ ስለኢየሱስ የተረዳችሁት መረዳት ምንድነው?______________________________________________

7. ኢየሱስ በምሳሌዎቹ ሲያስተምር ስትሰሙ ስለ እግዚአብሔር ያገኛችሁ አንድ መረዳት ምንድነው?______________________________________________

____________________________________________________________

8. ወደ ህይወታችሁ የሚመጡትን የተለያዩ ማንነቶች ስታስተናግዱ የምትከተሉት ተግባራዊ አካሄድ ምንድነው? ______________________________________________

____________________________________________________________